

ዛሬም ባልተቃና ኑሮ ...

ገጽ 16



በተራቀቀ ቴክኖሎጂ የተደራጀው የአንድነት መኪና ማቆሚያ

ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 091 ታኅሣሥ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




# "ብልጽግና ፓርቲ ኢትዮጵያን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ለማሻገር የጀመራቸውን ስራዎች አጠናክሮ ይቀጥላል"

- የብልጽግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ብልጽግና ፓርቲ ፈተናዎችን ወደ ድል በመቀየር ኢትዮጵያን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ለማሸጋገር የጀመራቸውን ስራዎች አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ የፓርቲው ፕሬዚዳንትና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

ብልጽግና ፓርቲ 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የፓርቲው ፕሬዚዳንትና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት በሐዋሳ ከተማ ማካሄድ ጀምሯል፡፡

ከትናንት ህዳር 30 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በሚቆየው ጉባኤው ላይ አንድ ሺህ 116 የሚሆኑ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡

የፓርቲው ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንዳሉት፤ፓርቲው በአንደኛ ጠቅላላ ጉባኤው ላይ ያስቀመጣቸውን ውሳኔዎች በመፈጸም ረገድ በርካታ ስኬታማ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ከጉባኤው ወዲህ በሰሜን ኢትዮጵያ ለሶስተኛ ዙር የተቀሰቀሰውን ጦርነት ጨምሮ በርካታ ፈተናዎች ማጋጠማቸውን ጠቅሰው፤ ፓርቲው እነዚህን ፈተናዎች በድል በመሻገር አገርን ከፍ ያደረጉ ስኬቶችን ማስመዝገብ ችሏል ብለዋል፡፡

ለአብነትም በጉባኤው "ኢትዮጵያ ስንዴ ኤክስፖርት ማድረግ አለባት" የሚል ውሳኔ መቀመጡን ጠቅሰው፤ በዘንድሮው ዓመት ኢትዮጵያ የስንዴ ምርትን ለወጪ ንግድ ማቅረብ ትጀምራለች ብለዋል፡፡

ከዚህ አኳያ በፓርቲው 1ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን ገቢራዊ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባራት ፈተናዎችን ወደ ድል በመቀየር ስኬት ማስመዝገብ እንደሚቻል ትምህርት የሰጡ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

"ብልጽግና ፓርቲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ



Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


## የማይጨው ከተማና አካባቢው ዳግም የኤሌክትሪክ አገልግሎት አገኙ

-የሽሬና ሁመራ አካባቢዎች በቅርቡ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያገኛሉ

**አዲሱ ገረመው**

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በተሰራው የተቀናጀ ሥራ የማይጨው ከተማና አካባቢው ዳግም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማግኘታቸውን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በማይጨው

የማይጨው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በጦርነቱ የተጎዱ ዜጎችን መልሶ ማቋቋም ሥራ የሁሉንም ርብርብ እንደሚሻ ተገለጸ

**ማህሌት አብዱል**



ዶክተር አጊቱ ወዳጆ

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ለሁለት ዓመታት ሲካሄድ በቆየው ጦርነትና በተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶች የተጎዱ ዜጎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ የሁሉንም ርብርብ የሚያሻው መሆኑን ሆልስቲክ ፍሪደም ኢንተርናሽናል መስራች እና ፕሬዚዳንት ዶክተር አጊቱ ወዳጆ አስታወቁ፡፡ በሀገሪቱ እውነተኛ እርቅና ሰላም እንዲመጣም ሁሉም ጥፋቶች በግልፅ የሚነገሩበትና በጉዳዮች ይቅርታ

በጦርነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችን ማስቆምና ተጠያቂነትን ማስፈን ካልተቻለ ለሰላም ጠንቅ ይሆናል

-ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## የሕዝብን ጥቅምና መብት የማስጠበቅ ተግባር ባግባቡ ተግባራዊ አልተደረገም

- ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ አካባቢዎች እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችን ማስቆምና ተጠያቂነትን ማስፈን ካልተቻለ ለአገር ሰላም ጠንቅ ከመሆን ባሻገር በአለም አቀፍ ደረጃ እንደሚያስጠይቅ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንትና

እየተከሰቱ ያሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር




0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


ሞሮኮ በኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ የለውጥ ስራዎችን እንደምትደግፍ

አምባሳደር ኔዛ አሉዊ ገለጹ

ገጽ 3

# የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና በመጪው ሰኔ ወር በተመሳሳይ ጊዜ ይሰጣል

- 200 ሺህ የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፈተናውን ይወስዳሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ ተማሪዎች በአንድ ጊዜ እንደሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ ገልጸዋል። ፈተናውን 200 ሺህ የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፈተናውን እንደሚወስዱ ተመልክቷል፡፡

የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ ኤባ ሚጀና (ዶ/ር) በጉዳዩ ዙሪያ በተዘጋጀ አውደ ጥናት ላይ እንደገለጹት፣ የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና በመጪው ሰኔ ወር በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ ተማሪዎች በአንድ ጊዜ ይሰጣል።

የመጀመሪያው ፈተና በሰኔ ወር ከተሰጠ በኋላ ቀጣዩ የመውጫ ፈተና ከስድስት ወራት በኋላ እንደሚሰጥም ዶክተር ኤባ አስረድተዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና ብቃት ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይድ መሀመድ በበኩላቸው፣ ፈተናውን ለ200ሺህ የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ፈተናው ለሁሉም ተማሪዎች በኦንላይን እንደሚሰጥ የጠቀሱት አቶ ሰይድ፣ ይህም የፈተና ስርቆትን ለመከላከል የተሻለ አማራጭ በመሆኑ ነው ብለዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱም ሆኑ ተፈታኝ ተማሪዎች ፈተናው በተመሳሳይ ጊዜ በኦንላይን እንደሚሰጥ አውቀው ከወዲሁ ዝግጅት እንዲያደርጉም አቶ ሰይድ አሳስበዋል።

በመውጫ ፈተና ብቃትና የፈተና ኮርሶች ልየታና የተገቢነት ማረጋገጥ ዙሪያ በተዘጋጀው አውደ ጥናት ከሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መምህራን ተሳታፊ መሆናቸውን ከትምህርት ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

የመውጫፈተናዎችተገቢውንእውቀትክህሎትና ሰብዕና ያሟላ ምሩቅ ለማፍራት እንደሚያስችል የተገለጸ ሲሆን፤ መውጫ ፈተናው በምሩቃን ፕሮፋይል መሰረት ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃንን በማውጣት ጥራት ያለውና በአግባቡ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለገበያው ለማቅረብ እንደሚያስችል ታውቋል፡፡የመውጫ ፈተናው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ አቅማቸው እስኪጎለብትና አካዳሚክ እና ተቋማዊ ነጻነታቸው ሙሉ በሙሉ እስኪረጋገጥ ድረስም ፈተናው በጊዜያዊነት በትምህርት ሚኒስቴር እንደሚሰጥ ተገልጿል።

የመውጫ ፈተናው ከመጪው ሰኔ ወር ጀምሮ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ እንደሚሰጥ እና ለዚህም ተገቢው ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡



# በአዲስ አበባ ማንኛውም የቋሚ ንብረት ስም ዝውውር አገልግሎት በጊዜያዊነት ታገደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማንኛውም የቋሚ ንብረት ስም ዝውውር አገልግሎት በጊዜያዊነት መታገዱን የከንቲባ ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡

በከንቲባ ጽህፈት ቤት የካቢኔ ጉዳዮች ዘርፍ ኃላፊ አቶ ቢኒያም ምክሩ እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ከተማ ከሕዳር 29 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ ማንኛውም የቋሚ ንብረት ስም ዝውውር አገልግሎት በጊዜያዊነት ታግዷል፡፡

አገልግሎቱ የታገደው በከተማዋ ህገ ወጥነትን ለመከላከል እየተደረገ ያለውን ሒደት ውጤታማ ለማድረግ መሆኑን ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ለሁሉም ክፍለ ከተሞች እና ለሚመለከታቸው አካላትም የተላለፋው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዲሆን ትዕዛዝ መሰጠቱን መግለጻቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል፡፡

በቅርቡም በሀገር ደረጃ የፀረ ሙስና ትግል የሚያጠናክር ብሄራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አማካኝነት ተዋቅሮ ወደ ስራ መግባቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማም በከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ አማካኝነት አምስት አባላት ያሉት የፀረ ሙስና ኮሚቴ መሰየማቸው ይታወሳል፡፡ህብረተሰቡ በ9977 የነፃ የስልክ መስመር አስፈላጊውን ጥቆማና መረጃ በመስጠት ለፀረ ሙስና ትግሉ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማድረግ ከኮሚቴው ጎን እንዲቆም የከተማ አስተዳደሩ ጥሪውን ማቅረቡ የሚታወስ ነው፡፡

ሙስና በአገር ላይ እያስከተለ ያለውን አደጋ ለመታገልና ከምንጩ ለማድረቅ መንግስት ቁርጠኛ አቋም ይዞ ወደ ተግባር መግባቱን በቅርቡ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡

# በኳታሩ ዓለም ዋንጫ ኢትዮጵያ ራሷን አስተዋውቃለች

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኳታር ባስተናገደችው የ2022 ዓለም ዋንጫ ኢትዮጵያ "ኢትዮጵያዊነት" በተሰኘው የባህል ቡድን ራሷን ማስተዋወቅ እንደቻለች ተገለጸ፡፡ ቡድኑ ቆይታውን ጨርሶ ወደ አገር ቤት ተመልሷል፡፡



የኢትዮጵያዊነት የባህል ቡድን አስተባባሪ ወጣት ታምራት እሸቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቀው፤ ቡድኑ የማኅበራዊ የትስስር ገጾችን በሚከታተሉ የፊፋ ተወካዮች በተደረገለት ግብዣ አማካኝነት የ2022 የኳታር ዓለም ዋንጫ ላይ አገራቸውን በኪነ ጥበቡ ለማስተዋወቅ ወደ ስፍራው ማቅናታቸውን ገልጿል፡፡ ባሳዩት የባህል ትዕይንትም ኢትዮጵያን በሚገባ ማስተዋወቅ እንደቻሉ ተናግሯል፡፡

ወጣት ታምራት፤ ቡድኑ በሚችለው አቅም የአገርን ባህል ሊያስተዋወቅ የሚችል ዝግጅት አድርጎ ወደ ሥፍራው ማቅናቱን በማስታወስ፤ በተለየ አቅራረብና በአማረ ሁኔታ የኢትዮጵያን ባህል ለዓለሙ ማህበረሰብ ማቅረብ መቻሉን ነው የገለጸው፡፡ ይህም ተወዳጅነትንና ተቀባይነትን ያተረፈ እንዲሁም ሌሎች ዜጎች ኢትዮጵያን እንዲያውቁ ያደረገ መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ጠቅሷል፡፡

ኪነ ጥበብ ዓለምን አንድ የሚያደርግና የሚያግባባ ጥበብ እንደሆነ የተናገረው ወጣት ታምራት፤ ቡድኑ በዓለም የእግር ኳስ መድረክ ላይ ተሳትፎ ባሳየው የባህል ትዕይንት አበረታች ግብረ መልስ ከታዳሚያን ማግኘቱን አስታውቋል፡፡ ኢትዮጵያ በእግር ኳሱ ዓለም ትልቅ በሆነው በዚህ መድረክ ባትሳተፍም የባህል ቡድኑ አገርን ወክሎ ባህልን በማስተዋወቅ ረገድ የነበረው ሚና ከፍተኛ እንደነበር አመላክቷል፡፡

እንደ ወጣት ታምራት ገለጻ፤ ኳታር የዓለም ህዝብ በአንድነት የተገኘበት ቦታ ሲሆን፤ አገሪቷ ለዓለም ዋንጫው ልዩ ዝግጅት አድርጋለች፡፡ ከእግር ኳሱ ጨዋታ ባሻገር ልዩ ልዩ ትዕይንቶች የተስተናገዱበት የፌስቲቫል ሁነት እንዱ ሆኗል፡፡ ተጨዋቾች ወደ ጨዋታው ከመግባታቸውና ከእግር ኳስ ሜዳ ከወጡ በኋላ የተለያዩ ትዕይንቶች እንዲቀርቡላቸው ተደርጓል፡፡

ትዕይንቶቹን ካሳዩት አገራት መካከል ኢትዮጵያን የወከለው "ኢትዮጵያዊነት" የባህል ቡድን አንዱ መሆኑን የተናገረው ወጣት ታምራት፤ አንጋፋ እግር ኳስ ተጨዋቾች ትዕይንቶቹን በመመልከት በተንቀሳቃሽ ምስሎች ሲቀርጹና ሲያበረታቱ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ያላቸውን አድናቆት ሲገልጹ መቆየታቸውን ጠቅሷል፡፡

አገርን ወክሎ በእንዲህ አይነት ትልቅ መድረክ ላይ መገኘትና ከታደሚያን አዎንታዊ ምላሽ ማግኘት አስደሳች እንደሆነ በመግለጽ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተለያዩ አገራት የመጡ ዜጎች ለነበራቸው አቅባበል፤ በኳታር የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲና ኢትዮጵያዊያን ላሳዩት መልካም አቀባበል ምስጋና አቅርቧል፡፡

"እግር ኳስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ እንደመሆኑ ከተሳታፊ አገራት ባሻገር ከተለያዩ የዓለም አገራት የመጡ ተመልካቾች ተገኝተዋል፡፡ እድሉን በመጠቀም አገራችንን በሚገባው ደረጃ ማስተዋወቅ ችለናል፡፡ ኪነጥበብ የዓለም ቋንቋና መግባቢያ እንደመሆኑ እኛም የአገራችንን ሰንደቅ ዓላማና ባህሏን በማሳየት ኢትዮጵያ ራሷን እንድታስተዋውቅ አድርገናል" ብሏል ወጣት ታምራት፡፡

ኢትዮጵያ የምትባል አገር መኖሯን የማያውቁ እንዲሁም ኢትዮጵያን በአሉታዊ ጎን የሚረዱት የአንዳንድ አገራት ዜጎች ባህሏን ባዩ ጊዜ አስተሳሰባቸውን በመለወጥና ከኢትዮጵያ ጋር በመተዋወቅ ያላቸውን አድናቆት ቸረዋል ነው ያለው፡፡

"ውብ የሆነውን ባህላችንን አሳይተናል፡፡ ይህ ለአገራችን ትልቅ ግብዓት ነው፡፡ ቡድኑ በየጊዜው ራሱን በማሻሻል በእንዲህ አይነት ሁነቶች እየተሳተፈ አገርን በኪነጥበቡ ዘርፍ ለማስተዋወቅ ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡ ተሞክሮዎችን በመጠቀም በቀጣይ ለአገራችን የተሻለ አበርክቶ ይኖረናል" ሲል ተናግሯል፡፡

እድሉ የተገኘው በራሳችን ጥረት ነው ያለው ወጣት ታምራት፤ መንግስት የአገርን ገጽታ ሊያስተዋውቁ የሚችሉ ሁነቶችን በመከታተል እድሉን መፍጠር እንዳለበት ጠቁሟል፡፡ ከኪነ ጥበቡ ባሻገር ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚሄድበት ስፍራ አገሩን የማስተዋወቅ ኃላፊነትን እንዲወጣም አስገንዝቧል፡፡

ኢትዮጵያዊነት የባህል ቡድን ለኢትዮጵያ በአስፈላጊዋ ጊዜ በጥበብ በማገልገሉ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እውቅና ተሰጥቶት እንደነበር ይታወሳል፡፡ ቡድኑ በኳታር የነበረውን ቆይታ ጨርሶ ወደ አገር ቤት መመለሱም ታውቋል፡፡

# ሞሮኮ በኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ የለውጥ ስራዎችን እንደምትደግፍ አምባሳደር ኔዛ አሉዊ ገለጹ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ የለውጥ ስራዎችን ለመደግፍ ዝግጁ መሆኗን ሞሮኮ ገለጸች። በኢትዮጵያ ባለፉት አራት የለውጥ ዓመታት በዳያስፖራ ተሳትፎን እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችን እንደምታደንቅም አስታውቃለች።

በኢትዮጵያ የሞሮኮ አምባሳደር ኔዛ አሉዊ ሐምዲ እንደገለጹት፣ ሞሮኮ በኢትዮጵያ ባለፉት አራት የለውጥ ዓመታት በዳያስፖራ ተሳትፎ አማካኝነት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችን ታደንቃለች፣ በቀጣይነትም እየደገፈች በትብብር ለመስራት ዝግጁ ነች ብለዋል።

እንደ አምባሳደሯ ገለጻ፣ ሞሮኮ በኢትዮጵያ የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማሳደግ ትሰራለች፤ ባለፉት አራት የለውጥ ዓመታት የተከናወኑ ስራዎችን ታደንቃለች። በቀጣይነትም ለውጡ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ የበኩሏ አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ ነች።

አምባሳደሯ ከኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሙሐመድ እንድሪስ ጋር በመከሩበት ወቅት እንደገለጹት፤ ሞሮኮ ኢትዮጵያ የዳያስፖራ ተሳትፎን ማሳደግ የምትችልባቸውን ሁኔታዎች ለመደገፍ ዝግጁ ናት።

አምባሳደሯ በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት ሀገራቸው ሞሮኮ ከኢትዮጵያ ጋር የምትጋራቻው በርካታ እሴቶች መኖራቸውን ገልጸው፤ በዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ላይ የመስራት ፍላጎቱ የመነጨውም በእነዚህ



ምክንያቶች ነው ብለዋል።

ሞሮኮና ኢትዮጵያ በርካታ ቁጥር ያለው የዳያስፖራ ማህበረሰብና ዘርፉን የሚመሩበት ህጋዊና መዋቅራዊ ማዕቀፎች ያላቸው ሀገራት መሆናቸውን አስታውሰው፣ ሁለቱ ሀገራት ተቀራርበው መስራት ከቻሉ የጋራ ትብብር አስፈላጊነትን ከማጉላት ባለፈ የዳያስፖራ ተሳትፎ ተሞክሯቸውን ለመለዋወጥ መልካም ዕድል ይፈጥራል ብለዋል።

ሀገራቸው በዳያስፖራ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የፖሊሲ ማዕቀፍ አዘጋጅታ መስራት ከጀመረች ሰላሳ ዓመታት መቆጠራቸውን የጠቀሱት አምባሳደሯ፣ በኢትዮጵያም ባለፉት አራት ዓመታት የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማሳደግ የተከናወኑ ስራዎችን የሚደነቁ ናቸው። ስራዎንም በቀጣይነት ድጋፍ ለማደረግ ዝግጁ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሙሐመድ እንድሪስም በበኩላቸው አምባሳደሯ ስላስተላለፉት መልዕክትና ስለጉብኝታቸው አመስግነዋል።

ኢትዮጵያ የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማሳደግ ያከናወነቻቸውን ተግባራት ለአምባሳሯ በዝርዝር አስረድተዋል።

ከለውጡ ወዲህ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ስራዎች ትኩረት መሰጠቱም ባለፉት አራት ዓመታት በሁሉም ዘርፎች የዳያስፖራው ተሳትፎ በማደግ ላይ እንደሚገኝ ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

ዳያስፖራው ያለውን ዕምቅ አቅምና የሀገሪቱን ፍላጎት የሚመጥን የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማረጋገጥ ሞሮኮን ከመሳሰሉ ሀገራት ትልቅ ተሞክሮ መውሰድ እንደሚቻል ያላቸውን እምነት ዳይሬክተሩ ገልጸው፣ በሁለቱ ሀገራትና አቻ ተቋማት መካከል የተጀመረው ትስስር ተጠናክሮ እንዲቀጥል አገልግሎቱ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ለአምባሳደሯ አረጋግጠዋል።

# ከ80 በላይ አንጋፋና ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች ከ“ሰዋሰው” ጋር ተፈራረሙ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ከ80 በላይ አንጋፋና ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች አብረውት ለመስራት የውል ስምምነት መፈራረማቸውን ሰዋሰው መልቲሚዲያ አስታወቀ። በትናንትናው እለት ሰዋሰው መልቲሚዲያ የአልበም ምርቃት፣ የስምምነት ፊርማ ስነ-ስርአት እንዲሁም የክፍያ ስርአት (ፕሪምየም) ማስጀመሪያ መርሀግብሩን በአዲስ አበባ አከናውኗል።

በ“ሰዋሰው” መተግበሪያ አማካኝነት የሙዚቃ ሥራዎችን ለታዳሚያን በማቅረብ ላይ የሚገኘው ሰዋሰው መልቲሚዲያ እንዳስታወቀው፤ ከ80 በላይ አንጋፋና ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች ጋር በመፈራረም ወደ ስራ ገብቷል።

“ሰዋሰው” በዘርፉ ባለሙያዎች ተቀባይነት በማግኘቱ አንጋፋዋን ድምጻዊት ማሪቱ ለገሰን ጨምሮ ቴዎድሮስ ካሳሁን /ቴዲ አፍሮ/፣ አብነት አጎናፍር፣ ግርማ ተፈራ፣ ሔኖክ አበበ፣ ራሄል ጌቱ፣ ያሙሉ ሞላ፣ ለምለም ኃ/ሚካኤል፣ ብሌን ዮሴፍ፣ ዘሩባቤል ሞላ፣ ካሙዙ ካሳ እና ሌሎችም ከ80 በላይ አንጋፋና ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች ከ“ሰዋሰው” ጋር ለመስራት የስምምነት ሰነድ ፈርመዋል ነው የተባለው።

የሰዋሰው መልቲሚዲያ ስራ አስኪያጅ አቶ ሀብቱ ነጋሽ በፊርማ ስነስርዓቱ ላይ እንደተናገሩት፤ “ሰዋሰው” ተሰርተው የተጠናቀቁ የሙዚቃ አልበም ስራዎችን ገዝቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለታዳሚያን ከማድረስ በተጨማሪ ባለተሰጥኦዎች ችሎታቸውን ማውጣት የሚችሉበትን አጋጣሚ ይፈጥራል። የሙዚቃ ዘርፉ ተዋንያን በስራዎቻቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ዘመናዊ አሰራርም በማስተዋወቅ ላይ ነው።

እንደ ስራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ሰዋሰው መልቲሚዲያ በቴክኖሎጂ የታገዘ ፈጠራን በማሳደግ፣ ዘመናዊ አዳዲስ አሰራሮችን የማስፋፋት ዓላማውን ሰንቆ የተነሳ ሲሆን፤ በመዝናኛው ኢንዱስትሪ በምስራቅ አፍሪካ ተመራጭ ድርጅት የመሆን ራዕይ ያለው ነው። ላለፉት ሦስት ዓመታትም መተግበሪያውን በማበልጸግ ሐደት ላይ ቆይቷል።

የሀገራችን የኪነ-ጥበብ ውጤቶች ድንበር ተሻጋሪ ታዳሚያን እንዲያፈሩ የራሱን ከፍ ያለ ሚና እንዲጫወት ታስቦ የጎለበተ የ“ሰዋሰው” መተግበሪያ እውን መሆን የጥበብ አምራቾች ወይም አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ተስፈኛ ባለተሰጥኦ ወጣቶች እንዲሁም መላው የጥበብ አፍቃሪያን በጋራ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ነው ሲሉ ስራ አስኪያጁ ተናግረዋል።

ሰዋሰው የሙዚቃ ስራዎች የአከፋፋይ እጥረት ገደብ ሳይኖርባቸው በመላው ዓለም የሚደመጡበትን በጎ እድል ይፈጥራል ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ መተግበሪያው የኪነ-ጥበብ ኢንዱስትሪውን በተለይም የሙዚቃን ግብይት በማዘመን የዘርፉን ችግሮች በቴክኖሎጂ አዘምኖ በማቃለል ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተጠቃሚ ያደርጋል። በተጨማሪም የሙዚቃ ታዳሚው ጥራት ያላቸውን የተመረጡ ስራዎች በቀላሉ እና በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኝ ያግዛል ብለዋል።

እንደ ስራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ሰዋሰው ሁሉንም ዓይነት የጥበብ ዘርፎች ያለ ቦታ እና ሁኔታ ገደብ ለማቅረብ የሚያስችለውን አሰራርም ዘርግቷል። ትናንት የተመረቀው አልበም በአቀናባሪ እና ፕሮዲውሰር ካሙዙ ካሳ የተዘጋጀው “ሻኩራ” አልበም ጃሉድ አወል፣ ዘቢባ ግርማ፣ ዳግም ታምራት ደስታ፣ ራስ ጃኒ፣ ኒና ግርማ፣ ጂጂ ካሳን ጨምሮ 10 ድምጻዊያን የተሳተፉበት ነው።

የሙዚቃ ባለሙያው ካሙዙ ካሳ ከሰዋሰው ጋር በመስራቱ የተሰማውን ደስታና የሙዚቃ መተግበሪያው የድምፃውያን የዘመናት ጥያቄ የነበረውን የኮፒራይት ጥያቄ ምላሽ የሰጠና ልባቸውን ያሳረፈ ስለመሆኑም መስክሯል።

“ሰዋሰው” መተግበሪያ ዘመናዊውን የክፍያ ግብይት ‘ፕሪምየም’ ማስጀመሪያ መርሃግብር በእለቱ አከናውኗል። የሰዋሰው መተግበሪያ ደንበኞች በመተግበሪያው ላይ የሚለቀቁ ሙዚቃዎችን ለማድመጥ ካሏቸው አማራጮች መካከል አንዱ የሆነው ‘ፕሪምየም’ (በክፍያ ያለ ማስታወቂያ) የሚያደምጡበት አሰራር በይፋ ተጀምሯል።

‘ፕሪምየም’ ደንበኞች በተመቻቸው ዲጅታል የክፍያ አማራጭ ክፍያ ፈጽመው የሚያደንቋቸውን ድምጻውያን ስራዎች የሚያደምጡበት እና ከመደበኛ ታዳሚዎች የላቀ አገልግሎት የሚያገኙበት ነው።

ድምጻ መጻሕፍት (የመጻሕፍት ትረካዎች)፣ ፊልም፣ ቴአትር፣ ስዕል እና ሌሎችንም የጥበብ ውጤቶች በማገበያየት ታዳሚውን እና ባለሙያዎችን ተጠቃሚ የማድረግ ውጥኑን ይገፉበታል። ሰዋሰው መተግበር ሲስተም በማበልጸግ ዘመናዊ አሰራርን ተከትሎ የሁነት እቅድና ዝግጅት፣ ማስታወቂያ እና ፕሮሞሽን፣ ብራንዲንግ እና ሪብራንዲንግ፣ ውድድርና ሽልማቶች፣ ሚድያና ኮሚዩኒኬሽን ወደፊት በሰፊው የሚሰማራባቸው ዘርፎች ናቸው።

ትናንት የፊርማ ስነ-ስርአቱን ያካሄዱት ድምፃውያን ማሚላ ሉቃስ፣ ሔኖክ መሃሪ፣ ፍጹም አበበ፣ አበባው ጌታቸው እና ሌሎችም ናቸው።

# የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ተገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የብሔር ብሔረሰቦች በዓል የፌዴራሊዝም ሥርዓት ግንዛቤን በማስፋት ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ትልቅ ሚና እንዳለው በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግስትና የፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ኃይለየሱስ ታዬ ገለጹ፡፡

በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግስትና የፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ኃይለየሱስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ማኅበረሰቡ በብዝኃነት እና በአንድነት ላይ የሰፋ ግንዛቤ እንዲይዝ ያደርጋል፡፡ ከዚህም ባለፈ በጉዳዩ ላይ የመነጋገሪና መወያያ ሃሳቦች የሚንሸራሸርበት እና ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር መነሻ የሆነ ውይይት የሚካሄድበት ነው፡፡

በመሆኑም የብሔር ብሔረሰቦች በዓል የፌዴራሊዝም ሥርዓት ግንዛቤን በማስፋት ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ያስችላል፡፡

ዶክተር ኃይለየሱስ፤ ፌዴራሊዝም ከጽንሰ ሃሳቡ ጀምሮ ስለ አጠቃላይ ሥርዓቱ እንዲሁም በውጭ ሀገራት ስላሉ ተሞክሮዎች በመዳሰስ እና የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በመተንተን ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ በመግለጽ፤ በዓሉ እንደዚህ ዓይነት አስተምህሮዎችን ለማጋራት ትልቅ ዕድል የሚፈጥር መሆኑንም አንስተዋል፡፡

ፌዴራሊዝም ውስብስብ የሆነ የመንግሥት ሥርዓት በመሆኑ በአንድ ጊዜ ተገንብቶ የሚያልቅ አይደለም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ብዙ ብሔር ብሔረሰብ እና የተለያየ ብዝኃነት ባለበት ሀገር ውስጥ የፌዴራሊዝም ሥርዓት ከምንም በላይ ሚዛናዊነትን የሚጠይቅ ሥርዓት ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በፌዴራሊዝም ሥርዓት ውስጥ ከብዝኃነት ጋር ተያይዞ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህልና የመሳሰሉት ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀሬ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ኃይለየሱስ፤ እነዚህን ጥያቄዎች ሚዛን ጠብቆ ማስኬድ እንደሚጠበቅ እና ይህን ለማድረግም የሰፋ ግንዛቤ መጨበጥ እንዳለበት አስታውሰዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ማንነት ላይ ብዙ የተቀነቀነበት ጊዜ



ዶክተር ኃይለየሱስ ታዬ

ማለፉን አንስተው፤ ፌዴራሊዝም ሲባል የራስ እና የጋራ የሚባሉ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች መኖራቸውን በመጥቀስ እነዚህ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች ከሌሉ ጉዳዩ ፌዴራሊዝም ሊባል እንደማይችል ተናግረዋል፡፡

ሆኖም የተዛቡ አመለካከቶችን ለማረቅ አሁንም ችግሮች እንዳሉ በመጥቀስ፤ የፌዴራልዝም ሥርዓት በኢትዮጵያ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ ከአንድ ድርጅት ጋር ስለተያያዘ እና በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናትና ምርምሮች ውስን በመሆናቸው የተዛቡ አመለካከቶችን በፍጥነት ለማረቅ አዳጋች ሁኔታ መፍጠሩን ነው የተናገሩት፡፡

ሆኖም በፌዴራሊዝም ላይ ያሉ የተንሻፈፉ እይታዎችን ለማስተካከል እና ሚዛናዊ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን መከበርም መሰል ችግሮችን ለመፍታት አንዱ መንገድ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ እያንዳንዱ ብሔር የራሱን አኗኗር፣ አመጋገብና አለባበስ እና ማንነት አውጥቶ ማሳየቱ የአንድነቱ አካል ነኝ ብሎ እንዲያስብ ያደርገዋል፡፡ በዓሉ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ውስጥ የኔም ባህል፣ የኔም አስተሳሰብ እና የእኔም አኗኗር አንዱ ክፍል ነው የሚል እሳቤ እንዲኖር ስለሚያደርግ ፌዴራሊዝምን ለማስረጽ እንደሚረዳ ጠቁመዋል፡፡

ዜና

## የማይጨው ከተማና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከተማ የዝቅተኛና መካከለኛ መስመር ጥገናው ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ ከተማዋና አካባቢው በትናንትናው ዕለት ዳግም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማግኘት ችለዋል። የሽሬና ሁመራ አካባቢዎች በጥቂት ቀናት ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ የጥገና ሥራዎች እየተከናወኑ ነው።

በትግራይ ክልል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በተሰራው የተቀናጀ ሥራ የማይጨው ከተማና አካባቢው በትናንትናው ዕለት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማግኘታቸውን የገለጹት አቶ መላኩ፤ አገልግሎቱ በክልሉ ያሉ የመብራት አገልግሎት የተቋረጠባቸው ከተሞች ዳግም አገልግሎት እንዲያገኙ መጠነ ሠፊ ተግባራትን እያከናወነ እንዳለም አቶ መላኩ አመልክተዋል።

አቶ መላኩ፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን አንስተው፤ በዚህም ምክንያት በአማራና አፋር ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ያሉ ከተሞች ከዓመታት በላይ በዘለቀ ጊዜ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተቋርጦባቸው መቆየቱን ጠቅሰዋል። በተደረገው የሠላም ስምምነት ተቋሙ በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግና የተለያዩ የቴክኒክ ቡድኖችን በማዋቀር አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት በአስቸጋሪ የአየር ጸባይ ውስጥ ሆኖ በርካታ አካባቢዎች ዳግም የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ እየሰራ እንዳለ ገልጸዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት በሽሬ፣ ሁመራና አካባቢው የሚገኙ ከተሞች በዋነኛነት ሀይል የሚያገኙት ከተከዜ ሀይል ማመንጫ በተዘረጋላቸው ከፍተኛ የሀይል ማስተላለፊያ መስመር አማካኝነት ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በኩል የዝቅተኛና መካከለኛ መስመር ጥገናዎች ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቋል። በሁመራና አካባቢው የሚገኙ እንደነ ዳንሻ፣ ባከር፣ ማይካድራ፣ ሶሮቃ፣ አዲ ጎሹ፣ አዲ ረመጥ የመሳሰሉ አካባቢዎች የዝቅተኛና መካከለኛ መስመር ጥገናም ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቋል።

መስመሩ በዋነኛነት ከተከዜ በተዘረጋ ከፍተኛ የሀይል ማስተላለፊያ መስመር አማካኝነት የሚመጣ በመሆኑ ይህንንም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ጥገናውን ማከናወኑን አስታውቀዋል። በዚህም ከትናንት በስቲያ የሽሬ ከተማ ለሰዓታት ያህል የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዳገኘችና በከፍተኛ ሀይል ማስተላላፊያ መስመር ላይ ብልሽት በማጋጠሙ አገልግሎቱ እንደተቋረጠባቸው ገልጸዋል። በሁመራና አካባቢውም በተመሳሳይ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጎ በመስመሩ ችግር በማጋጠሙ አገልግሎቱን ማግኘት እንዳልቻሉ ጠቁመዋል።

ሽሬን እንዲሁም ሁመራና አካባቢው የሚገኙ ከተሞች ላይ የሚገኙ መስመሮች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ዳግም እንዲያገኙ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል የጥገና ባለሙያዎች ከአገልግሎቱ ባልደረቦች ጋር በትብብር እየሰሩ ይገኛሉ ብለዋል። አካባቢዎቹም በጥቂት ቀናት ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሚሆኑም ጠቁመዋል።

## በጦርነቱ የተጎዱ ዜጎችን መልሶ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚጠይቁበት ሥርዓት ሊፈጠር እንደሚገባም አመልክተዋል።

ዶክተር አጊቱ ወዳጆ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ ከሁሉም ጦርነት በኋላ ትልቁና ከባዱ ችግር ተፈናቃዮችን ወይም በግጭቱ ተጎጂ የነበሩ ሰዎችን መልሶ ማቋቋም ነው። ይህም በሀገር ኢኮኖሚ፤ ማህበራዊ ግንኙነትና ፖለቲካው ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ተጎጂዎቹን መልሶ የማቋቋሙ ሥራ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ ባለመሆኑ ሁሉም የሀገሪቱ ህዝብ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል።

«ይህንን ችግር ለመፍታት ከሴንትራል አሜሪካ ተሞክሮ መቅሰም አለብን ብዬ አምናለሁ» ያሉት ዶክተር አጊቱ፤ በመጀመሪያ የፖለቲካ አንጃዎች እርቅ ከፈፀሙ በኋላ እርዳታ አሰባስበው ተፈናቃዮችን መልሶ የማቋቋም ስራ በመስራታቸው መፈናቀሉ ሊያደርሰው የሚችለውን ከፍተኛ ችግር አስቀድመው ማስቀረታቸውን አመልክተዋል። በኢትዮጵያም ይህ አይነቱ ተሞክሮ ሊተገበር እንደሚገባ ጠቁመው፤ አሁን ላይ በዋናነት መሰራት ያለበት እዚህ ጉዳይ ላይ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በጦርነትና ግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎችን ከመሬት ጀምሮ የፋይናስ አቅርቦትና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ መልሰው ራሳቸውን እንዲያቋቁሙና ከተረጂነት እንዲላቀቁ ማድረግ እንደሚገባም ዶክተር አጊቱ ተናግረዋል።

በዚህ ስራ ላይ ራሳቸው የመሳተፍ ፍላጎት እንዳላቸው ጠቁመው፤ «ከዚህ ቀደምም ልምዱ ስላለኝ፤ ይህንንም በሚመለከት ከሶስት ዓመት በፊት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃሳብ ስላቀረብኩኝ ከመንግስት ጋር ሆኜ ድጋፍ ለማድረግ አቅጃለሁ» ብለዋል። ስለዚህ ይህ መልሶ የማቋቋም ስራ ከስኬት እንዲደርስም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የየበኩሉን ጥረት ሊያደርግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

አንዱ ገዢ መደብ ሌላን ወገን በመበደል አብሮ የመኖር እሴት እየተሸረሸረ የመምጣቱ ችግር ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን ያስታወሱት ዶክተር አጊቱ፤ በተለይም የነበሩት ነገስታት በህዝብ መካከል ልዩነት በመፍጠር ጥቂቱን ማህበረሰብ ብቻ ተጠቃሚ በማድረግ ሌላውን በገዛ ሀገሩ ባይተዋር እንዲሆን እድሉን በመፍጠራቸው እንደሆነ አስረድተዋል። «ይህ ነገር ደግሞ አሁን ላይ ተባብሶ በመሄዱ ቀድሞ የጋራ የምንላቸውና የምንግባባቸውን ማንነቶች እያሳጡን ነው የሚገኙት» ብለዋል።

በአንድ ብሔር ስም ጥቂቶች የሀገሪቱን ስልጣንና ሀብት በመቆጣጠር ሌላውንም የሚጨቁን ስርዓት በመዘርጋቱ አሁን ላይ ያለው ትውልድ በልዩነት ብቻ እንዲያምን መደረጉንም አብራርተዋል።

በዚህም ምክንያት ነው አሁንም ድረስ በየአካባቢው አንጃ ኃይሎችና ለነፃነት እታገላለሁ የሚል አካል እየተፈጠረ ያለው የሚሉት ዶክተር አጊቱ፤ «ለዚህም ብቸኛ መፍትሔው ችግሩን ፍርጥ አድርጎ አቅርቦ፤ ፈጣሪንም ሆነ ህዝብን ይቅርታ መጠየቅ ነው የሚገባው» ብለዋል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ከሁሉ በፊት ህዝቡ ራሱ ይቅርታ መደራረግና ልቡ መፅዳት አለበት። የቂምና በቀል አመለካከት መወገድም ይገባዋል። ከአመራር ጀምሮ እስከ ህዝቡ ድረስ ቅንነትን ማስተማር ይገባል። በተለይም መሪዎች አብሮ ለመኖር እንቅፋት የሆነ ህግም ሆነ አሰራር ካለ ለማስወገድ ፈቃደኝነቱና ተነሳሽነቱ ሊኖራቸው ግድ ይላል። ልክ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ህዝቡን በማስተማር መቀነስ እንደተቻለው ሁሉ፤ እርስበርስ የመጠፋፋቱና የመመቀኛኘቱን ክፉ ባህል ለማስወገድ ከላይ እስከታች ማስተማር ተገቢ ነው።

በዚህ ረገድ የምክክር ኮሚሽኑ መቋቋም ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ያነሱት ዶክተር አጊቱ «ከዚህ ቀደም የለመድነው እርቅ ያለፈው ሳይነሳ ዝም ብሎ ይቅርታ ተባባሉ የሚል ነው። ይሄ ግን ፈፅሞ የሚሆን አይደለም። ምክንያቱም ችግሩን አፍረጥርጦ ባለመወራቱና በዳይ ጥፋቱን አውቆ ይቅርታ ባለመጠየቁ ቁስሉ ዳግም ሲያገረሽ አይተናል» በማለት ተናግረዋል።

አሁን ላይ ሁሉም ችግሩን የሚያነሳበት መድረክ ከተመቻቸ፤ አጥፊውም ተለይቶ ይቅር እንዲባባል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ብለው እንደሚያምኑም አስረድተዋል። «በተለይ የቅሬታና የልዩነት ምንጭ የሆኑ ነገሮችን ወደፊት ለፊት በማምጣት መነጋገርና መተራረም አለብን» ብለው፤ ችግሩ የሚፈታበትንም መንገድ ህዝቡ ራሱ ሊያመጣ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

## “ብልጽግና ፓርቲ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብልጽግና ፓርቲ ከተመሰረተ ጥቂት ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በርካታ አባላትን በመያዝ ግን በአህጉር አቀፍ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠቀስ ፓርቲ መሆኑን ተናግረዋል።

ፓርቲው በአፍሪካ በህዝብ ቁጥር ቀዳሚ ከሚባሉ ሀገራት ተረታ የምትሰለፍ ሀገር እየመራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞም በቀጣይ በርካታ ስራዎች ይጠበቁበታል ነው ያሉት።

ለዚህ ደግሞ እውቀትና ክህሎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እርስ በርስ በመደማመጥ ልንሰራ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የማደግ ተስፋ ያላት ታላቅ ሀገር መሆኗን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ለኢትዮጵያ የእድገት ጉዞ እንቅፋት የሆኑ ትርክቶችን መቅረፍ እንደሚገባ አብራርተዋል።

በተለይ ያለፉ ታሪኮች የግጭትና መለያየት ምንጭ መሆን እንደሌለባቸው ነው ያስገነዘቡት።

ከትናንት ታሪኮች ትምህርት በመውሰድ እንዳይደገሙ መስራትና የተሻለ ነገን ለመገንባት በጋራ መቆም እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ያጋጠመንን ጦርነት በተቀናጀ መንገድ በጋራ መመከት እንደቻልን ሁሉ ለዘላቂ ሰላም መረጋገጥም የበኩላችንን ሚና ልንወጣ ይገባል ብለዋል።

ሌብነት ላይ የተጀመረው ትግልም ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል።

በቀጣይም የፓርቲው አባላት የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ወደ እድል በመቀየር የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት የተጀመሩ ስራዎች እንዲሳኩ በቁርጠኝነት መስራት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል።

በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው ላይ የሚቀመጡ አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ፓርቲው በቁርጠኝነት እንደሚሰራም አረጋግጠዋል።

ብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ በበኩላቸው፤ ፓርቲው ያካሄደውን አንደኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ተከትሎ ከህዝብ የተነሱ ጥያቄዎችን በመመለስ ረገድ ስኬታማ ስራ ማከናወኑን ተናግረዋል።

በተለይ የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል ከጊዜያዊ መፍትሄ ባሻገር እንደ ስንዴ ልማት ባሉ ዘላቂ መፍትሄዎች ላይ ከፍተኛ ስራ ተከናውኗል ነው ያሉት።

የፓርቲውን ውስጠ-ዴሞክራሲ የሚያጠናክሩ ስራዎችን በማከናወን ረገድም የተሻለ ስራ መከናወኑን ተናግረዋል።

ብልጽግና ፓርቲ ለዴሞክራሲ ተቋማት መጠናከር በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ ፓርቲው በአስቸኳይ ጉባኤው የምርጫ ቦርድ የሰጠውን የማስተካከያ ሃሳብ ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል ነው ያሉት።

## እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችን ማስቆምና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የክርክር ፍርድ ቤት የግማሽ ጊዜ ዳኛ አቶ ሰለሞን አረዳ ተናገሩ።

አግባብነት ያላቸው ህጎች የሕዝብን ጥቅምና መብት ለማስጠበቅ ሕጋዊ መሰረት ቢኖራቸውም ባግባቡ አለመተግበራቸውን የሰብአዊ መብት ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ አመለከቱ።

የኢትዮጵያ የፍትህ አካላት ዓለም አቀፉን የሰብአዊ መብት "ክብር ነፃነትና ፍትህ ለሁሉም" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት በአዲስ አበባ በጋራ አክብረዋል።

በዓሉን ያከበሩት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች፣ የፍትህ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽን ቢሮ በጋራ ናቸው።

አቶ ሰለሞን በመክፈቻ ንግግሩ ላይ፤ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር ተያይዞ እየተበራከተ የመጣውን ችግር መፍታት የመንግስት ግዴታ ነው፣ ባለድርሻዎች ከመንግስት ጋር በመተባበር ተጠያቂነትን ለማስፈን ትብብር ማድረግ ይገባቿል ሲሉ አሳስበዋል።

ባለፉት ሁለት አመታት የተካሄደው፣ ለበርካቶች ሞት፣ ጥፋትና ከፍተኛ ውድመት ያስከተለው ጦርነት በሰላም ስምምነት በመፈራረም በተቋጨበት እና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ በተፈረመበት 75ኛ አመት ላይ በአሉ መከበሩ ልዩ እንደሚያደርገው ተናግረዋል።

በሰብአዊ መብት ጉዳይ የሚካሄዱ ውይይቶች በየቦታው እየተፈጸሙ ለሚገኙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እጅግ ወሳኝ መሆናቸውንም አመልክተዋል።

የሰብአዊ መብት ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ በዓሉን አስመልክተው በበይነ መረብ ባስተላለፉት መልእክት፤ አግባብነት ያላቸው ህጎች የሕዝብን ጥቅምና መብት ተግባራዊ ለማድረግ ሕጋዊ መሰረት የሚሰጡ ቢሆንም ባግባቡ ተግባራዊ እንዳልሆነ አመልክተዋል።

በሰብአዊ መብት ጉዳይ የሚደረጉ ውይይቶች ለሕብረተሰብ ጥቅምና ግንዛቤን ይበልጥ ለማዳበር፤ ተግዳሮቶችን ለመጠየቅና ለተግባራዊነቱ ለመስራት እንደሚያበረታታ ጠቁመዋል።

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ሁሉም ሰው ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለውና ማንኛውም ሰው የአባላቱን የጋራ ወይንም ልዩ ጥቅም የሚመለከት ማህበር ወይም ተመሳሳይ ፍላጎት ያለው አባል የሕግ ፍትህ የማግኘት መብቱን መጠቀም እንደሚችል መቀመጡን ተናግረዋል።

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 1234/2013 ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶችን በሚመለከቱ፣ በጉዳዩ ላይ መብት ወይንም ጥቅም ባለው ሰው ወይንም ጉዳዩን ለማቅረብ በቂ ምክንያት ባለው አካል የሕዝብ ጥቅም ሙግት ወይንም ክስ በቀጥታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችልም በግልጽ እንደሚደነግግ አንስተዋል።

የፌዴራል ጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ የኢኮኖሚ አቅም የሌላቸው የሕብረሰብ ክፍሎች ድጋፍ አገልግሎት እንዲሰጡና የሕዝብ ጥቅም እንዲጠበቅ የሚያበረታታ መሆኑንም አንስተዋል።

አግባብነት ያላቸው እነዚህ ህጎች የሕዝብን ጥቅም ተግባራዊ ለማድረግ ሕጋዊ መሰረት የሚሰጡ ቢሆኑም፤ በኢትዮጵያ በህግ ባለሙያዎች፣ በሲቪል ማህበረሰብ ዘንድ ብዙም የዳበረ አለመሆኑን፣ በሰብአዊ መብት ጉዳይ የተሰሩ ጅምር ስራዎች ቢኖሩም በርካታ ቀሪ ተግባራት መኖራቸውን ጠቁመዋል።

የህዝብ ጥቅም ሙግት አጠቃላይ ማሕበረሰብን ወይንም የተወሰነውን ማሕበረሰብ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚከናወን ነው ያሉት ዶክተር ዳንኤል፤ ፍትህ የማግኘት መብትን በሕጋዊ መንገድ ወይንም በፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስከበር ተብሎ በአብዛኛው በፍርድ ቤትና በሌሎችም መድረኮች ጭምር የሚካሄድ ሙግት፣ ክርክር፣ ውትወታን የሚመለከት መሆኑንም ጠቁመዋል።

በተለይም የዳኝነት ወጪን ለመሸፈን ሲባል የሚከናወንና አቅም ለሌላቸው ሰዎች ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ጠቁመዋል። ድምጻቸውን ለማሰማት ለተቸገሩና ትኩረት ያልተሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፍርድ ቤትና ውሳኔ ሰጪ አካላት ጉዳያቸው በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ትኩረት እንዲያገኝና የሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል።

ግንዛቤ በማስጨበጥ፣ አጥፊዎችን ተጠያቂ ለማድረግ፣ ሌላ ጥፋት እንዳይከሰት ለመከላከል፣ ተጎጂዎችም መፍትሄ እንዲያገኙ ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ነው የጠቀሱት።

በአገር ውስጥ፣ በአህጉራዊና አለም አቀፍ ስርዓቶች ውስጥ ብቁ የፍርድ አሰጣጥና ውጤታማ መፍትሄዎችን ማጠናከር፣ ለስራ አስፈላጊ ግብአቶችን ማቅረብ ለሰብአዊ መብት መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ዘመናዊ አሰራሮችንም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

የቀዳሚ መጽሄት

# አገልግል



## ‹‹የቅሬታና የልዩነት ምንጭ የሆኑ ነገሮችን ወደፊት ለፊት በማምጣት መነጋገርና መተራረም አለብን››

- ዶክተር አጊቱ ወዳጆ

ገጽ 6

## ገበያ ወይስ ጣቢያ?

ገጽ 11



## ዛሬም ባልተቃና ኑሮ ...

ገጽ 16

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመታገል - ኮርፖሬሽኑ የያዘው ቆራጥ አቋም

የተለያዩ የማህበረሰብ ሳይንስ ባለሙያዎችና አለምአቀፋዊ ተቋማት ባደረጓቸው ልዩ ልዩ ጥናቶች፤ ሙስና ጠንቁ አደገኛ ዳፋውም ልጅ አዋቂ ሳይለይ ሁሉንም የሚያቀነጭር ክፉ ማህበራዊ ደዌ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ተጠቁሟል፡፡ በሙስና በተጠቁ የተለያዩ የዓለማችን ሀገራት በግልጽ እንደታየው፤ ሙስና በእርግጥም አንዲት ሀገርና ህዝቦቿ ለዘመናት ተሳስረው የቆሙበትን ሁለንተናዊ የአንድነት ገመድ ያለአንዳች ኮሽታ ቀስ በቀስ እየበላ፣ በጣጥሶ የሚጥል ማህበራዊ ብል ነው፡፡ በተለይ በአፍሪካ ጥቂቶች ከሀብት ላይ ሀብት እያካበቱ ሰፊው ማሕበረሰብ የበይ ተመልካች የሆነበት ሥርዓት በመስፈኑ ህዝቦቿ በእርስ በእርስ ጦርነት፣ ስደት፣ ረሃብ፣ መፈናቀል ወ.ዘ.ተ መታመሳቸው የዘወትር ዜና ነው።

በዚህም በአገራችን ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲመጣ ካደረጉ አስገዳጅ ምክንያቶች አንዱ በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረው ሙስናና ብልሹ አሠራር ነው። ይህንን የተረዳው የለውጡ ኃይልም በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረውን ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመቅረፍ በርካታ የፖሊስ ማዕቀፎች፣ የሪፎርም ማሻሻያዎች፣ የህግ፣ የአሠራርና አደረጃጀት ማስተካከያ እርምጃዎች ወስዷል። እየወሰደም ይገኛል።



**የውይይቱ ተሳታፊዎች፤**

ከሰሞኑም መንግሥት በጥናት በደረሰባቸው የመንግሥት ሹመኞች፣ የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞች፣ አቀባባዮችና ጉቦ ሰጪዎች ላይ ምርመራ እያደረገ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ሙስና በባሕርዩ በረቀቀ መንገድ፣ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ አንዳንድ ጊዜም በሕጋዊነት ሽፋን የሚካሄድ በመሆኑ በመንግሥት ጥናት የተደረሰባቸው አካላትን ብቻ ለሕግ በማቅረብ የሚፈታ አይደለም፡፡ ሙስናን ከሥር ከመሠረቱ ለመንቀል እንዲቻል ከሕግና ከአሠራር ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ የሙስና ተዋንያን ሁሉ ሙስናን እርም እንዲሉ የሚያደርግ ርምጃ ያስፈልጋል፡፡ መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የሚያስተባብር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የሚለይና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ አቋቁሟል፡፡

ተቋማትም በበኩላቸው የተደረጉ የሪፎርም ሥራዎችን ተቀብለው ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመቅረፍ እየተጉ ይገኛሉ። መንግሥት ከሰሞኑ በሙሰኞች ላይ እያደረገው ለሚገኘው ምርመራም ምቹ ሁኔታን እየፈጠሩና የበኩላቸውን ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ ። ከዚህ አንጻር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በኮንስትራክሽን ዘርፉ ከመሰማራቱ አንፃር ዘርፉ ለሙስና የተጋለጠ በመሆኑ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመታገል ሂደት ውስጥ የተቋሙ ሠራተኞችና አመራሩ ቁርጠኛ ሊሆኑ እንደሚገባ ተመላክቷል።

ኮርፖሬሽኑ 17 ኛውን የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን " ህብረ ብሔራዊ አንድነታችን ለዘላቂ ሰላማችን " በሚል መሪ ቃል እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ19ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ-ሙስና ቀንን " ሙስናን መታገል በተግባር" በሚል መሪ ቃል በተዘጋጁ ሰነዶች ዙሪያ የተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞች ተወያይተዋል ፡፡

በተዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ የኮርፖሬሽኑ ዋና ዳሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት እንደተናገሩት፤ በተለይ ቤቶች ልማት ዘርፍ ላይ ቤት ለማግኘት ተመዝግቦ ከሚጠባበቀው ሰፊ ህዝብ አንፃረ "ከሌብነትና ብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ ካልሠራን የሙስና ጉዳት ሁላችንንም የሚነካ በመሆኑ ይህን አፀያፊና ነውረኛ ድርጊትን በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባርም የሚታይ ትግል በማድረግ ማሳየት ይጠበቅብናል። የዘንድሮ በጀት አመት እቅድ ለማሳካት ከሙስናና ብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ ግቦቻችንን ለማሳካት የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች በሙሉ አቅም በፈቀደ መጠን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በማድረግ ለስኬታማነት መስራት አለበት፡፡

ሙስና ሀገርን የሚገድል፣ የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚጎዳና የሰላም እጦት መንስኤ ነው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን የሚበጀን ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አስቀጥለን ሀገራችን እንድትለማና ብልሹ አሠራር እንዲቀረፍ ቀን ከሌት መሥራት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። በተለይም በሰላም እጦት ያጣነውን ልማት እንዲያገግምና የህብረተሰባችንን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆንና መሬት እንዲነካ የመንግስት ሠራተኛው የድርሻውን መወጣት አለበት ብለዋል ።

የኮርፖሬሽኑ የእቅድና በጀት ዳይሬክተር አቶ አለማየሁ ደንቦባ በበኩላቸው፤ ለ17ኛ ጊዜ የሚከበረውን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን" አስመልክቶ የተዘጋጀውን የፓናል ሰነድ ያቀረቡ ሲሆን የኮርፖሬሽኑ የስነምግባር መኮንን አቶ ሙላቱ ደግሞ በሀገራችን ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ ሙስና ቀን “ሙስናን መታገል በተግባር “ በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀውን ሰነድ አቅርበዋል። በሰነዶቹ ላይም ሰፊ ውይይት ከመደረጉም በላይ ከተሳታፊ ሠራተኞች ለተነሱ ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች በመድረኩ አወያዮች እና አመራሮች ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል ።

በመጨረሻም በተደረሰ መደምደሚያ እንደ ተቋም ግልፅ የሆነ አሠራር መዘርጋት፣ የሥራ ሰዓትን ሳይሸራርፉና ሳያባክኑ በመሥራት ፣ ለደንበኞች ተገቢውን ክብርና አገልግሎት መስጠት ፣ ጥፋቶችን እየተራረሙና እያስተካከሉ በመሄድ፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን አጥብቆ መታገል እንዲሁም እንደ ኮርፖሬሽኑ የበጀት አመቱ እቅድ ለማሳካትና በከተማ አስተዳደሩ በቤት ኪራይ የሚሰቃየውን የመዲናዋ ነዋሪ ችግር ለመፍታት የተቋሙ ሠራተኞችና አመራሮች የጋራ መግባባት ላይ ደርሰው ውይይቱ ተጠናቋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «የቅሬታና የልዩነት ምንጭ የሆኑ ነገሮችን ወደፊትለፊት በማምጣት መነጋገርና መተራረም አለብን››

- ዶክተር አጊቱ ወዳጆ

ማህሌት አብዱል

የተወለዱትና ያደጉት በምዕራብ ወለጋ ነጆ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ነጆ ከተማ በሚገኘው የስዊዲን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ተከታተለዋል፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ግን ከአካባቢያቸው 76 ኪሎ ሜትር ርቀት በእግርና በበቅሎ እየተጓዙ ነው ጊምቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሩት፡፡ በጎንደር ጤና ኮሌጅ በኮሚዩኒቲ ነርስኒግ ዲፕሎማቸውን አግኝተዋል፡፡ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁም በቀጥታ ሚዛን ተፈሪ በሚገኘው ጤና ጣቢያ ተመድበው ለጥቂት ጊዜያት አገልግለዋል። ሆኖም በሴትነታቸው የደረሰባቸውን ትንኮሳ በመሸሽ የአገልግሎት ግዳጃቸውን ሳይጨርሱ ቦጂ በሚገኘው የመካነ-ኢየሱስ ክሊኒክ ማገልገላቸውን ቀጠሉ፡፡ እዛው ሳሉ የሕጻናት ሕክምና ስልጠና በስዊድን ልማት ድርጅት አማካኝነት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ወሰዱ፡፡

በመከላከያ ኢንዱስትሪም ተቀጥረው ለሰባት ዓመታት ያገለገሉት እኚሁ ሴት በዚህ ተቋም ውስጥ በነበሩ ባለስልጣናትና ካድሬዎች ተመሳሳይ ጾታዊ ትንኮሳ ችግር ስላጋጥማቸው ሥራውን ለመልቀቅ ተገደዱ፡፡ በመቀጠልም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው ሠሩ፡፡ ፈተናው ግን በሥራ ቦታ ብቻ አላበቃም፤ ከትዳር አጋራቸውም ጋር አለመግባባት ተፈጠረ፤ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳታቸውም እየጨመረ መጣ፡፡ በዚህ ግን ተስፋ አልቆረጡም፤ ሁሉንም ችግር በትዕግስትና በፅናት በመጋፈጥ በሥራም ሆነ በእውቀት ራሳቸውን በማጎልበት አጠነከሩ፡፡ ከራሳቸው አልፈውም ኢንተር አፍሪካ ኮሚቴ ኦን ትራዲሽናል ፕራክቲስ ተቀጥረው እየሠሩ ጎን ለጎን የራሳቸውንና ችግረኛ ሴቶችን የሚረዳ የበጎአድራጎት ድርጅት አቋቋሙ፡፡ በዚህም ድርጅት አማካኝነት ለበርካቶች የሥራ እድል መፍጠር የቻሉ ሲሆን በጭቆና ላይ ለነበሩ ሴቶች መልካም ምሳሌ በመሆንም ይታወቃሉ፡፡ ይሁንና ይህ የድጋፍ ሥራዎች አሁንም በወቅቱ በነበሩ የቀበሌ ካድሬዎች ከፍተኛ ችግር ይደርስባቸው ጀመር ፡፡ የድርጅቱን ሕንፃ ግንባታ ከማገድ ጀምሮ በነፃ የሚሠሩበትን የቀበሌ ቦታ ኪራይ ከማስከፈልና በእርዳታ ያገኟቸውን ማሽኖች እስከመውሰድ በመድረስ የሚረዷቸው ሴት ተበተኑ፡፡ የፅናት ተምሳሌት የሆኑት እኚሁ ብርቱ ሴት በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲቋቋም ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ጭምር ለመንግሥት ሃሳብ በማቅረብ አስተዋፅዖ ማድረጋቸው ይጠቀሳል፡፡

ነፃ የትምህርት እድል አግኝተው አሜሪካ ከከተሙ አሁን 27 ዓመታት አልፏቸዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት አምስት ልጆችን እያሳደጉ ከመጀመሪያ ዲግሪ ጀምሮ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ ድረስ መሥራት ችለዋል። በተጨማሪም እንደእርሳቸው በትዳር አጋራቸውና በሌላ አካል ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ስደተኛ ሴቶችን ለመርዳት አልቦዘኑም፡፡ በስደት ሃገር የራሳቸውን የበጎአድራጎት ድርጅት ከፍተው ስደተኞችን ይረዳሉ፤ ያስተምራሉ፤ በኢኮኖሚ ያቋቁማሉ፡፡ ከዚህም አልፈው ለስደተኞች እንቅፋት የሆኑ የአሜሪካ ሕጎች እንዲሻሻሉ ብርቱ ተጋድሎ በማድረግ ስኬታማ ሆነዋል፡፡

ሃገራቸውን ከልብ የሚወዱት እንግዳችን በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ወገኖቻቸውን ይደግፋሉ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ የከተማ ግብርና ዘርፍ ላይ ኢንቨስት ለማድረግና ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በጦርነት የተፈናቀሉ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን ድጋፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀምረዋል፡፡ ይህንን የሕይወት ውጣ ውረዳቸውን የሚያሳዩ ሁለት መጽሐፍትን ለንባብ ያበቁ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በኦሮምኛ እና በአማርኛ ቋንቋ በማስተርጎም ላይ ነው የሚገኙት፡፡ በዚህና በሌሎች ሃገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሆልስቲክ ፍሪደም ኢንተርናሽናል መሥራችና ፕሬዚዳንት ከሆኑት ዶክተር አጊቱ ወዳጆ ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡


ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፡- በሴትነትዎ ያጋጥምዎት የነበረው ችግር አሁን ለደረሱበት ስኬት ምክንያት እንደነበር በጻፉት መጽሐፍ ላይ አንስተዋል። እስቲ ያሳለፉትን ፈተና እና ያለፉበትን መንገድ ያስታውሱን ?**

**ዶክተር አጊቱ ፡-** በመሠረቱ በዚያ ጊዜ በነበሩት ከፍተኛ አመራሮች ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ ነበረኝ። ሆኖም በወቅቱ የነበሩት አለቃዬና ካድሬዎች በሴትነቴ እጅግ ያስቸግሩኝ ነበር። በሌላ በኩል አሁን ልገልፀው የማልችለው ነገር ግን በመጽሐፌ ላይ ያሰፈርኩት በትዳሬ ከፍተኛ አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። የነበረብኝ ከፍተኛ ተፅዕኖ ቢሆንም እንደአንድ ክርስቲያን ሴት መታገስ እንዳለብኝ በማመኔና ልጆቼ በንፁሕ አዕምሮ እንዲያድጉ በማለት ችግሩን በፀጋ ተቀበልኩት። እነዚያ ፈተናዎች ግን እኔን ቀረፁኝ እንጂ ወደኋላ አላስቀሩኝም። በዚህ ምክንያት እሠራበት ከነበረው የመከላከያ ኢንዱስትሪ ለቅቄ ባሌ ለአንድ ዓመት ሠራሁኝ፤ በመቀጠልም እርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒካል አገልግሎት ለአንድ ዓመት ሠራሁ። ኢንተርናሽናል ኮርዲኔቲንግ ኮሚቴ ፎር ዌልተር ኤንድ ዴቨሎፕመንት ፕሮግራምስ በሚባልና ማዘጋጃ ቤት ውስጥ የነበረ ድርጅት ለጥቂት ጊዜ ሠርቻለሁ።

ይሁንና በከፍተኛ ባለስልጣናት የነበረውን ሙስና በመቃወሜ ከሥራ አባረሩኝ። ግን ዝም አላልኩም፤ ከስሼ የአንድ ዓመት ደመወዜን እንዲሰጡኝ አድርጌያለሁ። በአፍሪካ ኢኮኖሚክስ ኮሚሽን ውስጥ ጎጂ ባሕላዊ ልማዶች አስተባባሪ ሆኜ ተቀጠርኩኝ። ይህም ብሔራዊ ኮሚቴውን ነበር የሚመራው። የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ በየክፍለሃገሩ እየዞርን የሃይማኖት መሪዎች፣ የሴቶችና የወጣቶች ተወካዮች፤ የጤና ባለሙያዎች በተገኙበት ወርክሾፕ እናካሂድ ነበር። በዚህም ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ችለናል።

እንዳልኩሽ የነበርኩበት ወጀብ ቀረጻኝና ለድሃ ሴቶች ሕይወታቸውን የሚለውጥ ሥራ እንድሠራ መንገድ ከፈተልኝ። በዚያ መነሻ የሴቶች ራስን መቻል ማኅበር የርዳታ ድርጅት አቋቋምኩኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ድርጅት ምንድን ነበር የሚሠራው?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** ይህ የእርዳታ ድርጅት በቆዳ ውጤት፣ ልብስ ስፌት እና በምግብ ፕሮሰሲንግ ሥራ በስፋት ይሠራ የነበረ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የስዊድን የበጎአድራጎት ድርጅት፤ ክርስቲያን ሪሊፍ ዲፕሎፕመንት አሶሴሽን፣ ካናዳ ኤምባሲ ፋኒ ሴፍ ኔዘርላድስና የአሜሪካ ኤምባሲ ድጋፍ አድርገውልናል። በተጨማሪም ሴቶቹ ምንም ገቢ ስለሌላቸው በክርስቲያን ሪሊፍ ዲቨሎፕመንት አማካኝነት ዱቄት፣ዘይት፣ብርድልብስ፣ጫማና ሳሙና እንሰጣቸው ነበር። የሰው እጅ እንዳያዩና ሠርተው ራሳቸውን እንዲለውጡ ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ። ከዚሁ ጎን ለጎን በራሳቸው እንዲተማመኑና ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ሥልጠናዎችም ይሰጣቸው ነበር።

እነዚህ ሴቶች በነገራችን ላይ በወሎ ድርቅ ጊዜ ተፈናቅለው ቀበሌው በሠራላቸው ጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ የሰፈሩ ነበሩ። እኔ ስደርስላቸው እዚያ ጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ ለ15 ዓመት በከባድ ችግር ውስጥ የኖሩ ናቸው። በወቅቱ ሴቶቹ ራሳቸውን ችለው ቤተሰቦቻቸውን እንዲረዱ የሚያደርግ ከፍተኛ ሥራ በመሥራታችን ደስተኛ ነኝ። ራስን ከመቻል ባለፈ የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ በምርታማነት ማሻሻያና በአነስተኛ ጥቃቅን ባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰለጥኑ አድርጌያለሁ። በመሠረቱ ምርታቸውም ከፋብሪካ ምርቶች ጋር የሚወዳደር ነበር። ሲመረቁ የተለያዩ ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ጋበዝኳቸው፤ እንግዶቹ ባዩት ነገር በጣም ተደሰቱ። ከዚያ ድርጅቴ በከፍተኛ ደረጃ ድጋፍ ያገኝ ጀመር። በየትልልቅ መድረኩ እየተጋበዝኩኝ ድርጅቱና የሴቶችን ሥራ እንዲሁም የወደፊት እቅዳችንን አቀረብኩኝ። ሕንጻ ለመገንባት የሚያስችለንንም ድጋፍ አግኝተን ነበር። ኒጀር ሄጄ ልምድ ከቀሰምኩኝ በኋላ የመንግሥት ለውጥ መጣ።

በኋላ ሁኔታዎች መቀየር ጀመሩ፤ ቀበሌ ውስጥ የነበረውን ድርጅት 350 ብር እንድንከፍል ተደረገ። ግን በወቅቱ የቀበሌ ቤት ከ150 ብር በላይ አይከራይም ነበር። ልክ ተሳክቶልን ሥራችን መጠናከር ሲጀምር የቀበሌው ካድሬዎች አላሠራ አሉን። የቀበሌው ሊቀመንበር ጠርቶኝ ሴቶቹ በምርጫ እነሱ የሚፈልጓቸውን ሰዎች ብቻ እንዲመርጡ ማስገደድ እንዳለብኝ ነገረኝ። እኔ በሁኔታው ስላላመንኩኝ እዚህ ነገር ላይ አልገባም በማለቴ ጠምደው ያዙኝ። ከዚያ ማሳደድ ጀመሩ፤ በኤክስፖ 93 ላይ ምርታችንን ለማቅረብ ነፃ በተሰጠን እድል እንዳንሳተፍ በወታደር ተከለከልን። ደግሞ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተሰጠንን ማሽኖችና መሣሪያዎች ቀሙን።

እያሳደዱኝ ቢሆንም ለሴቶቹ አዲስ ባንክ አካውንት ከፍቼ በኅብረት ሥራ ማኅበር አቋቁሜያቸው ራሳቸውን በራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ፤ ምርታ ቸውን እንዲሸጡ አስተምረን ነው እኔ ወደ አሜሪካ የሄድኩት። ከሄድኩኝ በኋላ ኪራይ አልከፈላችሁም ብለው አባረሯቸው። የነበሩት ወፍጮዎች፤ የስፌት መኪናዎቹንም ወሰዱባ ቸው። በዚህ ምክንያት ሴቶቹም ተበታተኑ።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲቋ ቋም ለመንግሥት ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ሰጥተው እንደነበር ሰምቻለሁ። እስቲ ስለዚህ ሁኔታ ያብራሩልን?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** በነገራችን ላይ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጥሬ በምሠራበት ጊዜ በርካታ ሃገራትን በመጎብኘት ተሞክሮ ቀስሜያለሁ። ከዚህም መካከል ኒጀር የቀሰምኩት ልምድ ላይ ተሞርኩዤ የሴቶች ጉዳይ ማቋቋም የሚያስችል ፕሮፖዛል ለመጀመሪያ ጊዜ አዘጋጀሁና በወቅቱ ለነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ አቀረብኩኝ። ለካስ እነሱ ‹‹አይሴማገን ምን እናድርግ›› ብለው ተጨንቀው ስለነበር ፕሮፖዛሉ ለጭንቀታቸው መፍትሔ ነው የሆነላቸው። ደግሞም ከነመዋቅሩ የሠራሁላቸው በመሆኑ በጣም ተደሰቱ። ሥራም የቀለላቸው በመሆኑ በሦስት ወሩ በሰጠኋቸው ፕሮፖዛል አማካኝነት ሚኒስቴሩ ተቋቋመና ወይዘሮ ታደለች ኃይለሚካኤል እንድትመራው ተደረገ። በተጨማሪም ከ15 ሰዎች ጋር በመሆን ሴቶችን በሚመለከት የወጡ የቀድሞ ሕጎች ላይ ጥናት አደረግን። ለምሳሌ ሴቶች እንዳይወርሱ የሚደነግገውን ሕግ እንዲቀየር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ነበረኝ። የሚገርመው በድሮ ሕግ እኔ የሆነ ሰው ቢደበድበኝና ጥርሴ ቢሰበር ካሳ ለባሌ እንጂ ለእኔ አይሰጥም ነበር። እናም እነዚህን የመሳሰሉ ሴቷን ማዕከል ያደረጉ ሕጎች እንዲሻሻሉ ነው የተደረገው።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ አሜሪካ የሄዱበት አጋጣሚ ምን ነበር?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** ነጻ የትምህርት እድል አግኝቼ ነው ወደ አሜሪካ ከእነልጆቼ ሄድኩት። በነገራችን ላይ ሀገሬን በጣም ነው የምወደው። ከዚህ ቀደም በተለያዩ የርዳታ ድርጅት ውስጥ በምሠራበት ጊዜ በርካታ የዓለም ሃገራት የመሄድ እድሉ ገጥሞኛል። ግን እዛ ለመቅረት አስቤ አላውቅም። በኑሮዬም ፈጣሪ ባርኮኝ ስለነበር የማማርርበት ምክንያት አልነበረም፤ መሰደድ አልፈልግም ነበር። የሚገርምሽ አሜሪካ ከሄድኩኝ በኋላ በየዓመቱ ነው ወደ ሃገሬ እመላለስ የነበረው፤ በዚህ ምክንያት ብዙ ጓደኞቼ ‹‹የኢትዮጵያን ባንዲራ ውጠሽ ነው እንዲህ የሚያመላልስሽ›› እያሉ ይተርቡኝ ነበር። ሆኖም መሄዴ ራሱ የፈጣሪ ፈቃድ ስለነበር ከነአምስት ልጆቼ ነው ያለምንም ማንገራገር የተቀበሉኝ። እዛም እንደሄድኩም የማውቃትና የረዳኋት አሜሪካዊት እዛ አገኛኋትና እሷም በተራዋ ሙሉ ቤቷን ለቃ ከነልጆቼ ተቀበለችኝ፤ ልጆቼንም ትምህርት ቤት አስገባችልኝ። በነገራችን ላይ ሜትሮ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ተመዝግቤ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



እየተማርኩኝ እዚህ እየተመላለስኩኝ የበጎአድራት ድርጅቴን እከታተል ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- አሜሪካ ሄደውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ከፍተዋል። ስመሆኑ በሰው ሃገር እንዲህ አይነት ድርጅት ማቋቋም ስምን አስፈለገዎት?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** አሜሪካ ያቋቋምኩት የበጎ አድራጎት ድርጅት በዋናነት በስደተኞች ላይ የሚያጠነጥንና ለመብታቸው የሚታገል ነው። ስደተኞችን ወክለን አለአግባብ የወጡ ሕጎች እንዲስተካከሉ ከፍተኛ ጥረት አድርጌያለሁ። ለምሳሌ ብጠቅስልሽ ገና በረቂቅ ላይ የነበረና ስደተኞችን የሚጎዳ ሕግ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ሳይፈርሙ በፊት እኔ ለሂላሪ ክሊንተን በቀጥታ ደብዳቤ ፃፍኩኝ። ያ ሕግ ቤጂንግ ዓለምአቀፍ ኮንፍራንስ ላይ ከፈረሙት ጋር የሚጻረር መሆኑን ጠቅሼ ነው የፃፍኩት። ሕጎችና ደንቦች ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት በሕዝቦች ላይ የሚያመጡት ተፅዕኖ መጀመሪያ እንዲጠና ያዛል። ሆኖም ይህ ባለመሆኑ ሕጉ ተግባራዊ ከሆነ ባልና ሚስትን፤ ልጆችን ከወላጅ የሚለያይበትን ሁኔታ እንደሚፈጥር በደብዳቤዬ ለማስረዳት ሞክሬያለሁ። የሚገርመው በዚያ ወቅት እኔ ገና ተማሪ ነበርኩኝ፤ ሊያውም ስደተኛ። ግን ሂላሪ ደብዳቤዬን ሳትንቅ በቀጥታ ለፕሬዚዳንቱ አስተላለፈች። በአጭር ጊዜ ፕሬዚዳንቱ ራሳቸው ምላሻቸውን ያለሁበት ድረስ በደብዳቤ አሳወቁኝ።

ከዚህም ባሻገር ሜኒሶታ ላይ ብቻ አራት ሕጎችን እንዲቀየር አድርጌያለሁ። በእርግጥ ብቻዬን አይደለሁም፤ ሌሎችንም ሰዎች በማስተባበር ጭምር ነው። ለምሳሌ አንዱ ሕግ በእኔ ላይ ከደረሰው ችግር አንጻር ተነስቼ ነው እንዲስተካከል ያደረኩት። ይኸውም እኔ እዚህ የተማርኳቸው ኮርሶችን እዛ ተቀባይነት አያገኝም ነበር። በዚህ ምክንያት ብዙ በስደት ያሉና ከአሜሪካ ውጭ የሰለጠኑ ነርሶች የሥራ ፍቃድ ማግኘት አይችሉም ነበር። በዚህም ከነርስ ረዳትነት ያለፈ ተምረው ከፍተኛ ደረጃ እንዳይደርሱ እንቅፋት ሆኖባቸው ነበር። እናም እኔን ያጋጠመኝ ችግር የነርሶችን ችግር እንዳውቅ ስላደረገኝ በዚህ ላይ ከሚሠራ ቡድን ጋር በመሆን የቀድሞውን ሕግ የሚያሻሽል ረቂቅ ሕግ አዘጋጀን። ረቂቁን ለምክር ቤቱ ከማቅረባችን በፊት ግን ድጋፍ ለማግኘት አስበን የነርሶች ቦርድ አመራር የሆኑትን ሴት በብዛት የሰለጠነ ኃይል እዛው እያለ ፊሊፒንስ ድረስ እየሄዳችሁ ለምን ነርሶች ትቀጥራላችሁ ብለን አነጋገርናቸው። በተለይ እኔ ይህንን ሕግ ቢያሻሽሉ በአንድ በኩል የባለሙያ እጥረታቸውን እንደሚቀርፉ፤ በሌላ በኩል ባሕላዊ የውድድር መንፈስ ትፈጥራላችሁ ብዬ ተሟገትኳቸው። በዚያ መሠረት የእኛም ጥያቄ አብሮ ለምክር ቤት እንዲቀርብ ተደረገ። እናም ሕጉ በምክር ቤቱ ተቀባይነት አግኝቶ 44 የሚሆኑ የአሜሪካ ግዛቶች ይህንን ሕግ ተግባራዊ አድርገውታል።

በቀጣይ ደግሞ የፀጉር ሹሩባ እየሠሩ በሚተዳደሩ ስደተኞች ላይ የነበረውና አላሠራ ያለ ሕግ እንዲሻሻል ነው የሠራነው። በአሜሪካ ሁሉም የፀጉር ባለሙያዎች ‹‹ኮስሞቶሎጂ›› የተባለ ፍቃድ ማግኘት አለባቸው። እኔ ደግሞ ለስደተኞች ሴቶች አንድ የሙያ ማዕከል ከፍቼላቸው ስለነበር ሹሩባ ይሠሩ ነበር። ይሁንና ፈቃዱ ስለሌላቸውና ሕገወጥ ነው ስለሚባል ተረጋግተው አይሠሩም ነበር። ሕጉ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ሹሩባ የሚሠሩትን አይመለከትም ነበር። ስለዚህ ይህም ሕግና የተቀመጡ መስፈርት ተገቢ አለመሆኑን በማስረዳት ሕጉ እንዲሻሻል በራሴ ተነሳሽነት ጥያቄ አቅርቤ በብዙ ሂደት ተቀባይነት አግኝቷል። በነገራችን ላይ አሜሪካ በሠራኋቸው ሥራዎች ምክንያት ‹‹ቡሽ ሊደርሽፕ›› በተባለ ተቋም ነጻ የትምህርት እድል አግኝቼ ኤግዚኪዩቲቭ ፓፕሊክ አፌርስ ዘርፍ ማስተርሴን መሥራት ችያለሁ። በተመሳሳይ የዶክትሬት ዲግሪዬን ደግሞ በክርስቲያን ሊደርሺፕ የሠራሁትም ነፃ የትምህርት ከነሙሉ ወጭዬ አግኝቼ ነው።

እኔም ብሆን የማገኘው የገንዘብ ድጋፍና ከመጽሐፍቶቼ የሚገኘውን ገቢ ለችግረኛና ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ድጋፍ የሚውል ይሆናል። በቀጣይ ስደተኛ ሴቶች በባሎቻቸውና በሌላ አካል ጥቃት ሲደርስባቸው የአደጋ ጥሪ በማድረግ ወዲያውኑ የሕግ አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በመተባበር ለማቋቋም ነው እቅድ ያለኝ። ለዚህም እንዲረዳ ሌላ‹‹ ሆልስቲክ ፍሪደም ኢንተርናሽናል›› የተባለ የበጎ አድራጎት ድርጅት እዛው አሜሪካ አቋቁሜያለሁ። ከመጽሐፌም ከሚገኘው ገንዘብ በየግዛቱ ነው የምናቋቁመው።

በመሠረቱ እዚህ ከፍቼው የነበረው ድርጅት ቢዘጋም አቅመ ደካሞችን መርዳት አላቆምኩም። በየጊዜው እየተመላለስኩኝ የበኩሌን ድጋፍ አደርግላቸዋለሁ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በከተማ ግብርና እና የጓሮ አትክልት ዓሳ እርባታ ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ ዝግጅት እያደረኩኝ ነው የምገኘው። ከዚህ ቀደምም አርጀ ጉደቱ መሬት ተመርተን ግን ተዘርፌ መጉላላት ደርሶብኛል። በአዲሱ ፕሮጀክቴ ገበሬውንም ሆነ ከተሜውን ገቢ በሚያስገኝ ሙያ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ነው እቅዴ። አሁን ላይ ደግሞ ገላን አካባቢ መሬት ተመርቻለሁ። እንዳልኩሽ ግን ከኢንቨስትመንቱም፤ ከእርዳታ ድርጅትም ሆነ ከመጽሐፍ ሽያጭ የሚገኘው የሃገሬን ሕዝብ ለመርዳት ነው የማውለው።

**አዲስ ዘመን፡- በሴትነትዎ በቤትም ሆነ በውጭ ያጋጠሞትን ተግዳሮት በጽናት በማለፍ ለስኬት ደርሰዋል። ሌሎች ሴቶች ከእርስዎ የሕይወት ተሞክሮ ምን ሊማሩ ይገባል?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** እኔን እዚህ ያደረሰኝ አንደኛ አማኝ ከሆነ ቤተሰብ ውስጥ ማደጌ ነው። እንደአንድ አማኝ ደግሞ እምነት፣ ተስፋ፣ ሁልጊዜ መልካም ማሰብ እና የመጣብኝን ፈተና ለበጎ ነው ብዬ መቀበል ነው ብዬ አምናለሁ። ሌሎች እህቶቼም ከዚህ ፈተና ውስጥ ምንድን ነው የምማረው? ብለው ማሰብ ይገባቸዋል። አስቀድሜ እንዳልኩሽ እኔ በደረሰብኝ መከራ ምክንያት ነው ለሴቶቹ ድርጅት እስከማቋቋም የደረስኩት። በተለይ ሌሎች እንደእኔ በፈተና ውስጥ ያሉና እያለፉ ያሉ ሴቶችን መምከር የምፈልገው መከራውን እያሰቡ ማማረር ሳይሆን፤ ከዚያ መከራ ወይም ችግር ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማየትና መፈለግ እንዳለባቸው ነው። ምክንያቱም በሚመጣብሽ መከራ አልቅሰሽ የምታተርፊው ምንም ነገር የለም። ታግለሽ ግን ብዙ ታተርፊያለሽ። ቀና ቀናውን በማሰብ መልካም ነገር ማምጣት ትቺያለሽ። በአጠቃላይ በእኔ በኩል አንደኛ የመጣብንን ነገር ማጉረምረሚያ ማድረግ ሳይሆን ማድረግ የሚገባን ከእሱ ውስጥ ምንድን ነው የማገኘው ብሎ መፈለግ ነው። በመሠረቱ በመጣብን መከራ ያለንን ነገር ጭምር ሊያሳጣን ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- የሕዝቡ ታቻችሎ የመኖር እሴት አሁን አሁን እየተሸረሸረ መጥቷል፤ በእርስዎ እምነት ይህንን እሴት እንዴት መመለስ ይቻላል?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** በእኔ እምነት ይህ ችግር ብዙ ክፍለ ዘመናትን ያስቆጠረ ነው። ነገሥታት በሕዝብ መካከል ልዩነት በመፍጠር ጥቂቱን ማኅበረሰብ ብቻ ተጠቃሚ በማድረግ ሌላውን በገዛ ሃገሩ ባይተዋር እንዲሆን እድሉን በመፍጠራቸው ነው። ይሄ አሁን ላይ ተባብሶ በመሄዱ ቀድሞ የጋራ የምንላቸውና የምንግባባቸውን ማንነቶች እያሳጡን ነው የሚገኙት። በአንድ ብሔር ስም ጥቂቶች የሃገሪቱን ስልጣንና ሃብት በመቆጣጠር ሌላውንም የሚጨቁን ሥርዓት በመዘርጋቱ አሁን ላይ ያለው ትውልድ በልዩነት ብቻ እንዲያምን አድርጓል። ለዚህም እኮ ነው በየአካባቢው አንጃ ኃይሎችና ለነፃነት እታገላለሁ የሚል አካል እየተፈጠረ ያለው። እኔ በመጽሐፌ ላይ እንዳሰፈርኩት ብቸኛ መፍትሔ ያለውን ችግሩን ፍርጥ አድርጎ አቅርቦ፤ ፈጣሪንም ሆነ ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ ነው የሚገባው። ከሁለት ዓመት በፊት ብሔራዊ የንስሐ የእርቅ ቀን እንዲዘጋጅ ለጠቅላይ ሚኒስትሩም ሀሳብ አቅርቤ ነበር።

መጀመሪያ ሕዝቡ ይቅርታ መደራረግ አለበት። ልቡ መፅዳት አለበት። የቂምና በቀል አመለካከት ማስወገድ ይገባዋል። ያ ባለመሆኑ ነው በየዘመኑ እርስበርስ መገዳደልና መጠፋፋት እያደገ የመጣው። አብሮ ለመኖር የማያስችሉ ሕጎችን በመቀየር ረገድ ቅን የሆነ አመራር ያስፈልጋል ባይ ነኝ። ለምሳሌ የአሜሪካ ሥርዓት ውስጥ ቅንነት አለ። እዚህ ሃገር ሕግ እንዲሻሻል የሚጠይቅ ሰው ሕገ-መንግሥቱን ተቋወሙ ተብሎ በክፋት ነው የሚታየው። በመሆኑም ከአመራር ጀምሮ እስከ ሕዝቡ ድረስ ቅንነትን ማስተማር ይገባል። ልክ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ሕዝቡን በማስተማር መቀነስ እንደተቻለው ሁሉ፤ እርስበርስ የመጠፋፋቱና የመመቃኛቱን ክፉ ባሕል ለማስወገድ ከላይ እስከታች ማስተማር ያስፈልጋል። አንድ የማንክደው ነገር የእያንዳንዱ የኢትዮጵያ መሪዎች ችግር ሙስና ሳይሆን ስልጣናቸውን ያለልክ መውደዳቸው ነው። ሕጉ ስልጣንን የሚነካ ከሆነ ማሻሻልም አይፈልጉም። አሁን ግን ከራሳቸው በላይ ለሕዝብ ሊያስቡ ይገባል። አብሮ ለመኖር እንቅፋት የሆነ ህግም ሆነ አሠራር ካለ ለማስወገድ ፈቃደኝነቱና ተነሳሽነቱ ሊኖራቸው ግድ ይላል።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ ካነሱት ሃሳብ ጋር በተያያዘ መንግሥት ሃገራዊ የምክክር ኮሚሽን አቋቁሟል፤ ይሄ ኮሚሽን ምን ፋይዳ ይኖረዋል ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** በእኔ እምነት የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ መቋቋም ትልቅ ፋይዳ አለው። ከዚህ ቀደም የለመድነው እርቅ ያለፈው ሳይነሳ ዝም ብሎ ይቅርታ ተባባሉ የሚል ነው። ይሄ ግን ፈፅሞ የሚሆን አይደለም። ምክንያቱም ችግሩ ተፍረጥርጦ ባለመወራቱና በዳይ ጥፋቱን አውቆ ይቅርታ ባለመጠየቁ ቁስሉ ዳግም ሲያገረሽ አይተናል። እንደእኔ እምነት አሁን ላይ ሁሉም ችግሩን የሚያነሳበት መድረክ ከተመቻቸ፤ አጥፊውም ተለይቶ ይቅር እንዲባባል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ብዬ አምናለሁ። በተለይ የቅሬታና የልዩነት ምንጭ የሆኑ ነገሮችን ወደፊት ለፊት በማምጣት መነጋገርና መተራረም አለብን። ችግሩን የምንፈታበትንም መንገድ ሕዝቡ ራሱ ነው ሊያመጣ የሚገባው። በነገራችን ላይ እኔ ተማሪ ሆኜም በየአካባቢው ማጉረምረሞች ነበሩ። ግን በተለይ ንጉሡ በጥበብ ቅሬታዎችን ለመፍታት ጥረት ያደርጉ ነበር። በመሠረቱ አሁንም ቢሆን የማይፈታ ችግር አለመኖሩን ሕዝቡን ማስተማር አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ባለው ግጭት በተለይ ሴቶችና ሕፃናት ናቸው ተጎጂዎች። ይሄ ግጭት በምን መልኩ ነው ሊፈታ የሚገባው?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** እኔ ይህንን ችግር ለመፍታት ከሴንትራል አሜሪካ ተሞክሮ መቅሰም አለብን ብዬ አምናለሁ። እነሱ ያደረጉት በመጀመሪያ የፖለቲካ አንጃዎች እርቅ ነው የፈፀሙት። ከዚያ በኋላ እርዳታ አሰባስበው ተፈናቃዮችን መልሶ የማቋቋም ሥራ ነው የሠሩት። እኛም ሃገር ይህ ነው መሠራት ያለበት። ከሁሉም ጦርነት በኋላ ትልቁና ከባዱ ችግር ተፈናቃዮችን ወይም በግጭቱ ተጎጂ የነበሩ ሰዎችን መልሶ ማቋቋም ነው። በእኔ እምነት አሁን ላይ በዋናነት መሠራት ያለበት እዚህ ላይ ነው። ለእነዚህ ሰዎች ከመሬት ጀምሮ ፤ የፋይናንስ አቅርቦትና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ መልሰው ራሳቸውን እንዲያቋቁሙና ከተረጂነት እንዲላቀቁ ማድረግ ይጠበቃል። በነገራችን በዚህ ሥራ ላይ እኔ ራሴ መሳተፍ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም ልምዱም አለኝ፤ ከመንግሥት ጋር ሆኜ ድጋፍ ለማድረግ ነው እቅዴ። ይህንንም ከሦስት ዓመት በፊት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃሳብ አቅርቤያለሁ። ስለዚህ ይህ ሥራ ሲጀመር እኔም ሆንኩ ሌላው ኅብረተሰብ የበኩሉን ጥረት ሊያደርግ ነው የሚገባው።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ በውጭ የሚኖሩ ጽንፈኛ ብሔረተኞች ሀገር ውስጥ ያለውን ማኅበረሰብ እርስበርስ በማጋጨት ላይ ተጠምደዋል። ለእነዚህ ዲያስፖራዎች ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ?**

**ዶክተር አጊቱ፡-** በጣም ትክክለኛ ሃሳብ ነው፤ ይህንን በሚመለከት መጽሐፌም ላይ አስፍሬያለሁ። እኔ በምኖርበት ሜኔሶታ ግዛት በርካታ ዲያስፖራዎች ለሃገር እድገት ገንዘብ ከመላክ ይልቅ በሐሰት ትርክት እርስ በርስ ሕዝብን ለማጫረስ በገንዘብ ድጋፍ እንደሚያደርጉ አውቃለሁ። የሚገርምሽ በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ ተመቻችቶለት የኖረ፤ የተማረና ልጆቹን አስተምሮ ለወግ ማዕረግ ያበቃ ሳይቀር እዛ ሄዶ መልሶ ሃገርን ለመውጋት የሚያሴርበት ሁኔታ አለ። እኔ በበኩሌ በዚህ ሁኔታ እጅግ አዝናለሁ፤ በኢትዮጵያዊነቴም የምኮራ በመሆኔ እንዲህ ዓይነት ሰዎችን በገሃድ ነው የምቃወማቸው። በተለይ የኦሮሚያ ክልል ተወላጆች ኦሮሚያን ነፃ እናውጣ እያሉ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ አልደግፍም። ምክንያቱም የኦሮም ሕዝብ በአፄ ምኒልክ ጊዜም ለሃገሩ ደሙን አፍስሷል፤ እስካሁንም ድረስ ለሃገሩ አንድነት እየተዋደቀ ያለ ሕዝብ ነው። የኦሮሞም ሆነ ሌላው ሕዝብ በባህልም ሆነ በደም የተሳሰረ ነው። ስለዚህ ይህንን በፍቅር የተጋመደ ሕዝብ በምን አይነት ሊያለያዩ አይችሉም። ለምሳሌ እኔ ጎንደር ለትምህርት ስሄድ ብዙ መጥፎ ነገሮች ተነግሮኝ ነበር፤ ሆኖም እዛ ከሄድኩኝ በኋላ የተነገረኝን ነገር ሕዝቡን ሆኖ ያገኘሁት የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ያለው ሆኖ ነው። እንዳውም እንግዳ ተቀባይና የፍቅር ሰዎች ነበሩ። አሁንም ሕዝቡ ዘንድ ያለው ይህ አይነቱ ፍቅር ነው። በመሆኑም እነዚህ ሕዝቡን የሚያባሉ ሰዎች ይህንን አውቀው ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ነው መልዕክት ማስተላለፍ የሚፈልገው።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር አጊቱ፡-** እኔም ሃሳቤን እንድገልፅ ዕድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ትኩረት ያላገኘው የሚጥል በሽታ

እፀገነት አክሊሉ

በዓለማችን ከ50 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች በሚጥል በሽታ ይጠቃሉ። ከእነሱ ውስጥ ደግሞ 80 በመቶ ያህሉ በአፍሪካ ውስጥ ናቸው። የሚጥል በሽታ (epilepsy) የአዕምሯችንን ሕዋሳት ከትክክለኛው ሥርዓት በተለየና በበዛ መልኩ ሲነቃቃ የሚከሰት በሽታ ሲሆን፤ አንድ ሰው የሚጥል በሽታ አለበት ለማለት ምልክቶቹ ቢያንስ ሁለት ጊዜ መከሰት ይኖርባቸዋል። በሽታው መታከም የሚችል በመሆኑም ታማሚውን ወደ ሕክምና ቦታ ማምጣት እጅግ አስፈላጊ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ የሚጥል በሽታ ተጠቂዎች የበሽታውን መነሻ ለማወቅ ይቸግራሉ። ነገር ግን የሚከተሉት ነገሮች ለበሽታው መከሰት የራሳቸውን አስተዋፅዖ ያበረክታሉ ተብሎ ይታመናል። ለምሳሌ፣ በቅርብ የቤተሰብ አባላት ላይ ተመሳሳይ በሽታ ካለ፣ ጭንቀት፣ ከመጠን በላይ ትኩሳት፣ በእናት የእርግዝና ወራት የተከሰቱ ችግሮች፣ በጭንቅላት ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም አደጋ፣ወደ ጭንቅላት የተሰራጨ ካንሰር፣የደም ውስጥ ስኳር መጠን ማነስ፣ የአደንዛዥ ዕፆች ተጠቃሚነት፣የማጅራት ገትር በሽታ፣ ተደራቢ በሽታዎችና ሌሎችም ለሚጥል በሽታ ምልክቶች ናቸው።

በሌላ በኩልም በሽታው በብዛት ሰውነትን የሚያንዘፈዝፍ ሲሆን በዚህ ጊዜ ታማሚዎች ራሳቸውን ይስታሉ። ዓይናቸውን ወደ ላይ ይሰቅላሉና አረፋ ይደፍቃሉ። በአንዳንድ የበሽታው ዓይነቶች ላይ ምልክቱ ከመታየቱ በፊት ራስ ምታት፣ ልብ የመምታት ስሜት፣ የእይታ ብዥታ ሊታዩት ይችላሉ። ይህም ከአንድ እስከ ሁለት ደቂቃ ሊቆይ ይችላል። ታማሚዎቹ ከነቁ በኋላ የሆነውን ነገር ለማወቅ እና ለማስታወስ ይሳናቸዋል። ለተከታይ ደቂቃዎችም ሽንትና ዓይነምድራቸውን መቆጣጠር ያስቸግራቸዋል ።

በሌላ በኩልም የሚጥል በሽታ በአንድ ሰው ላይ ተደጋግሞ ሲከሰት ከ30 ደቂቃ በላይ የሚቆይ ማንቀጥቀጥ፣ መገለልና መድሎ፣ የግጭት አደጋዎች፣ የአዕምሮ ዘገምተኝነት፣ ድንገተኛ ሞት አስከትሎ ይመጣል። እነዚህን አስከፊ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ለመቆጣጠር ምልክቶቹ በታዩበት ጊዜ በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ ሕክምና ማግኘት ያስፈልጋል።

ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር ውስጥ 1 ነጥብ 10 ሚሊዮኑ የሚጥል በሽታ ያለባቸው መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ። ከእነዚህ ታማሚዎች መካከል ደግሞ ስለ ችግራቸው ቀድመው ተረድተው የሕክምና ክትትል የሚያደርጉት ከ5 በመቶ አይበልጡም፤ ቀሪዎቹ 95 በመቶ የሚሆኑት ታማሚዎች ወደ ሕክምና ተቋም ሄደው አያውቁም ።

በኢትዮጵያ የሚጥል በሽታ በሰዎች ላይ ከፍ ያለ ችግርን እያስከተለ ያለ ቢሆንም ችግሩን የሚመጥን ሥራ ግን እየተሠራ አይደለም። ይህ መሆኑ ደግሞ በታማሚዎች ላይ ከፍ ያለ የጤና፣የማኅበራዊ ግንኙነት አልፎ ተርፎም ኢኮኖሚያዊ ችግርን እያስከተለ ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በመሆኑም፣”ኬር ኤፒሊፕሲ ኢትዮጵያ”ም በአገራችን ሕመሙ ያለባቸው ሰዎች ተገቢው ትኩረት ሳይሰጣቸው ለዘመናት እየተሰቃዩ የሚኖሩ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የችግሩ ተጠቂ በሆኑት ወይዘሮ እናት የውነቱ የተቋቋመ፤ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ተመዝግቦ በ2008 ዓመተ ምሕረትም ወደ ሥራ ገባ።

መንግሥታዊም፣ ሃይማኖታዊም ያልሆነው ኬር ኤፒሊፕሲ ኢትዮጵያ በሕመሙ ላይ በብቸኝነት የሚሠራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሲሆን፤ ሲመሠረት ይዞት የተነሳው ዓላማ በሚጥል ሕመም ምክንያት ለተሸነፉ ማንቂያ በመሆን ተስፋን እንዲሰንቁ ማድረግ፣ ከሕመሙ ጋር ሕልማቸውን እውን አድርገው ስኬታማ ሕይወት መኖር እንዲችሉ ማስገንዘብ፤ እንዲሁም ታማሚዎቹ በራሳቸው እንዲተማመኑ ማስተማር ነው። በሌላ በኩልም ድርጅቱ የመጀመሪያና ብቸኛ እንደመሆኑ ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ በተዋረድ ካሉ የጤና ኬላዎች፣ የክልል ጤና ቢሮዎችና ተዛማጅ ተቋማት ጋር አብሮ በመሥራት በሕመሙ ዙሪያ የተወሰነ ግንዛቤን በመፍጠር፤ ሕሙማኑ ስለ



ሲስተር ሃይማኖት አልታሰብ

> “የሚጥል በሽታ ሀገራችን ላይ በመንግሥትም ደረጃ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው ሁኔታ ትኩረት አግኝቷል ማለት ይከብዳል...”

እኛ የሚመለከተው አካል አለ ብለው እንዲያስቡና በተቻለ መጠንም በራሳቸው ለመቆም የሚያስችላቸውን የሕይወት ጥበብ እንዲቀስሙ ሲያደርግ ቆይቷል፤ እያደረገም ይገኛል።

በኬር ኤፒሊፕሲ ኢትዮጵያ ውስጥ በሄልዝ ኦፊሰርነት የሚሠሩት ሲስተር ሃይማኖት አልታሰብ ወደ እነሱ ተቋም ስለሚመጡት የሚጥል ሕመም ተጠቂዎች እንደሚናገሩት ከሆነ፣ የሚጥል ሕመምን በተመለከተ በአገራችን ያለው ግንዛቤ ገና እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ ታማሚዎቹም ገና ትምህርት ቤት እንኳን በቅጡ የሚሄዱበት ሁኔታ የለም፣ይሄዳሉ የተባሉትም ቢሆኑ ለእነሱ በሚሆንና ችግሩ ሲያጋጥማቸውም እንክብካቤ በሚደረግላቸው መጠን እየተማሩ አይደለም። በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ አልፈው ተምረው ሥራ ላይ ሲሆኑም የሚያጋጥማቸው ነገር በትምህርት ቤት ካሳለፉት ሁኔታ የሚለይ አይደለም።

እንደ ሲስተር ሃይማኖት ሙያዊ ማብራሪያ የሚጥል ሕመም ታማሚዎች እንደ ማንኛውም የስኳር አልያም የደም ግፊት ሕመም ታማሚዎች ተገቢውን የሕክምና ክትትል እያገኙ መኖር የሚችሉ ቢሆኑም እንኳን ኅብረተሰቡ ሕመሙን ከእምነትና አጉል ልማድ ጋር የሚያያይዘው በመሆኑ እንደ ማንኛውም ሰው በማኅበራዊ ሕይወት ለመሳተፍ፣ትዳር ለመመሥረት፣ ልጆች ለመውለድ ከፍ ያለ ችግር ያጋጥማቸዋል።

እነዚህ ነገሮች ሲያጋጥማቸው ደግሞ ተቋቁመው ማለፍ ስለሚሳናቸው ከፍ ወዳለ አዕምሯዊ ቀውስ ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ሊሆናቸው ይችላል። ይህንን ሁኔታ ለማገዝና ሕመሙ ያለባቸው ሰዎች እንደማንኛውም የሕመም ዓይነት ሕክምናቸውን እየተከታተሉ፤ መድኃኒታቸውን እየወሰዱ መኖር እንደሚችሉ ለማስገንዘብ ኬር ኤፒሊፕሲ ኢትዮጵያ ከፍ ያለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ነው።

ሲስተር ሃይማኖት እንደሚሉት ሕመሙ ያለባቸው ሰዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን በብቸኝነትና



አቶ ዐቢይ አሥራት

ድብርት ውስጥ ነው የሚያሳልፉት። ይህ ለመሆኑ ዋናው ምክንያት ደግሞ ሰዎች እኛን ሊቀርቡን፣ ጓደኛ ሊያደርጉን፣ ችግራችንንም ሊረዱልን አይችሉም የሚል፤ ከፍ ያለ ስነልቦናዊ ጫና ነው። በዚህ ምክንያትም ራሳቸውን ከማኅበረሰቡ ነጥለው ብቻቸውን ለመቀመጥ ነው የሚፈልጉት፤ እነዚህን ሰዎች ማገዝና መርዳት ስለሚያስፈልግ ድርጅቱ በሚችለው አቅም ሁሉ የምክር አገልግሎት ፕሮግራም በማውጣት ሥራዎችን ይሠራል።

ሌላው ማንኛውም ሰው እስከ ክልል ድረስ ማለት ነው፣ ችግሩ አለብኝ ብሎ ወደ ኬር ኤፒሊፕሲ ኢትዮጵያ ሲደውል ምን ማድረግ እንዳለበት፤ ወዴት መሄድ እንደሚያስፈልገው መረጃ እንዲያገኝ ይደረጋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ችግራቸውን ለይተው መድኃኒት እየወሰዱ ያሉ፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ መድኃኒቶች ከገበያው ላይ ሲጠፉ መድኃኒት ሊገኝ የሚችልበትን ቦታ በመጠቆም፤ ችግሩ ከዛም በላይ ከሆነ መድኃኒቱን በመስጠት የማገዝ ሥራን ይሠራል።

የሚጥል ሕመም በሰዎች ላይ ሲከሰት፣በተለይም ሲጥላቸው ለአጭር ደቂቃ የሆነ የአእዕምሯቸው ክፍል ሥራውን አቁሟል ማለት ነው። በዚህን ጊዜ ራስን ስቶ መውደቅ፣ መንቀጥቀጥ፤ አልያም የአፍ መጣመም፣ የሰውነት ቀጥ ብሎ መቅረትም ሊኖር ይችላል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በሽታው ራሱ ዓይነቱ ብዙ ስለሆነ ነው። እኛ በተለምዶ የምናውቀው ”ሰው ራሱን ስቶ ይወድቃል፤ ከዛ አረፋ ይደፍቃል” ነው፤ ግን መገለጫው ይህ ብቻ አይደለም። እነዚህ ሰዎች ከክስተቱ በኋላ ወደ ነበሩበት አዕምሯዊ ይዞታ የመመለስ ሁኔታ አላቸው። በመሆኑም ኅብረተሰቡም ይህንን በቅጡ ሊረዳ፤ ተገቢውን ትኩረትም ሊሰጥ ይገባል።

ሲስተር ሃይማኖት እንደሚሉት የሚጥል ሕመም በየትኛውም የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን ሊያጠቃ ይችላል። ነገር ግን፣ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ አብዛኛውን ጊዜ ሕመሙ በወጣቶች ላይ ይበዛል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ደም ግፊት፣ስትሮክ ገጥሟቸው በጭንቅላታቸው ውስጥ ደም ከፈሰሰ በዚህን ጊዜ የሚጥል ሕመም ሊከሰትባቸው ይችላል። ይህ የሚያመለክተን በተለያዩ አደጋዎች ምክንያትም የሚመጣበት አጋጣሚ መኖሩን ነው።

“አሁን ላይ በአገራችን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚያሳየን ከሆነ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ከማዳበር አኳያ ብዙ መሥራት ያለበት መሆኑን ነው። ኬር ኤፒሊፕሲ ከተቋቋመ ስምንተኛ ዓመቱን ይዟል። በዋናነትም ትኩረቱን ግንዛቤ ላይ አድርጎ እየሠራ ነው። ነገር ግን ትንሽ የግንዛቤው ሁኔታ እያደገ የመጣ ቢመስልም ለውጡ ግን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሻለ ግንዛቤ ላይ ደርሷል ለማለት ይከብዳል። ምክንያቱም አዲስ አበባ ውስጥ ተቀምጠው ይህ ሕመም እንዳለ ሰምተው የማያውቁ፣ችግሩ ሲመጣም ምን መደረግ እንዳለበት የማያውቁ ብዙ ሰዎች አሉ። በዚህ ምክንያትም የሚጥል ሕመም የተከሰተባቸውን ሰዎች ከቡዳ፣ከእርኩስ መንፈስ ወዘተ ጋር የማገናኘት ነገር እንጂ ወደ ሕክምን ተቋም ሄዶ ከማማከር አኳያ ገና ብዙ ይቀረናል” እንደ ሲስተር ሃይማኖት ገለጻ።

የኬር ኤፒሊፕሲ ኢትዮጵያ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ዐቢይ አሥራት በበኩላቸው ድርጅቱ ሲመሠረት ዋና ዓላማው የሚጥል ሕመም ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የተሻለ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ነው። በተጓዳኝም፣ በበሽታው ዙሪያ የኅብረተሰቡን አመለካከት ቀይሮ ሕሙማኑ እንደማንኛውም ሰው የሚኖሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት ሕመሙ ላለባቸው ሰዎች የሕክምና እርዳታን ይሰጥ የነበረው አማኑኤል ሆስፒታል ብቻ ነበር። ነገር ግን ድርጅቱ ከተከፈተ በኋላ የጤና ባለሙያዎች ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ፤ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና ግንዛቤ በመፍጠር ለሕመሙ ትኩረት ከመስጠትም በላይ በመድኃኒትና በሌሎች ነገሮችም በኩል የተሻለ ነገር እንዲመጣ ሰፊ ሥራ ሠርቷል።

ዛሬ ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ ሕሙማኑ ነጻ የሕክምና አገልግሎትን እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው። በዚህም ማዕከሉ ወርሐዊ ነጻ የሕክምና አገልግሎት በስፔሻሊስት ሐኪሞች በመስጠት ላይ ይገኛል። በአሁኑ ሰዓትም የዕድሉ ተጠቃሚ የሆኑ ከ8 መቶ በላይ ታማሚዎችም አሉ።

እነዚህ ታማሚዎች የተሻለ የሕክምና አገልግሎት ከማግኘታቸውም በላይ ድርጅቱ የጤና መድህን ስለሚገባላቸው አቅም የለንም ብለው ከሕክምና አገልግሎቱ እንዳይገለሉ ሆኗል። መድኃኒቱ ሲጠፉም ድርጅቱ አፈላልጎ በመስጠት እንዳይቋረጥባቸው እያደረገ ይገኛል።

አቶ ዐቢይ እንደሚሉት አብዛኞቹ ታማሚዎች እንደ ኤምአርአይ እና አይጂን የመሳሰሉ ምርመራዎች አይደረጉላቸውም። ምክንያቱ ደግሞ ሰዎቹ የአቅም ውስንነት ስላለባቸው፤ እንዲሁም መሣሪያው እንደልብ ስለማይገኝ ነው። አሁን ድርጅቱ ኤይጂ ማሽን በእርዳታ በማግኘቱ ታማሚዎችን በመሣሪያው ታግዘን የመመርመር፤ ከዛ ባለፈም ተጨማሪ ምርመራዎች ሲያስፈልጉ በከተማው ካሉ ዲያግኖስቲክ ማዕከላት ጋር በመነጋገር በነጻ አገልግሎቱን የሚያገኙበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥራን በመሥራት ላይ ይገኛል። ይህ ምናልባትም ለታማሚዎች ከፍ ያለ እገዛ ነው።

“የሚጥል በሽታ ሀገራችን ላይ በመንግሥትም ደረጃ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው ሁኔታ ትኩረት አግኝቷል ማለት ይከብዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ሕክምናው ከአዕምሮ ጤና ችግር ጋር የተያያዘ ተደርጎ ተወስዷል። ነገር ግን መሆን የለበትም። ይህ ደግሞ ሰዎች በዚህ ሕመም ተቸግረው ሲመጡ የሚላኩት አማኑኤል ሆስፒታል ስለሚሆን የሚፈጥርባቸው መደናገጥ ከፍ ያለ ነው። በመሆኑም ይህንን ሁኔታ ተረድቶ ማስተካከል ያስፈልጋል። እኛም ላለፉት ስምንት ዓመታት ሁኔታው ይሻሻል ዘንድ ብዙ ጥረት እያደረግን ነው” ይላሉ ምክትል ሥራ አስኪያጁ።

ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት የመንግሥትን ሸክም እየተጋራ ያለ ቢሆንም በአንዳንድ በጎ አድራጊዎች፣ እንዲሁም በመሥራቿ ወይዘሮ እናት የውነቱ ጥረት እዚህ ይድረስ እንጂ ብዙ ችግሮች አሉበት። በተለይም ታማሚዎች መጥተው ሲመረመሩ ብዙ የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ይኖራሉ። እነዛን ሁሉ ነገሮች ለማሟላት፣በዚህ በሽታ የተያዙ ሕጻናት ያላቸውን ወላጆች በማገዝ በኩል ከፍ ያለ የአቅም ውስንነት አለበት። በመሆኑም ይህንን ብቸኛ ድርጅት ማገዝ ዜጎችን ማገዝ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የሚጥል በሽታ በሕክምና ቁጥጥር ስር እስካልዋለ ድረስ ምን ጊዜና የት ቦታ ሕመምተኛውን እንደሚጥለው ማወቅ አይቻልም። በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። የእሳት፣ የመብራት ወይንም የቴሌቪዥን ማንፀባረቅና ማብለጭለጭ በሽታውን ሊቀሰቅሰው እንደሚችል አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በሽታው ድንገት የሚቀሰቀስና ታማሚውን እጅግ ለከፋ አደጋ የሚዳርግ በመሆኑ የሚጥል በሽታ ያለባቸው ሰዎች መኪና ከማሽከርከር፣ ሳይክል ከመንዳት፣ ከዋና፣ ፈረስና በቅሎ ከመጋለብ፣ ከፍታ ቦታዎች ላይ ከመሥራትና እንደ አልኮልና ጫት ካሉ ሱሶች በእጅጉ መቆጠብ እንዳለባቸው ባለሙያዎች ይመክራሉ።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የአስተሳሰባቸው እስረኞች

**ማሰላሰያ፤**

በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ያህል ሕጋዊ የማረሚያ ቤቶች እንዳሉና የታራሚዎች ቁጥርም ምን ያህል እንደሆነ የሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም በቂ መረጃ እንዳለው ተስፋ እናደርጋለን። ቀደም ሲል በነበረው ሥርዓት በሹክሹክታና አንዳንዴም ጮክ በሚሉ የሚዲያ ድምጾች ሲታሙ የነበሩትና "በባለ ጊዜዎች" ይተዳደሩ የነበሩት ድብቅ የማሰቃያ እስር ቤቶች ዛሬም ድረስ ይኑሩ አይኑሩ ለጊዜው የአደባባይ ምስክርነት ለመስጠት መረጃውም ሆነ ማስረጃው ስለሌለን ርዕሰ ጉዳዩን ጫን ብለን ለመዳፈር አንሞክርም። "ነበርን" ያስታወሰነው ሆድ ሆዳችንን እንደ ሻህላ እየበላ ፋታ የነሳን ወቅታዊ ችግር ተጋርጦን እንጂ የላይኛውን ጉዳይ የጠቀስነው ዋና ትኩረታችን ስለሆነ አይደለም።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የምንሰማቸውና የምና ደምጣቸው አንዳንድ የንጹሐን ዜጎች የእገታ ትራጀዲዎች ከአሁን ቀደም በስፋት ያልተለመዱ ክስተቶች ከመሆን አልፈው የዕለት አፍ ማሟሻ ወደ መሆን መሸጋገራቸው እንቅልፍና እረፍት እየነሱን መሆናቸውን መሸሸጉ ግን አግባብም ጥበብም አይመስለንም። በጠራራ ፀሐይ ግለሰቦች እየታፈኑ በመቶ ሺህዎች እና በሚሊዮኖች ብር ቤዛ (Ransom) መጠየቁ የዕለት ተዕለት መርዶ ከሆነብን ውሎ አድሯል።

ይህን መሰሉ አዲስ መጥ የሽብር ድርጊት የግለሰባዊ ፍርሃት ውጤት ብቻም ሳይሆን ሀገራዊ እፍረት ወደ መሆን ደረጃ እየተሸጋገረ መሆኑን ጫን ብለን የምንገልጸው ዋነኛው የስጋት ምክንያትና ለፈውስም ይረዳ ስለመሰለን ነው። በሰላም ሀገር ምን ያስፈራችኋል? ምንስ ያስደነግጣችኋል? ተብለን እንደማንገሰጽና እንደማንወቀስ ተስፋ እናደርጋለን። ብንወቀስም ሆነ ማስተባበያ ቢሰጠን እውነቱ ስለማይደበቅ ሕግ ማስከበሩ ላይ ማተኮሩ ይበልጥ ያዋጣ ይመስለናል።

ደግሞም እኮ አለባብሰን ብናርስ በአረም መመለሳችን ስለማይቀር ገና በጠዋቱ ለመፍትሔ መጮኹ እኛን ዜጎችን ለጥንቃቄ፤ መሪዎቻችን ጨክነው ፍርሃታችንን እንዲገፉልን ጠቃሚ ሊሆን ስለሚችልም ሹመኞቻችንን እንደማያስቆጣ ተስፋ እናደርጋለን። ስለሆነም ነው ጉዳዩን ሳናድበሰብስ ለመንግሥታችንና ለሕግ አስከባሪ ክፍሎች በግልጽ ቋንቋ "አቤት! አቤት!" እያልን የምንማጸነው።

ዝምታን መርጠን በጉምጉምታ ስሜታችንን በየጓዳችን ለመግለጽ መሞከራችን ባይቀርም በኅሊናችን፣ በብዕራችን፣ በትውልድና በፈጣሪም ዘንድ ጭምር እንደሚያስወቅስ ስለምናምን "ሳይቃጠል በቅጠል" እንዲሉ፤ የግፍ ድርጊቱ ፈጥኖ እንዲቆም መጠየቁ አግባብም የዜግነትና የሙያ ግዴታም ጭምር መሆኑ እንዲታወቅልን እንፈልጋለን።

ይህ ከማቆጥቆጥም አልፎ በየአካባቢው ሥር እየሰደደ በመሄድ ላይ ያለው የአሸባሪ አጋቾች ድርጊት በእንጭጩ ካልተቀጨና የፍትሑ በትር ጠንከር ካላለ በስተቀር መዘዙ ውሎ ሲያድር ተመዞ ላያልቅ እንደሚችል በመሰል ችግር የተጠቁ የብዙ ሀገራት ታሪክ ትምህርት ሊሆነን ይገባል።

የአጋች ታጋች ድራማው "የተዘወተረ ክስተት" በሆነባቸው በርካታ ሀገራት የዜጎች ሕይወት እንደምን ወደ ምድራዊ ገሃነምነት እንደተለወጠ እየሰማንም እያየንም ስለሆነ በዝርዝር መተንተኑ እጅግም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ሥጋታችንን የምንገልጠው ዛሬ ዳዴ እያለ በእንፉቅቅ የሚሄደው የአፈናና የእገታ ተግባር ነግ ተነግወዲያ የሀገሪቱ ዋና መከራ ሆኖ አሳራችንን እንዳያበዛ በመፍራትም ጭምር መሆኑ ይታወቅልን።

### "እስረኞቹ አጋቾች"፤

አንድ ሰው በአስተሳሰቡና በአመለካከቱ የራሱ እስረኛ መሆን ሲጀመር ሌሎችን በግፍና በእብሪት ድርጊቶች ለማሸማቀቅና በደመነፍስ እየተመራ የወንጀል ድርጊቶችን ለመፈጸም አቅም እንደሚያገኝ የሥነ አእምሮ ጠበብቱ በሚገባ ትንታኔ ሰጥተውበታል። አስተሳሰብ በክፉ ድርጊቶች ሲበከልና ሲበረዝ የውስጥ ዕይታ አድማስ ይጠባል። የዕይታ አድማስ መጥበብ ከጀመረ ደግሞ አሻግሮ ሩቅ ለማየትና አሰላስሎ ለመወሰን አቅም ስለማይኖር የግልፍተኝነት ጭካኔ የእልህ መወጣጫና መገለጫ መሣሪያ ይሆናል።

ንጹሐን ዜጎችን ለማገት በድፍረት የሚንቀሳቀሱት ጨካኝ ዜጎች መገለጫቸው አንድም ተስፋ መቁረጥ ነው። አንድም የሱስ ባሪያ መሆናቸው ነው። አንድም ራስ ተኮር ትርክትን እየፈጠሩና ማንነታቸውን አሳንሰው ስለሚመለከቱ ለበቀልና ለግፍ ፈጣኖች ስለሆኑ ነው። አንድም ከኋላ ለሚገፉቸው "ዱር አደር" ኃይል ተንበርካኪ በመሆን ወኔያቸው ስለሚሰለብ ነው። በአንድምታው ብዙ ጉዳዮችን መዳሰስ ቢቻልም ጠለቅ ብሎ ሁሉንም ምክንያቶች መዘርዘሩ ስለማይሞከር ለማሳያነት ይበቃሉ የተባሉት ምሳሌዎች ብዙ አቅጣጫዎችን ለማሳያት ፍንጭ እንደሚሰጡ ተስፋ እናደርጋለን።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በዘረፋና በእገታ ተግባር ላይ የተሰማሩት ዓላማ ቢስ ግለሰቦች ንጹሐን ዜጎችን በማገት "ይህን ያህል የማስለቀቂያ ገንዘብ (ቤዛ) ካልከፈላችሁ ታጋቾቹን እንገድላቸዋለን" የሚለው መደራደሪያቸው የድኩም አስተሳሰባቸው እስረኛ መሆናቸው ብቻም ሳይሆን የኅሊና ቀውስ ተጠቂዎች እንደሆኑም ጭምር ለመገመት አይከብድም።

በጠራራ ፀሐይ ግለሰቦችንና ቡድኖችን እያፈኑ መውሰዳቸው ብቻም ሳይሆን ስለ እኩይ ድርጊታቸው በሕጋዊ አካል በኩል ታድነው እርምጃ እንደሚወሰድባቸው መዘንጋታቸው የድኩምነታቸው አንዱ መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በዚህ ፈጣን የቴክኖሎጂ ዘመን እንቅስቃሴያቸውን በቀላሉ መቆጣጠር እንደሚቻልና ግንኙነታቸውንና የቤዛው ገንዘብ የሚገባበትን የባንክ ሂሳብ ቁጥር በግላጭ ሲሰጡ በቀላሉ ሊደረስባቸው እንደሚችል ያለመረዳታቸው በራሱ የአስተሳሰብ እስረኞቹ አመለካከት ምን ያህል እንደጠበበና የኮሰመነ እንደሆነ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል።

ይህን መሰሉ የእርምጃ አወሳሰድ በግልጽ እየታወቀ እስከ ዛሬ አጋቾቹ እንዳሻቸው ሲፈነጩ ለምን ዝም ተባሉ? ለሚለው ጥያቄ መልሳችን "ሚስትህ ወለደች?" ተብሎ የተጠየቀው አባወራ "ማንን ወንድ ብላ!" በማለት የመለሰው መልስ "ከልብ ካለቀሱ እምባ አይገድም" ከሚለው ቢሂል ጋር ተጣምሮ ቢታወስ ያግባባን ይመስለናል።

ማንኛውም ድርጊት ይዘገይ ካልሆነ በስተቀር ተሰውሮ ሊቀር አይችልም። ይህ እውነታ ያልገባቸው ወይንም ገብቷቸውም የልብ ልብ የተሰማቸው አንዳንድ የመንግሥት ሹመኞችና በዙሪያቸው የተኮለኮሉት ደላሎችና አቀባባዮች በአስተሳሰባቸው እስረኛ ሆነው በሕዝብ ላይ ግፍ ለመፈጸም የሚጨክኑት "ሆዳቸው አምላካቸው፤ ነውራቸው ክብራቸው" ስለሆነ ነው። ነገሮችን አዟሮ ለማየትና ቆም ብሎ ኅሊናቸውን ለማድመጥና ሰክኖ ለማሰላሰል የተሳናቸውም የወረደው ሰብዕናቸው ስለማይፈቅድላቸው እንጂ እውነቱ ጠፍቷቸው አይደለም።

በተውገረገረ የቅዠት አስተሳሰባቸው ራሳቸውን በራሳቸው አጥረውና ጠፍረው የሚኖሩ እንደነዚህ ዓይነት የጥፋት መልዕክተኞች ሌላው ሰው ለእነርሱ ሰብዓዊ ፍጡር እንዳልሆነ እስከ ማሰብ ድረስ የሚደርሱ ከንቱዎች ናቸው። ሕግም ከእነርሱ ጉልበት በታች እንደሆነ ስለሚያምኑ ቀኑ ቀን ወልዶ ፍትሕ በአራት ዓይናማ አትኩሮቱ ወደ ብርሃን አውጥቶ በአደባባይ እንደሚገልጣቸው ለማመን ልባቸውን ሞራ ስለደፈነው እውነት እንደሚያሸንፍ ለማመን ዝግጁ አይደሉም።

እውነትና ንጋት እያደር እየጠራ ሄዶ ፍርዳቸውን በሚቀበሉበት ዕለት የውርደታቸውን ዋንጫ እያንገሸገሻቸውም ቢሆን እንደሚጎነጩ ለማስተዋል የዘቀጠው አስተሳሰባቸው የኅሊናቸውን ብርሃን ስላሰወር እንደ ሰው ለማሰብ የሰውነት ብቃት የላቸውም። ማጠንጠኛችን፡- "ፍትሕ ወይ ወዴት አለህ!" የሚለው ብርቱ ጩኸት ፈጥኖ ምላሽ እንዲያገኝ የሚመለከታቸው ሁሉ ጨክነው የታዳጊነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ እነሆ አቤቱታችንን ይድረስ የምንለው የነገው ቀናችን ስለሚያስፈራን ነው።

> *አስተሳሰብ በክፉ ድርጊቶች ሲበከልና ሲበረዝ የውስጥ ዕይታ አድማስ ይጠባል። የዕይታ አድማስ መጥበብ ከጀመረ ደግሞ አሻግሮ ሩቅ ለማየትና አሰላስሎ ለመወሰን አቅም ስለማይኖር የግልፍተኝነት ጭካኔ የእልህ መወጣጫና መገለጫ መሣሪያ ይሆናል*

ብዕረ መንገዳችንን ሌላም ተቀጥላ ሃሳብ ጠቀስ አድርገን እንለፍ። በኢትዮጵያ ምድር እየታገቱ ያሉትና ቤዛ የሚጠየቅባቸው ግለሰቦች ብቻም አይደሉም። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) "የሕዝብም የመንግሥትም" ያለመሆኑን የገለጹት ውሱን የሀገሪቱ የመሬት ሀብትም በእብሪተኛና በሕሊና ቢስ የመንግሥት ሹመኞችና በአቀባባይ ደላሎች አማካይነት በጠራራ ፀሐይ ታግቶ አጥር እየታጠረ ሲከለልና ሲቸበቸብ በእህህታ እየተብሰለሰለን "የፍትሕ ያለህ!" እያልን ስንጮኽ መክረማችን የሚዘነጋ አይደለም። ይህን መሰሉ ችግር ሊቀረፍ ነው መባልን እንደሰማን የተሳልነውን ስዕለት እንደየእምነታችን ለፈጣሪ ለማድረስ አልዘገየንም።

ይህ ጸሐፊ በሚኖርበት ክፍለ ከተማ ውስጥ በአስተሳሰባቸው የታሰሩ፣ በሕሊናቸው የታወሩ ደላሎችና ሹመኞች የሚፈጹሙትን የመሬት ወረራ እገታ ግፍ ሲያስተውል የኖረው እንባ በተቀላቀለበት ትዝብት ጭምር ነው። ማስረጃ አቅርብ ከተባለ መኖሪያ ቤቱን ተጎራብቶ በተወረረው መሬት ላይ የተገነቡትን በመቶዎች የሚቆጠሩ ቤቶችን በማስረጃነት ማቅረብ ይችላል። በአጽማቸው ቆመው የቀሩትና በታጋች አጋች ሤራ በተጠላለፉ የሌብነት ድራማዎች መሠረታቸውና ኮለናቸው ተገትሮ የቀረው ጅምር ቤቶች "ድምጽ አውጥተው ስለሚጮኹ" ራሳቸው ለራሳቸው ተጨባጭ ምስክሮች ናቸው።

ሌላውና በእገታ ቱሻ ተተብትቦ የኖረው የአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ምሑራን እውቀትና ጥበብ ነው። ያለ መታደል ሆኖ ሀገራዊ ሃይማኖቶቻችንና የፖለቲካው ሥርወ መሠረቶች ለዘመናት ታጥረው የኖሩት በግለኝነትና በድብቅ ፍላጎቶች ማህደር ውስጥ ታሽገው መሆናቸው የትዝብታችንም የታሪካችንም አካል ናቸው። እነኚህን መሰል የሀገራችን አንጡራ የጥበብና የዕውቀት ሀብቶች ዛሬም ድረስ በእገታ ተጠርዘውና ለመቃብር ዝግጁ ተደርገው የመኖራቸው ምሥጢር ፍቺ ሊገኝላቸው አልቻለም።

ይህን መሰሉ ዕንቆቅልሻችን "ምን ዕንቁላል ድፍን፣ ያያችሁ እንደሆነ ዐይናችሁ ድፍን" እንዲል የልጅነታችን ጨዋታ፤ ከብርሃን ተሸሽገውና ታግተው ያሉ እውቀቶችና ጥበቦች በቅብብሎሽ ለትውልድ ቢተላለፉ፣ ተላልፈውም ሥራ ላይ ቢውሉ ኖሮ የዛሬው ድህነታችንና ኋላ ቀርነታችን ብሔራዊ መታወቂያችን ባልሆነ ነበር።

የቀረው የዓለም ማኅበረሰብ እውቀቱንና እምቅ የአዕምሮ ሀብቱን ለማጋራት በሚቻኮልበት በዚህ የፈጣን ቴክኖሎጂ ዘመን እዚሁ እኛ ሰፈር ያለንን መልካምነት በስስትና በንፉግነት ሸሽገን አፈር ለማልበስ የመቃብር ጉድጓድ ስንምስ ውለን ማደራችን እንደ ባህል ወስደን በማጽደቅ ስለተጎናጸፍነው ይሞቀን ካልሆነ በስተቀር አይቀዘቅዘንም።

ካሁን ቀደም በዚሁ ዐምድ ሥር በዓለማችን ላይ ከፍተኛ ተነባቢነት ያተረፈውን የእንግሊዛዊ ጸሐፊ የቶድ ሄኒሪን አንድ መጽሐፍ ጠቀስ ያደረግሁበትን አጋጣሚ አስታውሳለሁ። የመጻሐፉ ርዕስ "DIE EMPTY" የሚል ሲሆን ተቀራራቢና የተፍታታው ትርጉሙ "መክሊትህን ለበጎነት አንጠፍጥፈህ እለፍ" የሚል ሃሳብ ያዘለ ነው።

ደራሲው የሚሞግተው እያንዳንዱ ሰው ከታጠረበት እኔ ብቻ አስተሳሰብ ተላቆ ለሌሎች ጥቅም አስቦ ያለውን ሁሉ አሟጦ በማካፈል እንዲያልፍ ነው። "በአስተሳሰባችን በረት" ውስጥ አግተን ያከማቸናቸውና ያጎርናቸው መክሊቶቻችን (ሀብታችን፣ እውቀታችን፣ መልካም ምክሮቻችንና አስተሳሰባችን ወዘተ.) የዕድሜ ድካም ሳይጫጫነን በፊት በጉብዝናችን ወራት ነፃ ወጥተው ለሰው ልጆች ሁሉ በምልዓት ጥቅም እስካልሰጡ ድረስ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው" የሚል ነው። ዛሬ ጠፍረን ያሰርናቸው በጎ ስጦታዎቻችን በጊዜው አገልግሎት ላይ እስካልዋሉ ድረስ "ቀናችን ሲቆረጥ" ሞት በሚሉት አይምሬውና ጨካኙ ጀግና ተማርከን ያከማቸነው ሁሉ "ለብልና ለምስጥ ሲሳይ" መሆናቸው እንደማይቀር ደራሲው አስረግጦ አስምሮበታል።

በዚህ ዐምደኛ ግምታዊ ስሌት መሠረት የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ቢፈተሽ በሕጋዊ ከለላ ጥላ ሥር ተጠብቀው እየታረሙ ካሉት እስረኞች ይልቅ በአስተሳሰባቸው ታስረው የተተበተቡት የራስ በራስ እስረኞች ቁጥር ሳይበልጥ የሚቀር አይመስለንም። ስንቱን አግተንና በስንቱ ኃይል ታግተን ኑሯችን ኑሮ ሳይመስል እስከ መቼ እየቆዘምንና እያነባን እንኖራለን? አንዳች ሀገራዊ ተስፋ ብልጭ ብሎ በተወለደ ማግሥት ተከትሎ የሚመጣው "የእንግዴ ልጅ" አበዛዙ ምን ይሉት አዚም እንደሆነ አልገባንም፣ ሊገባንም አልቻለም፣ ወደፊትም ይገባን እንደሆን እርግጠኛ ለመሆን አዳግቶናል።


ኢትዮጵያ ሆይ! አዲሱ የእገታና የታጋቾች ድራማ መጋረጃ የሚዘጋው መቼና እንዴት ነው? ያልገባንን መጠየቅ፤ አንቺም እንዲገባን መመለስ "በሕገ መንግሥትሽ ወርቃማ የዲሞክራሲ ቅብ መጽሐፍ" ውስጥ በዝርዝር የቀረበልን "ሜኑ" ስለሆነ "በሕግሽ አምላክ!" ብለን የምንጮኸው መፍትሔ እንድትሰጭን ነው። ዘንግተሽው ከሆነም ስምሽ የተጠቀሰበትን የዋስትና አንቀጽ ከራስሽ ሕገ መንግሥት እንደሚከተለው እናስታውስሻለን።

"ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፣ የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለ ፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር፣ ወይንም ኢ-ሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይንም በይቅርታ አይታለፉም።" (አንቀጽ 28፡1) እኛ ልጆችስ ብሶታችንን ሳንገደብ ዘርዝረን አራግፈንብሻል፤ አንቺስ ምን መልስ ትሰጭናለሽ? በትዕግሥት እንጠብቃለን። ሰላም ይሁን።

# ተናጋሪው ዶሴ

# ደረሰኝ ሻጮቹ

አስመረት ብስራት



አቶ ተስፋሁነኝ ተሾመ በንግድ ሥራ ላይ ተሠማርተው መሥራት ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በሥራቸው ስኬታማ ቢሆኑም የተሻለ ገንዘብ ፍለጋ ሁልጊዜ ግራና ቀኝ መመልከት ብቻ ሳይሆን ድንጋይ እስከ መፈንቀል የደረሰ ሥራን ያከናውናሉ። ሀብት የማፍራት ፍላጎታቸው እየጨመረ ሲሄድ በሥራ ከመክበር ይልቅ ሕገወጥ መንገድን ምርጫቸው አደረጉ። በዚህም የተለያዩ ሸያጮችን በሕገ ወጥ መንገድ ማስጓዝን ተለማመዱ።

ሕገ ወጥነትን ምርጫቸው ያደረጉት እኚህ ነጋዴ ደረሰኝ ሳይቆርጡ በርካታ ሽያጮችን ሲያከናውኑ ከቆዩ በኋላ የቫት ተመላሽ ገንዘብ ለማግኘት በማሰብ ምንም አይነት ግብይት ሳይኖር በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሐሰተኛ ደረሰኝ ቆርጠው ይይዛሉ። ይህንን ተግባር ከማከናወን አልፈው ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በመገናኘት ከሕገ ወጥ ደረሰኝ ሻጮች ጋር ሥራውን በስፋት ማከናወን ይቀጥላሉ።

በደላሎቹ አማካኝነት ሕገወጥ ደረሰኝ የሚሸጥበት ቦታ የሄዱት አቶ ተስፋሁነኝ በሐሰተኛ መታወቂያ በአንድ ግለሰብ ስም ከወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ላይ በሚሊዮኖች ግብይት ስለማከናወናቸው የሚገልፅ ደረሰኝን በሕገወጥ መንገድ ገዝተው ሲወጡ እጅ ከፍንጅ ተያዙ።

### ሕገወጧ የሽያጭ ሠራተኛ

ወይዘሪት ገነት ኃይሉ የሽያጭ ሠራተኛ በመሆን የተለያዩ ተቋማት ላይ በሽያጭ ማሽን ሥትሰራ ቆይታለች። ይች በሥራዋ ታታሪ የሆነች ግለሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የምታገኛቸው ባለሃብቶች በሕገወጥ ደረሰኝ የተለያዩ ግብይቶችን ሲያከናውኑ በዚህም ተዝቆ የማያልቅ ገንዘብ ሲያካብቱ ትመለከታለች።

ሕገወጥነት ይዞ የሚመጣውን ጦስ ብታስብም ከእለት ወደ እለት ግን ሰዎቹ በዚህ ሥራቸው ምንም ሳይደርስባቸው ሲቀር፤ ቀስ በቀስ በሕገወጥ ሥራው ለመሠማራት ልቧ ይነሳሳል። በዚህም በሕገ ወጥ መንገድ የሽያጭ ማሽን እጇ እንዲገባ ታደርጋለች። በመቀጠል በሥራ አጋጣሚ ከተዋወቀቻቸው ነጋዴዎችና ደላሎች ጋር በመሆን በሕገ ወጥ ሥራው ውስጥ ጠልቃ ትሰምጣለች።

ቀናት ቀናትን እየጨመሩ ገቢዋም ከፍ እያለ ሲሄድ በሕግ እጠየቃለሁ የሚለው ስጋት ከውስጧ ሙልጭ ብሎ ጠፋ። በስጋቱና በይሉኝታ ቦታ ድፍረትንና ስግብግብነትን አንግሳ ሀሳቧን በሙሉ ገንዘብና ገንዘብ ላይ ብቻ አደረገችው። ሆኖም ግን ከዕለታት በአንዱ ቀን በልደታ ክፍለ ከተማ ባልቻ ሆስፒታል አካባቢ ከሚገኝ አሕመድ ሕንጻ ውስጥ በሐሰተኛ መታወቂያ ስም ከወጣ ሕጋዊ ማሽን ላይ ግብይት ሳይኖር 12 ሚሊዮን 135 ብር ሐሰተኛ ደረሰኝ በማዘጋጀት ቆርጣ ስትሰጥ እጅ ከፍንጅ ተያዘች።

### ደሳሳው

አብዲ ጃቢር ፈጣን ወጣት ነው። ያንንም ያንንም መሞከር የሚያስደስተው አይነት ቅብጥብጥ ወጣት ነው። ከልጅነቱ ጀምሮ በተገኘው ሥራ ላይ በመሠማራት ገንዘብ ከማግኘት የተሻለ ምንም ዓይነት ሕልም አልነበረውም። የሚመርጠው ሥራ ሁሉ አየር በአየር የሚባለው ዓይነት ምንም ሳይደክሙ ገንዘብ ማግኘት ዓይነት ነው። በተገኘው አጋጣሚ በሙሉ ገንዘብ የሚያገኝበትን ነገር ይሞክራል። ገንዘብ የሚያስገኝለት ከሆነ ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይልም።

የተለያዩ ሥራዎችን እየሞከረ ቢቆይም ያሰበውንና እሱ ስኬቱ የሚለው ደረጃ ሊደርስ ባለመቻሉ ሌሎች አማራጮችን መመልከት ጀመረ። ያኔ በአካባቢው የድለላ ሥራን የሚሠሩ ወጣቶች የተለያዩ የማሻሻጥ ሥራ ላይ ተሠማርተው ጠቀም ያለ ገንዘብ ሲያገኙ ይመለከታል። እሱም በዛው የሥራ ዘርፍ ተሰማርቶ ቤቱንም መኪናውንም ሲያሻሽጥ ይቆያል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በአጋጣሚ የሕገወጥ ደረሰኝ የሚሸጡና መግዛት የሚፈልጉ ሰዎችን የማገናኘት ሥራ እንዳለ ይሰማል።

ይህም በቀላል በማመቻቸት መንገድ ጠቀም ያለ ገንዘብ የሚገኝበትን የሥራ አማራጭ ዓይኑን ሳያሽ ገባበት። ባለሀብቶችንና ሐሰተኛ ደረሰኝ ሻጮችን በማገናኘት የሚያገኘው ገንዘብ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ አኗኗሩም እየተቀየረ ከእግረኝነት ወደ ባለመኪናነት ሲሸጋገር የሚሠራው ሥራ ሕገወጥ መሆኑን እስከመርሳት ደርሶ ነበር። በሀገርና በወገን ላይ ሸፍጥ የሚሠሩ፤ ከሀገር ላይ በመስረቅ ሀብትን ለማካበት የተመኙትን እያገናኘ እሱም ወደ ሀብት ማማ ተመነጠቀ።

ይህ ሁሉ በሕግ ሲደረስበት ሳያስበው የወጣበት ከፍታ መውረጃው እስኪቸግረው ግራ ተገባ። ሕግም የተመለከተውን ሕገወጥ ሥራ አይተውምና ግለሰቡ ለራሱ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሐሰተኛ ደረሰኝ እንዲቆረጥ ለሽያጭ ያመቻቸ እና ሐሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው የተጭበረበሩ ወይም ሕገወጥ የሆኑ ደረሰኞች ለሽያጭ ማመቻቸት ወንጀል ተጠያቂ ተደረገ።

### የፖሊስ ምርመራ

በዚህ ሕገወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩትን ግለሰቦች ለመያዝ ፖለስ ያደረገው እልህ አስጨራሽ ጥረት ዛሬ በድል ተጠናቋል። ነገሩ እንዲህ ነበር፤ አቶ ተስፋሁነኝ ተሾመ ሐምሌ 24 ቀን 2013 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ልዩ ቦታው ቄራ ዳውን ታወን አካባቢ ካለው ንግድ ቤት ውስጥ ዐቃቤ ሕግ ምስክር ግብይት ሳይኖር ደረሰኝ ብቻ እንደምትፈልግ ለደላላው የነገረችው እና በእርሱ አገናኝነት ደረሰኙ ከሚይዘው ገንዘብ የደላላ አንድ በመቶ እና የደረሰኝ ኮሚሽን ሦስት ከመቶ እንደምትከፍል ተስማምተው በደላላው አማካኝነት አቶ ተስፋሁነኝ ተሾመ ከሚገኝበት ንግድ ድርጅት ከገቡ በኋላ በሐሰተኛ መታወቂያ በአንድ ግለሰብ ስም ከወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ላይ ግብይት ሳይኖር 17 ሚሊዮን 940 ሺ ብር ሐሰተኛ ደረሰኝ በማዘጋጀት ቆርጦ ሲሰጣት እጅ ከፍንጅ ልታስይዛቸው ቻለች።

ግለሰቦቹም በፈፀሙት ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ማቅረብ ወንጀል የተከሰሱ ሲሆን እንዲሁም ሐሰተኛ ደረሰኞችን ለማዘጋጀትና ለማተም የሚያገለግሉ ማሽኖችን ይዞ በመገኘት በተደራራቢ ወንጀሎች እንዲጠየቁ መደረጉን ፖሊስ አስረድቷል።

በዛው ዕለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሯ በተጨማሪ ሌላ ደረሰኝ ከሌላ ማሽን እንደምትፈልግ ለአቶ ተስፋሁነኝ ተሾመ ስትነግረው ተከሳሹ ስልክ በመደወል ደረሰኝ የሚፈልግ ሰው አለ መጣን በማለት በመዝገቡ ላይ 2ኛ ተከሳሽ የሆነችው ገነት ኃይሉ ከምትገኝበት በልደታ ክፍለ ከተማ ባልቻ ሆስፒታል አካባቢ ከሚገኝ አሕመድ ሕንጻ ውስጥ በሐሰተኛ መታወቂያ ስም ከወጣ ሕጋዊ ማሽን ላይ ግብይት ሳይኖር 12 ሚሊዮን 135 ብር ሐሰተኛ ደረሰኝ በማዘጋጀት ቆርጣ ስትሰጣት እጅ ከፍንጅ የተያዘች በመሆኑ በተጨማሪም ተከሳሿ ምንም አይነት የሽያጭ መመዝገቢያ ለመጠቀም የሚያስችል ሕጋዊ ፍቃድ እና ሰነድ ሳይኖራት በሐሰተኛ መታወቂያ ስም የወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ይዛ የተገኘች በመሆኑ በፈፀመችው ሐሰተኛ ደረሰኞችን ለማዘጋጀትና ለማተም የሚያገለግሉ ማሽኖችን ይዞ በመገኘት ወንጀል፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ በማቅረብ፣ ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ መስጠት እና የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ማዘጋጀት፣ መሸጥና ማሰራጨት ወንጀል በተደራራቢ ክሶች ተጠይቃለች።

በሌላ በኩል አብዲ ጃቢር ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ለራሱ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሐሰተኛ ደረሰኝ እንዲቆረጥ ለሽያጭ ያመቻቸ እና ሐሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው የተጭበረበሩ ወይም ሕገወጥ ደረሰኞች ለሽያጭ ማመቻቸት ወንጀል በቀረበበት ተደራራቢ ክሶች እንዲጠየቅ መደረጉን ፖሊስ አመልክቷል።

ፖሊስ ማስረጃውን በማጠናቀር በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ከፖሊስ ጋር በመሆን ግብይት ሳይኖር ከ29 ሚሊዮን ብር በላይ ሐሰተኛ ደረሰኝ በማዘጋጀትና በመሸጥ ለግል ጥቅማቸው ባዋሉ ሦስት ግለሰቦች ላይ ምርመራ በማጣራ፤ ዐቃቤ ሕግ ክስ መሥርቷል።

### የፍርድ ቤት ክርክር

ክርክሩ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት የተደረገ ሲሆን፤ የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው 1ኛ ተከሳሽ ተስፋሁነኝ ተሾመ፣ 2ኛ ተከሳሽ ገነት ኃይሉ፣ 3ኛ ተከሳሽ አብዲ ጃቢር፣ የተባሉት ላይ ዐቃቤ ሕግ 10 የተለያዩ ክሶች አቅርቦ በመከራከር ረትቷል።

ተከሳሽ ተስፋሁነኝ ተሾመ ሐምሌ 24 ቀን 2013 ዓ.ም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ልዩ ቦታው ቄራ ዳውን ታወን አካባቢ ካለው ንግድ ቤት ውስጥ ለ1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ግብይት ሳይኖር ደረሰኝ ብቻ እንደምትፈልግ ለ3ኛ ተከሳሽ የነገረችው እና በእርሱ አገናኝነት ደረሰኙ ከሚይዘው ገንዘብ የደላላ አንድ በመቶ እና የደረሰኝ ኮሚሽን ሦስት ከመቶ እንደምትከፍል ተስማምተው በደላላው አማካኝነት 1ኛ ተከሳሽ ከሚገኝበት ንግድ ድርጅት ከገቡ በኋላ በሐሰተኛ መታወቂያ በአንድ ግለሰብ ስም ከወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ላይ ግብይት ሳይኖር 17 ሚሊዮን 940 ሺ ብር ሐሰተኛ ደረሰኝ በማዘጋጀት ቆርጦ ሲሰጣት እጅ ከፍንጅ የተያዘ በመሆኑ በፈፀመው ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ማቅረብ ወንጀል የተከሰሰ ሲሆን እንዲሁም ሐሰተኛ ደረሰኞችን ለማዘጋጀትና ለማተም የሚያገለግሉ ማሽኖችን ይዞ በመገኘት ወንጀል በሦስት ተደራራቢ ክሶች ክርክር ሲያደርግ ቆይቷል።

በዛው ዕለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሯ በተጨማሪ ሌላ ደረሰኝ ከሌላ ማሽን እንደምትፈልግ ለ1ኛ ተከሳሽ ስትነግረው ተከሳሹ ስልክ በመደወል ደረሰኝ የሚፈልግ ሰው አለ መጣን በማለት በመዝገቡ ላይ 2ኛ ተከሳሽ የሆነችው ገነት ኃይሉ ከምትገኝበት በልደታ ክፍለ ከተማ ባልቻ ሆስፒታል አካባቢ ከሚገኝ አሕመድ ሕንጻ ውስጥ በሐሰተኛ መታወቂያ ስም ከወጣ ሕጋዊ ማሽን ላይ ግብይት ሳይኖር 12 ሚሊዮን 135 ብር ሐሰተኛ ደረሰኝ በማዘጋጀት ቆርጣ ስትሰጣት እጅ ከፍንጅ የተያዘች በመሆኑ በተጨማሪም ተከሳሿ ምንም አይነት የሽያጭ መመዝገቢያ ለመጠቀም የሚያስችል ሕጋዊ ፍቃድ እና ሰነድ ሳይኖራት በሐሰተኛ መታወቂያ ስም የወጣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ፣ ይዛ የተገኘች በመሆኑ በፈፀመችው ሐሰተኛ ደረሰኞችን ለማዘጋጀትና ለማተም የሚያገለግሉ ማሽኖችን ይዞ በመገኘት ወንጀል፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ማቅረብ፣ ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ መስጠት እና የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ማዘጋጀት፣ መሸጥና ማሰራጨት ወንጀል በአራት ተደራራቢ ክሶች ክርክር ስታደርግ ቆይታለች።

በሌላ በኩል 3ኛ ተከሳሽ የሆነው አብዲ ጃቢር ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ለራሱ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሐሰተኛ ደረሰኝ እንዲቆረጥ ለሽያጭ ያመቻቸ እና ሐሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው የተጭበረበሩ ወይም ሕገወጥ ደረሰኞች ለሽያጭ ማመቻቸት ወንጀል በቀረበበት ተደራራቢ ክሶች ክርክር ሲያደርግ ቆይቷል።

### ውሳኔ

ዐቃቤ ሕግም ሦስቱ ተከሳሾች የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኝት በማሰብ ሕግን በመተላለፍ ፈጽመውታል ባላቸው 10 የተለያዩ ክሶች ማስረጃ በማቅረብ ክሱን በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ የዐቃቤ ሕግን እና የተከሳሾችን ክርክር የመራው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎትም 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በተከሰሱባቸው ክሶች በሙሉ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት የቅጣት ውሳኔ በማሳለፍ በአጠቃላይ በ1ኛ ተከሳሽ በ 14 ዓመት ጽኑ እስራት ፣ 2ኛ ተከሳሽ በ12 ዓመት ጽኑ እስራት ፣ እንዲሁም በ3ኛ ተከሳሽ እና የማገናኘት ሥራ የሠራው ተከሳሽም በተከሰሰባቸው 4 ክሶች መካከል በአንድ ክስ ብቻ የጥፋተኝነት ውሳኔ በማሳለፍ በ3 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን ከእስራት ቅጣቱ በተጨማሪ 1ኛ ተከሳሽ የ360 ሺ ብር፣ 2ኛ ተከሳሽ የ210 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ገበያ ወይስ ጣቢያ?

ይበል ከሳ

አሁን አሁን ከሚገርሙኝ ነገሮች መካከል ሀገራችን ውስጥ በየኤፍ.ኤም ሬዲዮንና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የሚተላለፉልን ፕሮግራሞችና ፕሮግራሞቹ የሚቀርቡባቸው መንገዶች ዋነኞቹ ናቸው። ሁል ጊዜ ስገረም አንድ ቀን ግን በቁም ነገር ቁጭ ብየ ማስታወሻ ይዤ ሁኔታውን በሥርዓት ለመታዘብ ወሰንኩ። ከዚያም ከብዙዎቹ አንደኛውን የኤፍ.ኤም ሬዲዮ ፕሮግራም መሰራጨ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ተከታተልኩት።

በዚህ መሰረት ለመከታተል የመረጥኩት ከቀኑ 10፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት የሚቀርብ፤ የአንድ ሰዓት የሚቆይ የሬድዮን ፕሮግራም ነበር። አቅራቢዎቹ እንደሚሉት "አድማጮች እየተዝናኑ የሚማሩበት" የመዝናኛና የቁምነገር የሬዲዮ ፕሮግራም ነው። ቀደም ሲል በሌላ ቀን ሲተዋወቅ በሰማሁት መሰረት ፕሮግራሙ የሚጀምረው ልክ ከቀኑ አስር ሰዓት በመሆኑ አስቀድሜ ተዘጋጅቼ ስከታተል አስር ሰዓት ሊጀምር አልቻለም። ከፕሮግራሙ መጀመር በፊት ለአራት ደቂቃ ያህል የጣቢያው ዋና ዋና ዜናዎች ቀረቡ። ዜናዎቹ ተደምጠው እንዳበቁ ፕሮግራሙ ይጀምራል ብዬ ብጠብቅም አልሆነም። ለቀጣዮቹ አራት ደቂቃዎች ያህል ሙዚቃ ነበር የተደመጠው። ከዚያ በኋላ 10፡08 ላይ ፕሮግራሙ ተጀመረ። እንግዲህ ከተያዘለት የሰዓት ምጣኔ ላይ ስምንት ደቂቃዎች ተቀነሰለት ማለት ነው። ከዚያም ከ10፡08 እስከ 10፡16 ለስምንት ደቂቃወች ያህል የፕሮግራሙ አቅራቢ ጋዜጠኞች ፕሮግራሙን አሁንም ፕሮግራሙን ያቀርባሉ ብየ ስጠብቅ የፕሮግራሙን አጋሮች መልዕክት አቀረቡ። ከ10፡16 እስከ 10፡21 ለአምስት ደቂቃ ያህል እንደገና የአጋሮች መልዕክት በድጋሜ ቀረበ። ቀጥለው ከ10፡21 እስከ 10፡25 ባሉት አራት ደቂቃዎች "የሚወዷቸውንና የሚያከብሯቸውን" አድማጮቻቸውን ሙዚቃ ጋበዟቸው።

ከዚያ ከ10፡26 እስከ 10፡36 ለአስር ደቂቃወች ያህል የፕሮግራሙ ይዘት ቀረበ። ከ10፡37 እስከ 10፡41 ለአራት ደቂቃ በሙዚቃ እረፍት ተደረገ። 10፡42 እስከ 10፡45 ለሦስት ደቂቃ ከአድማጮች የመጡ አስተያቶች እና አድናቆቶች ቀረቡ። እንደገና ከ10፡46 እስከ 10፡53 የፕሮግራም ይዘት ያለው ጉዳይ ይቀርባል ብዬ ስጠብቅ አሁንም በድጋሜ "የአድማጮችን አስተያቶችና አድናቆቶች" መሰረት ያደረጉ ከዋናው የፕሮግራሙ ይዘት የወጡ ወሬዎች ተሰሙ። 10፡54 እስከ 11፡00 ለሦስተኛ ጊዜ የአጋሮች መልዕክት ተሰማና ፕሮግራሙ አለቀ።

ከዚያ ሰዓቶችን ማስላት ጀመርኩ። ከአንድ ሰዓቱ ፕሮግራም ውስጥ ስምንት ደቂቃ ተቀንሶለት ስለተጀመረ አጠቃላይ የሚኖረውን ሰዓት ስናሰላው 42 ደቂቃ ይሆናል። ከ42ቱ ደቂቃ ውስጥ 21ዱ ደቂቃ ለማስታወቂያ ውሏል። ስምንት ደቂቃ ለሙዚቃ፣ 13 ደቂቃ ከፕሮግራሙ ይዘት ውጭ የሆነ ወሬ የተወራበት ሲሆን የዕለቱን ፕሮግራም ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ የዋለው አስር ደቂቃ ብቻ ነው። ይህን የአንድ ሬድዮ ጣቢያ ፕሮግራም ለማሳያነት አነሳሁ እንጂ አብዛኞቹ ማለት በሚቻልበት ደረጃ ተመሳሳይ ናቸው።

ይህም እውን የሬድዮ ጣቢያዎችና አብዛኞቹ ፕሮግራሞቻቸው "አዝናኝና አስተማሪ ፕሮግራም" ነው ለአድማጮች እያቀረቡ የሚገኙት? ማዝናናቱና ማስተማሩ ይቅርና እናቀርባለን የሚሉት ፕሮግራም በራሱ ቀርቧል ማለትስ ይቻላልን? በእንዲህ ዓይነቱ የአቀራረብ ሁኔታ ለሬዲዮ አድማጮችና ለቴሌቪዥን ተመልካቾች ከመገናኛ ብዙሃን እየቀረበ ያለው ፕሮግራም ወይስ ማስታወቂያ? ምናልባት በጋዜጠኝነት(Journalism) እና ማስታወቂያ (Advertisement) መካከል ልዩነት የለም ወይንም "ግብርና መር ኢኮኖሚ" እንደሚባለው "ማስታወቂያ መር ጋዜጠኝነት" አለ የሚል አዲስ ምሁር ካልተነሳ በቀር በጊዜ ሰሌዳው ውስጥ ያለው የሰዓት ምጣኔ በግልጽ እንደሚያሳየው አሁን ላይ በብዙወቹ የሃገራችን መገናኛ ብዙሃን እየቀረበ ያለው ፕሮግራም ሳይሆን ማስታወቂያ ነው። ይህ ደግሞ ከአገር አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ጋርም የተቃረነ ነው።

ይህ ሁኔታ መገናኛ ብዙሃኑ ከተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ማሰራጫ ከመሆን ይልቅ በብዛት የንግድ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎቶች ማሻሻጫ ሆነው ሲሰሩ መታየታቸው የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያወች ወይስ ሻጭና ገዥ የሚገናኙባቸው ገበያዎች ብለን እንድንጠይቅ ያስገድዳል። እናም በመገናኛ ብዙሃኖቻችን በሚቀርቡልን ዕለታዊና ሳምንታዊ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ከሕዝባዊ አጀንዳ መድረክነት ወይንም እንደ ስማቸው የብዙሃን መገናኛ ከመሆን ይልቅ የነጋዴዎች መገበያያ መድረክ እየሆኑ መምጣታቸው፤ "ለመሆኑ የጋዜጠኞችና የጋዜጠኝነት ዓላማ ምንድነው?" ብለን እንድንጠይቅ የሚያደርግም ነው።

ጋዜጠኝነት ክቡር ሞያ ነው ብለናል። ክቡርነቱም ክቡር ከሆነው ከሰው ልጅ ህይወት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑን አመላክተናል። ጋዜጠኝነት ክቡር ብቻ አይደለም ታላቅም ነው። መነሻውም መድረሻውም ታላቁ የሰውነት ተፈጥሮ ነውና! ዓላማው ሕዝብና የሕዝብ ጥቅምን ማስጠበቅ ነውና። ተልዕኮው ሰውን አስቀድሞ በሰዎች መካከል እኩልነት፣ ፍትህ፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲ እንዲኖር፤ የሃገርና ሕዝብ ዕድገትና ብልጽግና እንዲረጋገጥ መንገድ ማቃናት ነውና። ከዚህ የሚበልጥ ትልቅ ዓላማም የለም።

ሌላው አስገራሚ ጉዳይ ከማስታወቂያ ውጪ የሚቀርቡ ፕሮግራሞች ራሳቸው ከማስታወቂያ የተለዩ አለመሆናቸው ሲሆን ዜናና የህጻናት ፕሮግራሞች ጭምር በስፖንሰሮች የሚቀርቡበት ሁኔታ በህግ የተከለከለ መሆኑ የተዘነጋ ይመስላል።

ታዲያ አሁን ላይ በሀገራችን መገናኛ ብዙሃን የምናየው ከሕዝብ ይልቅ ጥቅምን መሰረት ያደረገ፣ ከብዙኃን አገልጋይነት ይልቅ የጥቂት ባለሀብቶችና ነጋዴዎች መገልገያ የሆነ፣ መረጃን ለሕዝብ ከመስጠትና ከማድረስ ይልቅ ዓላማው ለንግድ ማስታወቂያዎች ገበያን ማፈላለግ ዓይነት የሆነ ጋዜጠኝነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ? እንዲህ ዓይነቱ ሥራ በእርግጥ ጋዜጠኝነት ሊባል ይችላል ወይ? ዋናው ጥያቄ ነው።


በቴሌቪዥን ወይም በኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎቻችን ፕሮግራሞች ላይ ሲተላለፉ የምንሰማቸው ማስታወቂያዎች ብዙውን ጊዜ የሚያልቁት "ለየት ያደርገናል"፣ "ተሸላሚ ሆነናል"፣ "ተመራጭ ሆነናል"፣ "ደንበኞቻችን ኮርተውብናል" ...ወዘተ በሚሉ የምረጡኝ ቅስቀሳዎችና መፎከሮች ነው። ይህም የሚያመለክተው ድርጅቶቹ ደንበኛን በብቸኝነት ጠቅልሎ ለመያዝና ኢኮኖሚያዊ የበላይነትን ለማምጣት ከፍተኛ የእርስ በእርስ ፉክክር(ጦርነት ቢባል ይቀላል) ውስጥ መግባታቸውን ነው።

ይህንኑ የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ የተሻለው አማራጭ ደግሞ በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ደንበኛን ማብዛት ነውና ረብጣ ገንዘብ ከፍለው ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃሉ። ረብጣ ገንዘብ የተከፈለው የአንድ ፕሮግራም አዘጋጅም ከሌሎች ፕሮግራሞች በላይ ተወዳጅ እና ተከፋይ ለመሆን የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። በዚህ መካከል የሰው አለቃው ህሊናው መሆኑ ቀርቶ የሚያገኘው ብር ይሆናል። የሞራል ዋጋ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፣ ምን ይሉኝ ይጠፋል። አቅራቢው ድንገት ጋዜጠኝነቱን ረስቶ አስተዋዋቂ ሆኖ ቁጭ ይላል ማለት ነው።

ይህ አሳሳቢና አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ የብሮድካስት ባለስልጣንም ሬድዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ምን ያህል የማስታወቂያ አዋጁን በየፕሮግራሞቻቸው እየተገበሩ እንደሚገኙ በቅርብ በመከታተል አዋጁን ተላልፈው የተገኙት ላይ ሁሉንም ሊያስተምር የሚችል እርምጃ መውሰድ አለበት።

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያና አሜሪካ የእስረኛ ልውውጥ አደረጉ





ሩሲያ የአሜሪካ የሴት ቅርጫት ኳስ ኮከብ ብሪትኒ ግሪነርን "አስደናቂ" በተባለ የከፍተኛ የእስረኞች ልውውጥ መፍታቷን የአሜሪካ ባለስልጣናት አስታውቀዋል። ከሩሲያ ጋር በስምንት ወራት ውስጥ ለሁለተኛ የተደረገው ይህ ልውውጥ በውጭ አገር የታሰሩትን ታዋቂ አሜሪካውያንን ከእስር እንዲፈቱ አድርጓል።

ግሪነር የሁለት ጊዜ የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ስትሆን፤ በአደንዛዥ ዕፅ ክስ ለወራት በእስራት ቆይታለች። የግሪነርን መፈታት ለማረጋገጥ ፕሬዝዳንቱ ቦወት እንዲፈታ ያዘዙ ሲሆን፤ የቦወትን የ25 ዓመት እስራት እንዲቋረጥ ትእዛዝ ፈርመዋል። በዩክሬን ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ውጥረት በነገሰበት ወቅት ይህ ልውውጥ ለፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ከፍተኛ ግብ አሳክቷልም ተብሏል።

በአንድ ለአንድ እስረኛ ልውውጡ አለም አቀፍ የጦር መሳሪያ ነጋዴው ቪክቶር ቦወት ተለቋል። "የሞት ነጋዴ" የሚል ቅጽል ስም የተሰጠውን ሩሲያዊ ለመልቀቅ የተስማማው የባይደን አስተዳደር ግሪነርን ወደ ሀገሯ ለመመለስ ያጋጠማትን ከፍተኛ ጫና አጉልቶ አሳይቷል ሲል አሶሼትድ ፕረስ ዘግቧል።የሩስያ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ልውውጡን አረጋግጧል። የሩሲያ የዜና አገልግሎት በሰጠው መግለጫ ልውውጡ የተካሄደው በአቡ ዳቢ ሲሆን ቦውት ወደ ሀገር ቤት መመለሱን አረጋግጧል።

አንድ ለአንድ እስረኛ ልውውጡ በአለም አቀፍ የጦር መሳሪያ ነጋዴው ቪክቶር ቦወት እና የአሜሪካ የቅርጫት ኳስ ተጨዋች ብሪትኒ ግሪነርን ተደርጓል፡፡ይህ በሁለቱ አገራት የእስረኛ ልውውጥ የተደረገው የአረብ ኢምሬትስ እና ሳውዲ አረቢያ መሪዎች ሩሲያን እና አሜሪካንን በማደራደራቸው ነው።አሜሪካ እና ሩሲያ በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ እና ሳውዲ አረቢያ መሪዎች አደራዳሪነት የአንድ ለአንድ እስረኞችን ተለዋውጠዋል።

ሩሲያ ታዋቂዋ የቅርጫት ኳስ ተጫዋቿን ብሪትኒ ግሪነር በአደገኛ እጽ ዝውውር ወንጀል ተጠርጥራ ላለፉት ዓመታት በሞስኮ ባለ እስር ቤት ነበረች።አሜሪካም ሩሲያዊው ቪክቶር ቦትን በህገ ጦር መሳሪያ ንግድ እና ዝውውር ወንጀል ተጠርጥሮ በተመሳሳይ እስር ላይ እንደነበር ተገልጿል።

ኢምሬትስ ፕሬዝዳንት መሀመድ ቢን ዛይድ እና የሳውዲው አቻቸው መሀመድ ቢን ሰልማን በጋራ በመሆኑ አሜሪካ እና ሩሲያ የእስረኞች ልውውጥ እንዲያደርጉ ማደራደራቸውን የሁለቱ ሀገራት ውጭ ጉዳይ ሚንስቴር በጋራ ባወጡት መግለጫ አስታውቀዋል።

የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጆ ባይደንም የአረብ ኢምሬትስ እና ሳውዲ አረቢያ መሪዎች ላደረጉት ጥረት ምስጋናቸውን አቅርበዋል። አሜሪካንን በሁለት የኦሎምፒክ ውድድር ላይ በመወከል ለሀገሯ የወርቅ ሜዳሊያ ያመጣችው ግሪነር ከእስር መለቀቋ አሜሪካዊያንን አስደስቷል ተብሏል።

አሜሪካ በዓለም የጦር መሳሪያ ንግድ ዋነኛ ሸሪክ እንደሆነ በሚጠቀሰው ሩሲያዊው ቪክቶር ቦት ላይ የ25 ዓመት እስር ወስናበት ነበር።ሩሲያ ለብሔራዊ ጥቅሟ ስትል በጥብቅ የምትፈልገው ቪክቶር ቦት ከዋሽንግተን እስር ተለቆ በእጇ መግባቱን ማረጋገጧን የዘገበው አል ዐይን ነው፡፡

## የአንድ የቤልጂዬም መንደር ነዋሪዎች በሎተሪ 143 ሚሊዮን ዩሮ አሸነፉ

በቤልጂዬም አንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ 165 ሰዎች በጋራ የ143 ሚሊዮን ዩሮ ሎቶሪ አሸናፊ ሆኑ።ኦልምን በተባለ መንደር የሚኖሩት ሰዎች ሎቶሪውን የገዙት እኩል ገንዘብ አዋጥተው ነበር። ከሎቶሪው እያንዳንዳቸው 868 ሺህ ዩሮ ይካፈላሉ።የቤልጂዬም ብሔራዊ ሎቶሪ እንዳለው፣ በሎቶሪው ከ27 ሚሊዮን በላይ እጣዎች ያሉት እንደነበር ተገልጿል።




ሰባት ትክክለኛ ቁጥሮችን በማስገመት ለአሸናፊዎች ከፍተኛ ገንዘብ የሚሰጠው ዩሮሚሊዮንስ፣ በዘጠኝ የአውሮፓ አገራት መካከል የሚካሄድ የሎቶሪ እጣ ሲሆን አሸናፊዎች እስከ 142 ሚሊዮን 897 ሺህ 164 ዩሮ ድረስ ይሸለማሉ። የብሔራዊ ሎቶሪ ቃል አቀባይ ጆክ ቨርሞር እንዳለችው፣ ቤልጂዬም ውስጥ በቡድን ተወዳድረው አሸናፊ የሆኑ ሰዎች ማግኘት የተለመደ አይደለም። ከዚህ ቀደም እንዲህ ብዙ ሰዎች በጋራ ተወዳድረው አሸንፈውም አያውቁም።

165ቱ የአንድ መንደር ነዋሪዎች ሎቶሪው እንደደረሳቸው ሲሰሙ እጅግ እንደተደሰቱ የገለጸችው ቃል አቀባዩዋ "ምርጥ የገና ስጦታ ነው ያገኙት" ብላለች።እጣውም ቤልጂዬም ውስጥ የሚያዘጋቸው ወኪል ተቋም ኃላፊ፣ ለዓመታት ሰዎች በጋራ እጣ እንዲያወጡ ሲያበረታታ ቆይቷል።የአንድ መንደር ሰዎች በጋራ ማሸነፋቸውን ለማመን ስለከበዳቸው ዜናውን ስድስት ጊዜ ደጋግመው እንደሰሙትም ተናግሯል።

ያሸነፉት ሰዎች ማንነት እስካሁን ይፋ አልተደረገም። ከዚህ ቀደም አንድ የዩናይትድ ኪንግደም ዜጋ 195 ሚሊዮን ፓውንድ አሸንፎ ነበር። ይህም አንድ ሰው የደረሰው ትልቁ ገንዘብ ነው። ከወራት በፊት ደግሞ 184 ሚሊዮን ፓውንድ አሸንፈዋል።ዩሮሚሊዮንስ የሚዘጋጀው በቤልጂዬም፣ ፈረንሳይ፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ስፔን፣ ፖርቹጋል፣ አየርላንድ፣ ኦስትሪያ፣ ስዊዘርላንድ እና ሉግዘምበርግ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

## መጋቢ አዕምሮ

# ስጦታን በመስጠት

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

በምናባችን የልደት ፕሮግራም ለመሳተፍ በጉጉት እየጠበቁ ያሉ ልጆችን እንመልከት። በጊቢው ውስጥ ያሉት ልጆች ሁሉ ሰዓቱ እርቋቸው እየተቁነጠነጡ ነው። ልደትን ማክበር ልዩ ስሜት ይፈጥርላቸዋል። የራስ ልደት ሲሆን ደግሞ የበለጠ።

ልጆች ልደታቸውን በጉጉት እንዲጠብቁ ከሚያደርጋቸው ነገሮች መካከል አንዱ ስጦታ ነው። የሚሰጣቸው ስጦታን ታሳቢ አድርገውም ይጠብቃሉ።

የልደቱ ሰዓት ተጀመረ። እናት ፕሮግራሙን በጸሎት አስጀመሩ። ልደቱ ስለሚከበርለት ልጅ አምላካቸውን እያመሰገኑም ጸለዩ፤ በመቀጠልም መዝሙር ተዘመረ። በማስከተል ልደቱን ሊያከብሩ የተሰበሰቡ ልጆች ስለ ጓደኛቻቸው የሚሰጡትን አስተያየት መስጠት ጀመሩ። ሁሉም አስተያየታቸውን ሰጡ። ከአስተያየቶቹ መካከል የልጁ ታናሽ እህት አስተያየት ትኩረትን የሚስብ ነበር፤ “ወንድሜ በጣም እወድሃለሁ፤ አንተ ለእኔ ስጦታዬ ነህ፤ እና መልካም ልደት።” ብላ ንግግሯን ዘጋች። ባለልደቱ በእህቱ አስተያየት ልቡ ተነካ።

ባለልደቱ ታዳጊ እንደወትሮው “ማን ምን ስጦታ ይሰጠኛል?” ብሎ እየጠበቀ ነው። እንደተለመደው አባቱ፣ እናቱ፣ ወንድሞቹ፣ እህቱ፣ አጎቶቹ ወዘተ ይህን ለልደተህ እያሉ የሚያበረክቱትን እየጠበቀ ነበር። ከታናሽ እህቱ የመጣው አስተያየት ስለ ስጦታ የሚያስበውን አስተሳሰብ እንዲጠይቅ ያደረገው ሆነ። እርሱ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው፤ እርሱ ስጦታ ሆኖ በመስጠቱ ውስጥ ስላለው ትልቅ ነገር እንዲያስብ አደረገው።

ኬክ ተቆርሶ የልደት ፕሮግራሙ እየተደረገ እያለ ዘወትር በስራ የሚባክነው አባት ከቤት ደረሰ። አባትም ለልጁ የገዛለትን እቃ ይዞ ቀረበ። ልጁም አባቱን “አባዬ ተቀይሜሃለሁ እኔ ከስጦታው በላይ የምፈልገው አንተን ነው፤ አንተ ለእኔ ቦታ ካለህ ቢያንስ በልደቴ ቀን ቀልብህን ሰብስበህ መገኘት አለብህ። እኔ ለአንተ ዋጋ እንዳለኝ የምለካው በምትገዛለኝ ቁሳቁስ ውድነት አይደለም፤ አንተ ለእኔ በምትሰጠው ጊዜ እንጂ” ሲል ተናገረ። አባት ከልጁ ባገኘው ባልጠበቀው መልስ ደነገጠ። ልጁ ነገሮችን በጥራት ማሰብ የሚችልበት እድሜ ላይ እንደሆነም ተረዳ።

የልደት ፕሮግራሙ አልቆ ሁሉም ወደቤቱ ሲመለስ ልደቱ የተከበረለት ታዳጊ ግን በአይኑ ላይ እምባ ሞላ፤ እህቱ አንተ ለእኔ ስጦታዬ ነህ ያለችው ቃል በውስጡ ጎልቶ አሁንም ይሰማዋል።

ሰዎች መፈለግን፤ መወደድን፤ በሰዎች ውስጥ ቦታ ያለን መሆኑን እንድንረዳ እንፈልጋለን። በእለቱ ታዳጊው ክፍል ከሞሉት ስጦታዎች መካከል ጎልቶ በውስጡ ያለው የታናሽ እህቱ ንግግር ሆነ።

ዛሬ በስጦታ ገበያው ሰፊ የሆነ የቁሳቁስ ልውውጥ ይደረጋል፤ አንዱ ገዢ ሌላው ሻጭ ሆነው ተሰልፈዋል። ቁሳቁስ ከአንዱ ወደሌላው ይቀያየራል። ቁሳቁስን ተከትሎ የሚመጣው ቅጽበታዊ ተስፋም እንዲሁ ቦግ እልም እያለ ይቀጥላል። የሰው ልጅ ግን ቦታን የሚሰጠውን ሰው በልዩ ሁኔታ እየናፈቀ ይገኛል፤ ስጦታን በመስጠት ውስጥ ፈልጎ።

በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በሕይወታችን ውስጥ ልዩ ቦታ ስላላቸው ሰዎች እያሰብን እንዘልቃለን። የምናነሳው ቁልፍ ነጥቦችም ስጦታን፤ መሰጠትን እና መስጠትን የሚያነሱ ሆነው ይገኛሉ።

ስጦታ መስጠትም ሆነ መቀበል ከፍቅር ይመነጫል። ሰው ሊሰጠው የሚችለው የመጨረሻ ነገር ህይወቱን ነው። ከህይወት መለስ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ ወዘተ ስጦታ ሆኖ ይቀርባል። ሰጪውም ሆነ ተቀባዩ ለራሱ ግለሰብ ነው። ለራሱ ፍቅርን መስጠት በመጀመር ውስጥ በመሰጠት ውስጥ ያለው መስጠት ትርጉም አለውና ስለ ፍቅር እናንሳ።

### ስመሰጠት መነሻ የሆነው የፍቅር ህይወት

ከፍቅር ውጭ የሆነች ዓለም ምን እንደምትመስል ለማሰብ እንሞክር። እናት ለልጇ የምትሆነው ከውስጥ የሆነ ፍቅር የሌለባት ዓለም። መስጠትን እንጂ መቀበልን ስሌቱ የማያደርገው እውነተኛ ጾታዊ ፍቅር የሌለባት ዓለም። ሕዝብን ለማገልገል ብሎ በፖለቲካ መድረክ ላይ የሚገኝ የህዝብ ወዳጅ ሰው የሌለባት ሀገር። የእድሜ ልክ ጉርብትና ሆኖ የሚቀርብ ወዳጅነት የሌለባት ማህበራዊ ህይወት። መቀበልን ሳያስቡ መስጠት ስሌትን ያላደረጉ ሰዎችን የማታውቅ ፕላኔት።

ፍቅር የምድር ትልቁ ሃይል ነው። ራስን ከመውደድ ተነስቶ በመሰጠት ውስጥ ወደ ሌሎች መድረስ የሚቻልበት።

በተሳሳተ መንገድ ትርጉም ከሚሰጣቸው ነገሮች መካከል አንዱ ራስን መውደድ ይገኝበታል። ራስን በመውደድ ውስጥ የሚኮነን ሰው ራስ ወዳድ ይባላል። ራስ ወዳድነትን በማነወር ስንገልጽ በሰፊው ይስተዋላል። ለራስ የተጋነነ ቦታ መስጠት ላይ ስላለው ችግር ስምምነት ላይ ለመድረስ አንቸገር ይሆናል። ራስን መውደድ ግን በሚዛኑ ቦታው ሊፈለግለት ይገባልና አስቀደምነው።

“ባልንጀራን እንደራስ መውደድ” አምላካዊ ትእዛዝ ውስጥ በውስጠተዋቂነት ራስን መውደድ የእያንዳንዱ ሰው ተፈጥሯዊ መገለጫ መሆኑን አምኖ የተቀበለ ነው። በሕይወት ውስጥ ትርጉም ያለው አስተዋጾ ለማድረግ ራስን መውደድ ግድ ነውና። ለሌሎች ለመስጠት ስንነሳ ለራሳችን መስጠትን ማስቀደም ይኖርብናል።

ራስህን ትወዳለህ? ራስሽን ትወጃለሽ? እንግዲያውስ ውስጣችንን እናዳምጥ። በውስጣችን የሚፈጠረውን የትኛውንም ተፈጥሯዊ ስሜት እንግራ። መቀበልን ስሌት ሳናደርግ የመስጠት ህይወታችንን እንመርምር። በፍቅር ስሜት ላይ ስሌትን ጨምረን ፍቅር አልባ ህይወትን ከመኖር ራሳችንን እንጠብቅ። ፍቅር ተፈጥሮ፤ ተኮትኩቶ፤ ፍሬ እንዲያፈራ ሲደረግ የተፈጠረበትን ዓላማ የሚያሳካ ይሆናልና። ለራስ ብቻ ከመኖር ወደ ሌሎች መዘርጋትን ያስከትላልና።

ራስን ተቀብሎ በመሰጠት ውስጥ መኖር ተግባራዊ ህይወትን መኖርን ይጠይቃል። ለራሱ ቦታ የሚሰጥ ሰው ተግባራዊ ኑሮ በመኖር ውስጥ ለሌሎች መድረስ የሚችል ነው። አባት በልጁ የልደት ፕሮግራም ላይ አለመገኘቱ ለታዳጊው የፈጠረው ስሜት የምናብ ታሪካችን ይነግረናል። በመስጠት ውስጥ መሰጠትን የሚፈልገው ታዳጊ ተግባራዊነትን የፍቅር መገለጫ አድርጎ ለአባቱ ነገረ።

### ተግባራዊነት የመሰጠት እውነተኛ ማሳያ

አንድ የቆየ አባባል አለ እንዲህ የሚል “ፍላጎቱ ካለህ ትችላለህ” የሚል። በፍቅር ተነሳስተው ለውጤት የሚሰሩ ሌላ ሰው መጥቶ እስኪቀሰቅሳቸው ድረስ የሚጠብቁ አይደሉም። እራሳቸውን ከምኞት ቀጠና ገፍተው ከፍቅር ወደ ሆነ ተግባር ስራ የሚያስገቡ ናቸው። ይህንንም መደበኛ ስራቸው ያደርጋሉ። በእዚህም ምክንያት ነው የ20ኛው ክፍለዘመን ምርጥ አነሳሽ መሪዎች መካከል ፕሬዝዳንት ሩዝቬልት የሚጠቀሱት። እኒህ ፕሬዝዳንት እንዲህ አሉ “እንድሰራው የማምንበትነት ነገር ከመስራት ውጪ በእኔ ውስጥ ትልቅ ቦታ የምሰጠው አስደማሚ ነገር የለም። እንድሰራ ያመንኩበትን ነገር ለመስራት የተግባር እርምጃን የምወስድ ነኝ።”

እድሎች ወዳለህበት በር ድረስ መጥተው ላያንኳኩ ይችላሉ። አንተ ወደ እድሎችህ ልትሄድና ልታንኳኩ ይገባል። ያለህን ሃብት፣ ችሎታ እና ልዩ-ልዩ ሃብቶችን ቁጠር፤ ይህን ማድረግህ ያለህን እምቅ-አቅም ሊያሳይህ ይችላል። ከእዚያን በየእለቱ ያሉትን እድሎችን መመልከት ጀምር። የሆነ ነገር እንደሚያስፈልግህ የሚሰማህ ምን ላይ ነው? አንተ ያለህን ችሎታ/ክህሎት የሚያስፈልገው ሰውስ ማን ነው? የትኞቹ ያልተደረሱ የህብረተሰብ ክፍሎች አንተ ያለህን ነገር ባለማግኘታቸው በተግባር እየሞቱ ነው? እድሎች ሁሉም ቦታ አሉ፤ ከፍቅር የሆነ ተግባራዊነት ከእያንዳንዱ ሰው ይጠበቃል።

በመሰጠት ህይወት ውስጥ መስጠትን በተግባራዊነት ለማሳየት አንዳንዴ የመጋፈጥ ጫፍ ላይ እንድንገኝ ሊያደርገን ይችላል።

### መጋፈጥ የመሰጠት ጫፍ፣

እናት ስለ ልጆቿ ስትል የማትጋፋጠው ምንድን ነው? መሪው ምን እንደሚፈልግ ከተረዳና ወደ ተግባር ለመቀየር ግፊት ካደረገ አንድ ሊያልፈው የተገባ መሰናክል አለ። ይህም መሰናክል ስጋቶችን ለመጋፈጥ መፍቀድ ነው። ተነሳሽ ሰዎች ሁልጊዜ ስጋቶችን የሚጋፈጡ ናቸው። ስጋቶችን የሚጋፈጡበት ምክንያቱ ተነሳሽ የሆኑለት ነገር ባይከናወን የሚያጎድለውን ነገር ስለሚያውቁ ነው። ፕሬዝዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ እንዲህ አሉ “የተግባር ስራን በመስራት ፕሮግራም ውስጥ ስጋትም ሆነ ዋጋ መክፈል አለ፤ ነገርግን ከእዚህ የበዛው ዋጋ መክፈል ያለውን ስራ ለመስራት ባለመነሳት ውስጥ ነው።”

ተጋፋጭነት መሰጠታችን የእውነት እንዲሆን ያደርጋል። በመሰጠት ውስጥ የመስጠት ህይወትን ለመለማመድ ተጋፋጭነትን ባህሪያችን ማድረግ ያስፈልጋል። በምንኖርበት ምድር ውስጥ ምንም ነገር አልጋበአልጋ አይመጡም፤ መጋፈጥን የሚጠይቁ አያሌ ጉዳዮች አሉና።

ብዙ ጊዜ መጋፈጥን በመሸሽ ለሰዎች መስጠት የምንችለው አያሌ ነገር እያለ አልችልም ባይነትን መለያችን እናደርጋለን።

### የአልችልም ጠላት መሆን

በተጨባጭ እንደምናየው እችላለሁ ብሎ መነሳት ለብዙ ሰው ይቸግረዋል፤ ምክንያቱም እችላለሁ በማለት ብቻ የሚሆን ነገር ስለሌለ። የአልችልም ጠላት ለመሆን ራስ ላይ መስራት ይገባል፤ ከራስ በላይ መመንዘር የሚቻለው በመቻል መንፈስ ውስጥ በመሆን ስለሆነ።

ሁላችንም አዲስ አመት በመጣ ቁጥር በአመቱ ውስጥ ምን ማሳካት እንዳሰብን የመዘርዘር ልማድ ይኖረን ይሆናል። ማሳካት የፈለግነውን ማሳካትን ስናስብ አስቸጋሪ የሚሆኑብንን ነጥቦችም እንዲሁ ልንለያቸው እንሞክራለን። ለለውጥ መነሳትን ስንመርጥ አትችልም የሚለን በአካባቢያችን የሚሰማ ድምጽ እግራችን ላይ የታሰረ ገመድ ሆኖ ልናገኘው እንችላለን።

አትችልም፤ አትችይም የሚለው ድምጽ በበረከተበት ከባቢ ውስጥ እየኖርን በእችላለሁ መንፈስ ለለውጥ የሚነሱት ማግኘት አንችልም፤ መሰጠትም ሆነ መስጠት የለውጥ መንፈስ ውጤት ነውና።

አለመቻልህን በውስጥህ ከምታመላለስ መቻልህን ለራስህ ንገረው። የጊዜ ቀለበት ውብ ሆኖ የሚታየው በመቻል መንፈስ፤ ለመቻል ተግባራዊ እርምጃን በመራመድ ነውና። በዙሪያህ ያለው ሳርቅጠሉ ስለመቻል የሚናገረው ድምጽ ጎርናናነቱ በዝቶ ጆሮህን እስክትይዝ የሚያደርስ ቢሆንም አሁንም መቻልን አስብ። በመቻል መንፈስ ውስጥ ስለ መሰጠት መጋፈጥ ትችላለህ።

የምንኖርበት የድህነት ጥግ ይታወቃል። አልጠራ ያለው የፖለቲካ መንገዳችን የፈጠረው ውጥንቅጡ እንዳለ ነው። የትምህርት ጥራቱ አሽቆልቁሎ ባለዲግሪውና ዲግሪው የሌለው መካከል በእውቀት ላይ ልዩነት የሌለው ሆኖም ይታያል። ሁሉም ነገር አለመቻላችንን እየነገረን ባለንበት ዘመን ውስጥ ስለ መቻል ማንሳት እብደትም ሊመስል ይችላል። በመሰጠት ህይወት የለውጥ መንገዱ ውስጥ ግን የመቻል መንፈስ ግን የሚይዘው ቦታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። የመቻል መንፈስ ለሁላችን እንዲሆንልን በመስጠት ውስጥ የምንሰጠው ትርጉም ውስጥ ቦታ ይኑረው። በአንድ ወር ውስጥ ይህን ማድረግ እችላለሁ፤ በአመት ውስጥ፤ በሦስት አመት ውስጥ ብሎ ግብን ለማስቀመጥ የመቻል መንፈስ እጅጉኑ ያስፈልገናል።

በመቻል መንፈስ ውስጥ ተጋፋጭነት ይኖራል፤ ተጋፋጭነት ከምክንያት በላይ የሆነ መሰጠት በውስጣችን ይነግሳል፤ መሰጠታችን መስጠትን ከሕይወታችን እንዲገኝ ያደርጋል። የመስጠት ህይወት አንዳችን ለሌላችን ስጦታ እንደሆንን በማሰብ ውስጥ።

### የሴሉቱ ጩኸት

ለረጅም ጊዜያት በወለጋ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች የሚሆነው ነገር እንደ ሀገር ሁላችንንም አንገት ያስደፋ ነው። ከሞት ጋር የሰው ልጅ እንደ ቀላል እንዲገናኝ ያደረገ ስብራት። ያልተደመጡ ድምጾች በሞት ሜዳ ውስጥ። አንዳችን ለሌላችን ያለን መሰጠትን ደረጃው ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ።

በጭንቅ ላለችው ነፍስ የሚያደምጥ ቢገኝ ምንኛ እፎይታን ታገኝ ነበር። በሞት ጥላ ውስጥ ለሚያልፉ የሚታደግ አካል ኮቴ ትርጉሙ ምን ያህል ይሆን። ጆን ማእክስዌል የተባለው ጸሐፊ አንድ ጥያቄ ይጠይቃሉ



እንዲህ በማለት፤ “ከአሜሪካ ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች መካከል ዝርዝር ብትባል የማንን ስም ትጠቅሳለህ? ፕሬዝዳንቶቹን ትጠቅስ ይሆን? ወይንስ ማይክል ጆርዳንን? ወይንስ ቢል ጌትስን? እኔ ግን በዝርዝርህ ውስጥ ኦፕራ ዊንሬን እንድትጨምር እጠይቅሃለሁ።” ይላሉ። ስለ ኦፕራ ሲጽፉም “ኦፕራ በ1985 እ.አ.አ ኦፕራን በተግባር የማትታወቅ ተራ ዜጋ ነበረች። በቺካጎ አካባቢ ስርጭት ባለው የጠዋት ሾውን በመምራት ለአንድ አመት ወደ መድረክ ስትወጣ ትኩረት መሳብ ጀመረች። የእርሷ ስኬት ጆርባ ያለው ጉዳይ የመናገር አቅሟ ጥሩ መሆኑ እንደሆነ በብዙ ሊታሰብ ይችላል፤ በእርግጥ ትክክል ነው። በልጅነት ወቅት ማለትም የሁለት አመት ልጅ እያለች በቤተክርስቲያን መድረክ ላይ ንግግር አድርጋ ምእመናኑ ጥሩ ተናጋሪ ነሽ ብለዋት እንደነበር ታስታውሳለች። ነገርግን ከመናገር በላይም የማዳመጥ አቅሟም ትልቅ ነው። ከዘውትር ልምዷ መካከል ዋናው ለመማር ያላት ፍላጎት ነው። የጸሃፊያንን ጥበብ በንባብ ውስጥ እንደሚገኝ በማዳመጥ ውስጥ በሰዎች ውስጥ ያለውን ጥበብ ለማግኘት ትወዳለች። ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡና እንደሚሰማቸው ለማወቅ ልብወለድ መጻህፍትን፣ የግለታሪኮችን ወዘተ ለማወቅ ትጥራለች። የአድማጭነት አቅሟ የስራዎን መስመር አሳድጎታል። በተግባርም በቴሌቪዥን መስኮት የምታቀርበውን ፕሮግራም ተወዳጅነት ጨምሮታል። ጉዳዮቹን ለአየር ለማብቃት በተከታታይነት ነገሮችን መመልከት እና ማድመጥ ትወዳለች። ወደ ፕሮግራሙ የምታቀርባቸውን ባለሙያዎች፣ ጸሃፊዎች፣ አርቲስቶች በትኩረትና ከውስጥ በሆነ መስማት ታደምጣቸዋለች። ኦፕራ ባላት የአድማጭነት አቅም ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች ተርታ እንድትሰለፍ ሆናለች። እርሷ የአለማችን ከፍተኛው የመዝናኛ ዘርፍ ተከፋይ ባለሙያዎች ተርታ ትመደባለች፤ ግማሽ ቢሊዮን ዶላር የሚገመትም ሃብት አላት። በአሜሪካ ብቻ የሳምንቱ ሰላሳ ሦስት ሚሊዮን ህዝብ የእርሷን የቴለቪዥን ፕሮግራም ይከታተላል።” በማለት የኦፕራን የማድመጥ አቅም ይናገራሉ።

ኦፕራ ያደመጠቻቸው በሞት ዋዜማ ላይ ያሉትን አይደለም። በድረሱልን ጩኸት ውስጥ ያሉ አይደሉም። ነገርግን በመደበኛ ህይወታቸው ውስጥ ሆነው መደመጥን የሚፈልጉ። መደመጥን ከዚህ ከፍ አድርገን በአደጋ ባለ ሰው ህይወት ውስጥ ሆነን ስንመለከት የሚገባን ትልቅ ነው። አቅማችንን አይተን ፈጽሞውኑ ወደ ኋላ እንድንል የማያደርጉ ድምጾች።

ዛሬ ስለ መስጠት ስናነሳ ያልተሰሙ ድምጾችን ለመስማት የምንሄድበትን እርቀት ልናስብ ግድ ይላል። በተጋፋጭነት መንፈስ ሁላችንም ስለ አንድ ሰው ሞት አብረን የምንቆምበት ጊዜ። ሰው ስጦታ መሆኑን ተረድተን አንዳችን ለሌላችን ስጦታ ሆነን የምንኖርበት ህይወት።

ቀኖች መጥተው ይሄዳሉ። ህይወትም ይቀጥላል። አንዳችን በሌላችን ህይወት ውስጥ የሚኖረን ቦታ ግን ለህይወት ትርጉም ያለው ሆኖ ይታያል። በእንባ ውስጥ ለሚገኝ እምባን ማበስ በሌላው ሰው እንዲሆን እሻለሁ።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# “የእኔ ትልቁ ሱስ መሥራት እና ለአቅመ ደካሞች መስጠት ነው”



ፎቶ፡- እዮብ ተፈራ

ባለሀብቱ አቶ መሠረት መኮንን

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

የተወለዱት በደቡብ ጎንደር ነው። አባታቸው ሊቀ ካህናት መኮንን ታዬ በኃይለሳሴ ዘመነ መንግሥት በጎንደር ጠቅላይ ግዛት በከፍተኛ ኃላፊነት ደረጃ ይሰሩ ነበር። እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን በደቡብ ጎንደር መካነ እየሱስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተከታተሉት።

በ1980 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ በሀገሪቱ ጦርነት ስለነበርና አማራጭ ስላልነበራቸው ትምህርቱን ገታ አድርገው ፊታቸውን ወደ ንግድ አዞሩ። ገና በ19 ዓመታቸው የንግዱን ዓለም መቀላቀል ሲያስቡ ለመነሻ የሚሆን ገንዘብ የሚሰጣቸው አላጡም። ከቅርብ ቤተሰባቸው 500 ብር አገኙ፤ ንግዱንም አሀዱ ብለው ጀመሩት።

እኚህ የዛሬው የስኬት አምድ እንግዳችን አቶ መሠረት መኮንን ይባላሉ። ባገኙት ገንዘብ ጥራጥሬ ወደ ሱዳን እየወሰዱ መሸጡን ተያያዙት። ከሱዳን ደግሞ ጨው በማምጣት ጎንደርና ባህርዳር አካባቢ መሸጥ ጀመሩ። በዚህ ንግድ ዓመታትን ቆዩ፤ ጥሪትም አጠራቀሙ።

ጦርነቱም ረገበ። እርሳቸውም በወርሃ ነሃሴ 1983 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ከተሙ። ከዚያም ወደ ቶጎ ጫሌ፣ ኬኒያ፣ ሞያሌ፣ ጅቡቲ በመመላለስ የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችንና ዕቃዎችን መነገዱን ቀጠሉ። አቅማቸው ይበልጥ እየደረጀ ሲመጣ በ1992 ዓ.ም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚል ኩባንያ መሰረቱ።

በዚህ የንግድ ዓለም ውስጥ ነገሮች አልጋ ባልጋ እንዳልነበሩም ይናገራሉ። ብዙ ፈተናዎችን አልፈዋል። በርሃ ለበረሃ ተንከራተዋል፤በዚህም ሙቀቱ ፈትኗቸዋል። በማያውቁት አካባቢ ሲሄዱ ቋንቋ ፈትኗቸዋል። አልፎ አልፎም የንግድ መንገራገጮች ገጥሟቸዋል።

ቀደም ሲል በንግድ ዓለም ከተዋወቋቸው ሰዎች ጋር መመካከርና አዳዲስ ሐሳቦችንም ማፍለቅ ጀመሩ። 1992 ዓ.ም የኢትዮጵያን ባለሃብቶች ምርታቸውንና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ የሚያስችል ትልቅ አለም አቀፍ ኤግዚቢሽን በሳውዲ አረቢያ አዘጋጁ። ሜድሮክ ኢትዮጵያ፣ ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ፣ አምቦ ውሃ፣ አያት መኖሪያ ቤቶች፣ የኢትዮጵያ ማዕድንና ኮርፖሬሽንና ሌሎችም በኤግዚብሽኑ ተሳታፊ እንደነበሩ አቶ መሰረት ይገልጻሉ። እነዚህ ድርጅቶችም በዚያ ኢግዚቢሽን ብዙ ተጠቅመዋል ብለው እንደሚያስቡ የሚናገሩት አቶ መሰረት፣ እሳቸውም በዚያ ሥራቸው በሳውድ አረቢያ ልዩ ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል።

አቶ መሰረት በመቀጠልም ከሌሎች ባለሃብቶች ጋር በመቀናጀት ጥራጥሬ፣ ቅባት እህሎች፣ የሥጋ ውጤቶችና ቅመማ ቅመም ለውጭ ገበያ ማቅረብ ጀመሩ። ከአስመጪነትና ላኪነት በተጨማሪም በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራቱን ተያያዙት።

በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ፣ በሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍ፣ በሪል ስቴት ፕሮጀክት፣ በመኪና ኪራይ፣ በህንፃ ሽያጭና ኪራይ፣ በአስመጭነትና ላኪነት የተሰማሩ አገር በቀል ድርጅት ባለቤት ለመሆን በቅተዋል።

በአዲስ አበባ በ300 ሚሊዮን ብር ያስገነቡት ቤዝ ኢትዮጵያ ኢንተርናሽናል ሆቴል በአሁኑ ወቅት አግልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ በ130 ሚሊዮን ብር ካፒታል የታይልስ ፋብሪካ ያቋቋሙ ሲሆን 230 ዜጎች የሥራ ዕድል ማግኘት ችለዋል። 15 የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች፣ በአዲስ አበባ በኩባንያው ስም የተመዘገቡ ሦስት ግዙፍ ህንፃዎች ባለቤትም ሆነዋል።

በ500 ብር የጀመሩት ንግድ አጠቃላይ የፕሮጀክት ካፒታል በአሁኑ ወቅት 10ነጥብ5 ቢሊዮን ብር መድረሱን የሚናገሩት አቶ መሰረት፣ ሁሉም ፕሮጀክቶቻቸው በስራ ላይ መሆናቸውንም ነው የሚገልጹት። በእነዚህ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ተቋሞቻቸው ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

አቶ መሠረት አገራቸውን እና ዜጎቿን በእጅጉ እንደሚወዱ ይገልጻሉ። ይህንንም መንግሥት ለሚጠይቃቸው የልማትና የድጋፍ ጥያቄዎች ሁሉ ቀድመው ምላሽ በመስጠት እያረጋገጡ መሆናቸውን ነው የሚናገሩት። በዚህ በኩል ላከናወኗቸው ተግባሮች በርካታ የምስክር ወረቀቶች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ከንቲባ፣ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽንና ከሌሎች የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች እንደተበረከቱላቸውም ይጠቅሳሉ።

ባለሀብቱ አሁንም ሌላ ትልቅ ራእይ ሰንቀው መስራት ጀምረዋል። ለአዲስ አበባ ከተማ አቅሜ የፈቀደውን ይዤ መጥቻለሁ ሲሉ ይገልጻሉ። በአሁኑ ወቅት በሰፊው የገቡበት የሪል ስቴት ልማት ለዜጎች ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ትልቅ የውጭ ምንዛሬ ገቢን የሚያስገኝ ነው። ዳያስፖራዎችንና ትውልደ ኢትዮጵውያንን ከባንክ ጋር በማስተሳሰር የቤት ባለቤት ለማድረግ አቅደዋል።

ለዚህም ሥራ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በ8ነጥብ5 ቢሊዮን ብር ለሚገነባው ዘመናዊ መንደር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውሳኔ መሰረት በሊዝ መሬትና ካርታ ተረክበው ሥራ ጀምረዋል። ግንባታው 10 ባለ 12 ወለል ህንጻዎች፣ 90 ባለ ሁለት ወለል ቪላዎችና ዘመናዊ ቤቶች፣ ሲኒማ እና ሞል ያካተተ ነው። ይህ ግንባታ ለ2ሺ300 ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዓብይ አህመድ በተደጋጋሚ ስለሀገሪቱ ዕድገት፣ ቱሪዝምና ምጣኔ ሃብት ዕድገት ይመከራሉ፤ በተግባርም ያሳያሉ ሲሉ የሚጠቅሱት ባለሀብቱ፣ እንጦጦ ፓርክንና ሌሎች ፕሮጀክቶችን ማስገንባታቸውን ጎርጎራና የመሳሰሉትን ደግሞ እያሰሩ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

ባለሃብቶች ከዚህ በበለጠ መሥራት አለብን ሲሉም ነው ያስገነዘቡት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግብርና፣ በቱሪዝም፣ ቴክኖሎጂና ሌሎች መስኮች እያደረጉት ያለው ጥረት በጣም የሚደነቅ ነው። የእርሳቸውን ራዕይና ተልዕኮ ከጎናቸው ሆነን ማሳካት አለብን ሲሉ ገልጸው፣ይህ ሲሆን ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ማማ መውሰድ በጣም ቀላል ይሆናል ይላሉ።

እኛ እንደ አንድ ድርጅት የኢትዮጵያን ቱሪዝም ለማሳደግ በስፋት እየሰራን ነው ይላሉ- አቶ መሰረት። አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ሳውድ አረቢያ፣ አውስትራሊያ፣ ዱባይ እና ሌሎች ሀገራትም የቢዝነስ አጋር እየፈጠርን ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በክልል ከተሞችም ከፍተኛ የቤት እጥረት መኖሩን በመጥቀስም፣ ልማቱን ወደ ክልልም ይዘን ለመግባት ወስነን ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትርና ከክልሎች ጋር ተነጋግረናል ይላሉ። በዚህም በቀጣይ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ደቡብ፣ ድሬዳዋ ተጋጣጣሚ ቤቶችን ለመገንባት ዝግጅት እየተደረገ ነው። ለሥራቸው መቀናትም ከቱርክ ኩባንያዎች ጋር ተነጋግረዋል። ባለሀብቶች ጠቅላይ ሚኒስትሩን በትንሹም ቢሆን ማገዝ ይጠበቅብናል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች አሉ፤ እኛ ግን መሥራት አልቻልንም›› የሚሉት አቶ መሰረት፣ ኢትዮጵያ ተስማሚ የአየር ንብረት፣ የማዕድን፣ የተፈጥሮና የእንስሳት ሃብት እንዳላት ጠቅሰው፣ በቱሪዝም፣ በኢንዱስትሪ፣ በኮንስትራክሽን፣ በሪል እስቴትና ሌላውም ዘርፍ ለመስራት የሚያስችል በጣም ብዙ ዕድል እንዳለ ተናግረዋል።

የፖለቲካው ውጥንቅጥ፣ የሥራ ባህል አለመጠናከር፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ የተረጋጋ ገበያ አለመኖር ግን ፈተናዎች መሆናቸውን ነው የገለጹት። ይህ ሁሉ ተግዳሮት ብዙ መሥራት እየቻልን እንዳንሰራ እያረገን ነው ይላሉ። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ችግር አለ ብሎ ከማውራት ይልቅ መፍትሄ አይጠፋውም ብሎ መንቀሳቀስ ይበጃል ባይ ናቸው።

እኔ አንድ የሚሰማኝ ነገር አለ ይላሉ አቶ መሰረት፤ ሃብት የሚፈጠረው ለግልና ለሀገር ብቻ አይደለም ሲሉም ይገልጻሉ፤ በርካታ የሀገሪቱ ዜጎች ሥራ አልባ ናቸው። በዚህ ወቅት እንደ ባለሃብት የሥራ ዕድል መፍጠር አለብኝ። እኔ ያለኝን ሃብት ተጠቅሜ የሥራ ዕድል መፍጠር ግዴታዬ ነው። ሥራ የፈጠርኩለት ዜጋ ልጆቹን፣ እናቱን፣ አባቱን ወገኑን ሲረዳ ማየት ከምበላውና ከምጠጣው በላይ ያስደስተኛል ብሎ ማሰብ እንዳለበት ነው ያስገነዘቡት። ካለው ሃብት በላይ ትልቅ ተስፋ እና ደስታ መስጠት ነው። የእኔ ትልቁ ሱስ ሥራ መሥራት እና ለአቅመ ደካሞች መስጠት ነው። ያለን ማካፈል ሁሌም ያስደስታል። ምንም የማይሰሩት እናቶችና አባቶች ተስፋቸው እኛ ነን። ይህችን ሀገር ያቆዩ ሰዎች ሲጎሳቆሉ ማየት ያማል ይላሉ።

እኔ በቅርቡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባቀረበልኝ ጥሪ መሰረት፤ ለአቅመ ደካሞችና ለድሃ ድሃ የከተማዋ ነዋሪዎች የሚያገለግሉ ቤቶችን ሰርቻለሁ ሲሉ ይጠቅሳሉ። በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ባለሃብቶች ኮሚቴ ሆነን 180 ቤቶች ገንብተናል። ለድሃ ድሃ አራት የዳቦ ፋብሪካዎች በ87 ሚሊዮን ብር አቋቁመናል። በአጠቃላይ 210 ሚሊዮን ብር አሰባስበን ወጪ አድርገናል።

ከሸገር ዳቦ ፋብሪካ ጋር በመዋዋል በቀን 30ሺ ዜጎች ዳቦ እንዲያገኙ ማድረግ ችለናል። የሸገር ዳቦ ሱቆችን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በሚገኙ 13ቱም ወረዳዎች ገንብተናል። አሁንም በ90 ቀን ሰው ተኮር ፕሮጀክት ባለሃብቶችን በማስተባበር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እየሠራን ነው።

ድርጅታቸው ደግሞ የቱሉ ዲሚቱ ዓደባባይን በ10 ሚሊዮን ብር እጅግ ዘመናዊ በሆነ ዲዛይን እየገነባ መሆኑን ይገልጻሉ። እኔና ቤተሰቤ አሁን ያለንበትን ህይወት እግዚአብሄር ሰጥቶናል፤ ቤተሰቤ ሲደሰት ሌላው መብራት ላይ ቆሞ ሲለምን ውስጤን ይነካኛል ይላሉ።

እሳቸው ሰው ለምን ይለምናል? ሲሉ ይጠይቃሉ። ሥራ ቢኖረው፤ አቅመ ደካማ ባይሆን ወይንም ወላጅ አልባ ባይሆን አይለምንም። እነዚህን መርዳት ከደስታ በላይ ነው። እኔ ለአንድ ድሃ ስሰጥ መጀመሪያ ጥሪውን የሚያቀርበው፣ የሚያመሰግነውና ደውል የሚደውለው ለፈጣሪው ነው። ይህ ደግሞ በእምነት ዓይን ትልቅ መልዕክት አለው። መስጠት በረከት ነው፣ በራሱ ዕድል ነው፤ ፀጋ ነው። ሃብት ሰብስበን መጨረሻ ጥለነው እንሄዳለን። ለሀገር፣ ለወገን፣ ለዜጋ ሰጥቶ መሄድ መልካም ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ።

አቶ መሠረት በብዙ ስራዎች ውስጥ ናቸው፤ እንዲያም ሆኖ አሁንም ቢሆን፣ ገና ምን ተሰርቶ ሲሉ ይጠይቃሉ። ኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፍ ያልተነካ ሃብት እንዳላት ነው የሚናገሩት።

ከዘመናዊ አፓርታማዎች በተጨማሪ ከ5 እስከ 10 ዓመታት በሚሆን ጊዜ ውስጥ ከመንግስት ጋር በመሆን አንድ ሚሊዮን አነስተኛ እና ወጪ ቆጣቢ ቤቶችን ለመገንባት ዝግጅት እያደረጉ ነው። ለዚህ የሚያስፈልጉትን ሁሉንም ግብዓቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ማምረት እንደሚቻል ይናገራሉ። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ቴክኖሎጂ የማስገባት ሥራ መጀመራቸውን ይገልጻሉ።

ባለሀብቱ በአገልግሎት ዘርፍ ብዙ ሥራዎችን ያሰቡ ቢሆንም፤ በአሥር የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ መዝናኛና የባህል ማዕከላትን መገንባት ቀዳሚው ሥራቸው ነው። ቤዝ ኢትዮጵያ ኢንተርናሽናል በአሥር የቱሪስት መዳረሻዎች አካባቢዎች እያንዳንዳቸው ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የቱሪስት መዝናኛና የባህል ማዕከላት የመገንባት ውጥን አለው። በተለይም ኤርታሌ፣ ሶፍ ኡመር፣ ጢስ ዓባይ፣ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ዳሎል አፋር፣ አርባ ምንጭ፣ ኮንሶ፣ የቱሪስት መዳራሻዎች በዚህ ፕሮጀክት ታቅፈዋል።

ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ ከኬኒያ፣ ታንዛኒያ፣ ዑጋንዳ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ አቅም አላት፤ የምታገኘው ገቢ ግን እነዚህ ሀገራት ከሚያገኙት አኳያ ሲታይ አምስት በመቶ አይሞላም የሚሉት አቶ መሠረት፤ በርካታ የቱሪስት መዳረሻዎች ሠላማቸው የተጠበቀ ባለመሆኑና ባለሃብቱም በዚህ ላይ ባለመስራቱም ሀገራችን ከዘርፉ አልተጠቀመችም የሚል ቁጭት አላቸው። በቀጣይ በእነዚህ የመዳረሻ ቦታዎች የመዝናኛና የባህል ማዕከላትን የሚገነቡት ይህን ታሳቢ በማድረግ ነው።

በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡት እነዚህ ማዕከላት ከጥቂት ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በስተቀር ሙሉ በሙሉ አካባቢው ላይ ባሉ ባህላዊ ቁሳቁስ የሚሠሩ ናቸው። እያንዳንዳቸው ከ50 በላይ የመኝታ ክፍሎች፣ ዘመናዊና ባህላዊ ሬስቶራንቶች፣ የየክልሉን ባህል የሚያሳዩ ሙዚቃ የሚቀርቡባቸው፣ ጎብኚዎች ባህላዊ ምግብና መጠጦች የሚያገኙባቸው አዳራሾች፣ አነስተኛ ሙዚየሞች፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችና ሌሎችም ዘመናዊ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። ለእነዚህ ስራም የገንዘብ አቅርቦት ከባንክ መገኘቱን አቶ መሰረት ጠቅሰው፣ የፀጥታው ችግር መፍትሄ ካገኘ ግንባታውን በቀጥታ እንደሚጀምሩም ነው የተናገሩት።

አቶ መሰረት መልዕክትም አስተላልፈዋል። ሁልጊዜም የምናገረው ኢትዮጵያ ትልቅና ሃብታም ሀገር ናት። በሁሉም ዘርፍ ተዝቆ የማያለቅ ሃብት አላት፤ ግን አልተጠቀመችበትም ይላሉ። እንድትጠቀም የምናዳርገው ደግሞ በዚህች ሀገር ጥላቻን በማስወገድ፣ በመተባበር፣ በቅንነትና በመተሳሰብ እና በመተባበር ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ፍቅር፣ አንድነትና ሠላም ካለን ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናት፤ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገሮች በበለጠ ትልቅና የተለየች ናት፤ ችግሩ የእኛ የዜጎቿ እንጂ ኢትዮጵያ እንከን የለባትም ያሉት አቶ መሰረት፣ ሀገሪቱ በአጭር ጊዜ ትልቅ ለውጥ ማምጣት እንደምትችልም ነው ያስታወቁት። ማንም ባለሃብት፣ ዜጋ ሆነ ባለስልጣን ሀገሩን መስረቅ እንደሌለበት አስገንዝበው፣ ይህን የሚደርግ ከራሱ እንደሰረቀ ማሰብ አለበት ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ በፓርላማ ስለሙስና የተናገሩት በጣም ትክክል መሆኑንም በመጥቀስ፣ እኔ የሚታየኝ ይህችን ሀገር አምስት ቡድኖች እያጠቋት እንደሆነ ነው ሲሉ ይጠቁማሉ። ማፊያ ባለስልጣናት፣ ማፊያ አክቲቪስቶች፣ ማፊያ ባለሃብቶች፣ ማፊያ ፖለቲከኞች እና በሃይማኖት ካባ ተደብቀው የሚንቀሳቀሱ ማፊያ ሃይማኖተኞች ሀገሪቱን በከፍተኛ ደረጃ እያጠቁ እና ህዝብን ለችግር እየዳረጉ ነው ሲሉ አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ባለሃብት ነኝ የሚል ሰው፤ ሀገሩን፣ መንግስትን፣ ህዝብን፣ ሃይማኖቱን የሚያከብርና ከሀገሩ የማይሰርቅ መሆን አለበት። ታሪክን ለማሸጋገር መጀመሪያ ለራስ ንጹህ መሆን ያስፈልጋል። ጥሩ ዜጋ ለመፍጠር መጀመሪያ ንጹህ መሆን ይገባል።

‹‹ራዕይችን ሰፊ መሆን አለበት፤ ሀገራችን ለሁላችንም ሁሉንም መሆን ትችላለች፤ ሀገራችን የተፈጠርንባት፣ ያደግንባትና የምንኖርባት ስለሆነ ልንጠብቃት ይገባል›› ሲሉ አስገንዝበው፣ ፍቅር፣ ሠላም፣ አንድነትና ለውጥ እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## በተራቀቀ ቴክኖሎጂ የተደራጀው የአንድነት መኪና ማቆሚያ

መላኩ ኤሮሴ

መኪና ላላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች መኪና የሚያቆሙበትን ቦታ ማግኘት ትልቁ ጥያቄ ከሆነ ቆይቷል። የአዲስ አበባና ከተለያዩ ክልሎች ወደ ከተማዋ የሚመጡ ባለተሽከርካሪዎች በከተማዋ የሚስታዋለውን አሰልቺውን የትራፊክ መጨናነቅ በትዕግስት አልፈው የሚፈልጉበት ቦታ ከደረሱ በኋላ መኪና ማቆሚያ ቦታ ለማግኘት ብዙ መባዘን ይጠበቅባቸዋል።

በመኪና ማቆሚያ ቦታ እጦት ምክንያት ባልተገባ ቦታ ለማቆም ይገደዳሉ፤ ይህ ደግሞ ለተሽከርካሪ እቃዎች እና በመኪና ውስጥ ላስቀመጧቸው እቃዎች ስርቆት እንዲሁም ለትራፊክ ቅጣት እያጋለጣቸው ይገኛል። ተሽከርካሪዎች የሚሰረቁበት ሁኔታም ይስተዋላል።

በከተማዋ እየተባባሰ በመጣው የመኪና ማቆሚያ ቦታ ችግር ምክንያት ከመኪና አሽከርካሪዎች ባልተናነሰ እግረኞችም ሲቸገሩ ይታያል። በመንገድ ዳር እና በእግረኞች መንገድ ላይ መኪናዎች እንዲቆሙ የሚደረግበት ሁኔታ የትራፊክ እንቅስቃሴን ከማስተጓጎሉ ባሻገር የእግረኞችን ጉዞ አስቸጋሪ አድርጎታል።

በአዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የከተማዋን መኪና ማቆሚያ ችግር በመጠኑም ቢሆን ሊያቃልሉ የሚችሉ የመኪና ማቆሚያዎች እየተገነቡ ናቸው። በመገናኛና በመርካቶ አንዋር መስኪድ አካባቢ ቀደም ሲል የመኪና ማቆማያዎች ተገንብተዋል፤ ባለፈው አመት ደግሞ በመስቀል አደባባይ ግዙፍ የመኪና ማቆሚያ በመሬት ውስጥ ተገንብቷል። የመስቀል አደባባዩ የመኪና ማቆሚያ በአካባቢው ያለውን የመኪና ማቆሚያ ችግር በወሳኝ መልኩ ይፈታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ነው።

በቅርቡ ደግሞ የአንድነት ፓርክ መኪና ማቆሚያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ ተመርቆ እነዚህን የመኪና ፓርኮች ተቀላቅሏል። የመኪና ማቆሚያው የከተማዋን በተለይም በአንድነት ፓርክ አካባቢ ሲታይ የቆየውን የመኪና ማቆሚያ እጥረት ይፈታል።

የመኪና መቆሚያው በአንድ ነጥብ ሁለት ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ግንባታው የመሬት ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ የዋለበትም ነው። ከመሬት በታች አራት ወለሎችን /G-4/ እንዲይዝ ተደርጓል። በተጨማሪም ከመሬት ወደ ላይ ባለ አራት ወለል ህንጻም /G+4/ አለው።

መረጃዎች እንደሚያሳዩትና እኛም ተዘዋውረን እንደተመለከትነው፤ ከወለል በታች ያሉት አራቱም ወለሎች ሙሉ በሙሉ ለመኪና ማቆሚያነት የሚያገለግሉ ናቸው። ወለሎቹ / ቤዝመንቶቹ/ አውቶብሶችን ጨምሮ ከአንድ ሺህ በላይ መኪናዎችን በአንድ ጊዜ የማስተናገድ አቅም አላቸው።

እጅግ ሰፊ የሆነው ይህ የአንድነት የመኪና ማቆሚያ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በሌሎች የመኪና ማቆሚያዎች ያልተገጠሙ ቴክኖሎጂዎች ተደርገውበታል። የመኪና ማቆሚያ ደህንነቱን አስተማማኝ ለማድረግ ከ200 በላይ የደህንነት ካሜራዎች ተገጥመውለታል። ካሜራዎቹም ተሽከርካሪው የቆመበትን ጊዜ ይቆጥራሉ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የመኪና ማቆሚያን የሚያረጋግጥ የክትትል ቅኝት ሥራ ይሰራሉ፤ እንደ አስፈላጊነቱ የመኪና መለያ /ሰሌዳ/ እንዲሁም የተገልጋዩን ማንነት መለየትም ያስችላሉ።

በዚህ የመኪና ማቆሚያ ለሰዎች ብቻ አይደለም አሳንሰር/ ሊፍት/ የተገጠመው። ለመኪናዎችም ነው። ይህ አሳንሰር መኪኖችን ከወለል በታች ካሉ የማቆሚያ ቦታዎች ጋር በቀላሉ ለመተሳሰር ከመርዳቱም በተጨማሪ የዝቅታ ፍርሀት ያለባቸውንም ሰዎች ታሳቢ ተደርጎ የተገጠመ ነው።

በተጨማሪም ዘመናዊ የተሽከርካሪዎች መረጃ መመዝገቢያና፣ ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት መፈጸሚያ፣ የደህነነት መጠበቂያ ሥርዓቶችን ያሟላም ነው። ለአብነትም ተሽከርካሪ የሚቆምበትን ቦታ መያዝ እና አለመያዝ የሚያሳዩ በርካታ ስክሪኖች አሉት፤ ይህም በጣም ዘመናዊ ያደርገዋል።

ከመኪና ማቆሚያ ውጪ ባሉ ቦታዎች ላይ ደግሞ ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ አራት ወለሎችም አሉት። ወለሎቹ ለቢሮ አገልግሎት፣ ለመስሪያ ቤት፣ ለተገልጋዮች መሰብሰቢያ፣ የጥበብ ትርኢቶች እና ሌሎች ዝግጅቶች ማካሄጃ የሚውሉ ስፍራዎች አሉት። የተለያዩ መዝናኛዎች እና አገልግሎቶችን የሚሰጡ ባንኮች፣ ካፌዎች፣ ወዘተ፣ ገብተው እየሰሩ ይገኛሉ። በአጠቃላይ





ፕሮጀክቱ በርካታ አገልግሎቶችን በአንድ ቦታ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተገነበ ነው።

ህንጻው የተሰራበትና አበቦችና ሌሎች አትክልቶች የለሙበት መንገድ ግቢውንና አካባቢው ይበልጥ ውብ አርገውታል። አካባቢውን / በተለይም አንድነት ፓርክን፣ የሳይንስ ሙዚየምንና የመሳሰሉትን የአካባቢውን ገጽታዎች በቅርብ ርቀት ለመቃኘት የሚያስችል መሆኑ በራሱ የሌላ ውበት ባለቤት አርጎታል።

የመኪና ማቆሚያውን ከአንድነት ፓርክ ጋር የሚያገናኝ ውስጥ ለውስጥ መተላለፊያ መንገድም/ ዋሻ/ ተገንብቶለታል፤ የአንድነት ፓርክን መጎብኘት የሚፈልጉ መኪና የያዙ ጎብኚዎች መኪናዎቻቸውን አስተማማኝ በሆነው የአንድነት መኪና ማቆሚያ ውስጥ በማቆም በዋሻው ውስጥ አልፈው ፓርኩን መጎብኘት ይችላሉ። ሌሎች የአንድነት ፓርክ ጎብኚዎችም በእዚህ ህንጻ በኩል አርገው በዋሻው ውስጥ አልፈው ነው ፓርኩን የሚጎበኙት።

ከአካባቢው በቅርብ ርቀት ለሚገኙት ሳይንስ ሙዚየም፣ አብርሆት ቤተ መጽሃፍት እና የወዳጅነት አደባባይ በእግር ጉዞ ርቀት ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ዝና ብለው በእግር መጓዝ የሚፈልጉ ሁሉ መኪናቸውን በአንድነት ፓርክ ለመቆም የሚያስችል ሌላ ተመራጭ ስፍራ ነው።

የመኪና ማቆሚያው ከህዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት በነጻ የፓርኪንግ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፤ በርካታ ተገልጋዮችም በነጻ የፓርኪንግ አገልግሎቱ ተጠቃሚ እየሆኑ ነው።

የመኪና ማቆሚያውን ወለሎች አንድ በአንድ በእግር እየወረድን ጎብኝነው። በእያንዳንዱ ወለል በርከታ መኪኖችን ማቆም የሚያስችሉ ውብ ስፍራዎች ተዘጋጅተዋል። በየወለሉ የተለያዩ ስፍራዎች ለአሽከርካሪዎች መረጃ የሚያስተላልፉ ልዩ ልዩ ምልክቶች ተደርገዋል፤ መግቢያ መውጫውን የሚያመላክቱ፣ ሊፍቱን ደረጃውን የሚጠቁሙ መረጃዎች በየአቅጣጫው በግልጽ ተመልክተዋል። አንዳንዶቹ ወለሎች መኪና ቆምባቸዋል፤ አንዳንዶቹ መኪኖችን ይጠብቃሉ።

ወይዘሮ ጊፍቲ ሳሙኤል የስራ ቦታቸው ከአንድነት መኪና ማቆሚያ ጀርባ በሚገኘው ፓላስ ህንጻ ላይ ነው፤ ባለሱቅ ናቸው። ቀድሞ በአካባቢው መኪና ማቆሚያ እንዳልነበረ ይናገራሉ። በዚህም ምክንያት እሳቸውም ሆኑ ደንበኞቻቸው መኪና ለማቆም እጅግ ይቸገሩ ነበር።

ካዛንቺስ አካባቢ የሚገኙ መንገዶች ቀኝና ግራ መኪና ለማቆም አስቸጋሪ መሆኑን ይገልጻሉ። በተለይም ጠዋት ከ4 ሰዓት በፊት በአካባቢው መኪና ማቆም አይቻልም፤ ማታ ከ11 ሰዓት በኋላ መቆም አይቻልም። በዚህም ምክንያት ለደንበኞቻቸው አገልግሎት ለመስጠት እጅግ አስቸጋሪ ሆኖባቸው ቆይተዋል። ደንበኞች በሚፈልጉበት ሰዓት መኪና ማቆሚያ በማጣታቸው እንደሚቸገሩ ይናገራሉ።

የአንድነት መኪና ማቆሚያ ግንባታ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ግንባታው ተጠናቆ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን በጉጉት ሲጠባበቁ እንደነበሩ የሚናገሩት ወይዘሮ ጊፍቲ፣ የፓርኩን ግንባታ እያንዳንዱን ሂደት በቅርበት ሲከታተሉ መቆየታቸውን ይናገራሉ። ፕሮጀክቱ መቼ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል ብለው በጉጉት ሲጠባበቁ ቆይተዋል፤ ፕሮጀክቱ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሮ ማየታቸው እጅግ አስደስቷቸዋል። ፕሮጀክቱን በቅርብ ጊዜ ከተገነቡ የተሳኩ ፕሮጀክቶች አንዱ ሲሉ ገልጸውታል።

ፓርኩ ገና ስራ መጀመሩ ቢሆንም አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ወዲህ ለሁለት ቀናት መጠቀማቸውን የሚጠቅሱት ጊፍቲ፤ ይህን ቃለ ምልልስ በሰጡን ቀን ለሶስተኛ ቀን ወደ ፓርኩ መምጣታቸው ነው። መኪና ማቆሚያው ለስራ ቦታቸው ቅርብ ከመሆኑ ባሻገር ለመኪናቸውም ደህንነት እጅግ ምቹ ሆኖ አግኝተውታል። በፓርኩ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ለማየት እና በቀጣይ የአገልግሎቱ ቋሚ ተጠቃሚ ልሁን ወይስ አልሁን የሚለውን ለመወሰን ወደ ፓርኩ በተደጋጋሚ መመላለሳቸውን ተናግረው፣ የመኪና ማቆሚያው ቋሚ ደንበኛ ለመሆን መወሰናቸውን ተናግረዋል።

የክፊያ ተመን ሲወጣ ተጠቃሚውን ለማብዛት ክፊያው ተመጣጣኝ ቢሆን መልካም ነው ያሉት ጊፍቲ፣ የሰውን ገቢ ያማከለ ቢሆን ተገልጋዮችንም ሆነ ፓርኩን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ይጠቁማሉ።

አዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የሆነ የፓርኪንግ ችግር ያለባት ከተማ መሆኗን የጠቆሙት ጊፍቲ ፤ በተለይም ካዛንቺስ አካባቢ የንግድ እንቅስቃሴ የሚበዛበት እንደመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የመኪና ማቆሚያ ችግር እንዳለ ይገልጻሉ። እሳቸው አንድነት መኪና ማቆሚያ ይህን የአካባቢውን የመኪና ማቆሚያ ችግር የሚቀርፍ እንደሚሆን እምነቱ አላቸው።

በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች የሚስታዋለውን የፓርኪንግ ችግር ለመፍታት ተመሳሳይ መኪና ማቆሚያዎች በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች መገንባት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል። የመሰል መኪና ማቆሚያዎች መበራከት ለተገልጋዮች ከሚያስገኘው ጥቅም ባሻገር ለከተማዋ ውበት የራሱን አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ተናግረዋል።

በፓርኪንጉ ውስጥ የባንክ፣ የቴሌ፣ የካፌ እንዲሁም የአየር መንገድ የቲኬት አገልግሎቶችን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶች መኖራቸው ለአካባቢው፣ መኪናውን ለሚያቆሙት እንዲሁም ለፓርኩ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያስገኝ ጠቁመዋል። በተለይም አብዛኞቹ በፓርኩ ውስጥ የተከፈቱ አገልግሎች በአካባቢው የሌሉ መሆናቸው ለአካባቢው ማህበረሰብ ያላቸው ፋይዳ የላቀ መሆኑንም ይገልጻሉ።

ፓርኩ ከአሁኑ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር ችሏል። በርካታ ወጣቶች አስፈላጊውን ስልጠና ወስደው ወደ ስራው መግባታቸው በስፍራው ከሚሰሩ ወጣቶች መረዳት ችለናል። ደሳለኝ አጥናፉ በፓርኩ ውስጥ የስራ እድል ከተፈጠረላቸው ወጣቶች አንዱ ነው። ደሳለኝ ወታደር ነበረ፤ በውጊያ ወቅት ቆስሎ ህክምናውን ጨርሶ ከወጣ በኋላ አስፈላጊውን ስልጠና ወስዶ በመኪና ማቆሚያው ውስጥ የስነ ስርዓት አስከባሪ ሆኖ እየሰራ ነው። እንደሱ በተመሳሳይ ወደ 48 የሚደርሱ ሰዎች ስራ እድል እንደተፈጠረላቸውም ተናግሯል።

ማቆያ በለጠም እንዲሁ ሌላ የስራ እድል የተፈጠረለት ወጣት ነው፤ ማቆያ ስራ አጥ ነበረ፤ ፓርኩ የስራ ማስታወቂያ ሲያወጣ ተወዳድሮ መቀጠሩን ይገልጻል። በመኪና ማቆሚያው ውስጥ ካሸር ሆኖ ማገልገል ጀምሯል። በደረጃ 4 ተወዳድረው 15 ልጆች በካሸርነት ተቀጥረው እየሰሩ መሆናቸውን ጠቅሶ፣ ሌሎችም በተለያዩ ስራዎች ተቀጥረው እየሰሩ መሆናቸውን ጠቁሟል።

ፕሮጀክቱ በተመረቀበት ወቅት ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በከተማዋ ውስጥ የተለያዩ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ መሆናቸውን ተናግረዋል። እነዚህ ፕሮጀክቶች ተሰናስለው አዲስ አበባን አዲስ ገጽታ በማላበስ የብልጽግናን አይቀሬነት የሚመሰክሩ ናቸው ብለዋል። የአንድነት መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በመሆን አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ ከሚያደርጓት ፕሮጀክቶች አንዱ ነው ብለዋል።

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፤ የፕሮጀክቶቹ ትርጉም ብዙ ነው። ለሌሎች ፕሮጀክቶች ትልቅ ትምህርት የሚሰጡም ናቸው፤ ፕሮጀክት ጀምሮ በመጨረስ አዳዲስ ልምዶች ተገኝቷል፣ ግንባታቸውን በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት በማጠናቀቅ የሌብነትን በር መዝጋት ተችሏል ብለዋል።

በተለይም የፕሮጀክት ጊዜ በመራዘም ምክንያት የሚጨምሩ በስፔስፊኬሽን ውስጥ ያልገቡትን በማስገባት ዋጋን በማዛባት የሚበላው የህዝብ ገንዘብ እንዳይበላ በማድረግ ብዙ ልምድ እንደተገኘበትም አብራርተዋል። እስካሁን የተገነቡ ፕሮጀክቶችን ለሌሎች ፕሮጀክቶችም እንደ ምሳሌ በመውሰድ የሚታቀድበት እና የሚተገበርበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማስቻላቸውን ነው ያብራሩት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ መኪና ማቆሚያውን መርቀው ሲከፍቱ እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ ለኢትዮጵያ፣ ለአዲስ አበባ፣ ለኢትዮጵያ ልጆች፣ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚመጥን ነው። የነገይቱን ኢትዮጵያ ምስል የሚያሳይ ነው።

መጀመሪያ ቢሯችንን ቀጥሎ ግቢያችንን፣ ከዚያም አካባቢያችንን እንዲሁም ሀገራችንን በሚለው መርህ በቤተመንግስት አካባቢ ትናንት፣ ዛሬን እና ነገን የሚያገናኙ በርካታ ፕሮጀክቶች ተሰርተዋል ብለዋል።

ዛሬ ድልድይ ሆኖ ትናንትናን ከነገ የማያገናኝ ከሆነ የሀገር እና የተቋም ግንባታ በተሟላ መልኩ እንደማይከናወን ጠቅሰው፣ ትናንትናን ከዛሬ፣ ዛሬን ከነገ የሚያገናኙ ፕሮጀክቶች ስንሰራ ከብልጽግና መንገድና ዐሻራ፣ ከብልጽግና ጉዞ ጋር የሚቃኝ ዕሳቤ ያለው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል። ማንኛቸውም ስራዎች ለኢትዮጵያ የሚገባትን ብልጽግና የሚያመጡ መሆናቸውን ታሳቢ ያደረጉ ስራዎች መሆናቸውን ገልጸው፣ ከለውጡ በኋላ የተገነቡ ፕሮጀክቶች ትናንትናን እና ነገን የሚያገናኙ ናቸው ብለዋል። ፕሮጀክቶች ለትውልዱ ለአዕምሯዊና አካላዊ ጤንነት ከፍ ያለ ጥቅም ያላቸው መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ፕሮጀክቶች ቃል በተገባላቸው መሰረት እየተፈጸሙ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጀመርነው የለውጥ ጉዞ ስኬት ለትውልድ እንዲተርፍ በብሩህ ተስፋችን ላይ ጸንተን እንቁም !

አንድ ሃገር እንደ ሃገር ለመቀጠል ከትናንት ላይ የሚነሳ ነገን ተስፋ ያደረገ የአስተሳሰብ መሠረት ሊኖራት ይገባል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ትልቅ ሀገር ስለመፍጠር ቀርቶ ስለ ሃገር ማሰብ የሚቻል አይደለም። ለማሰብ መሞከርም ከየዋህነት ባለፈ ”ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ” ያህል ነው የሚሆነው።


በተለይም እንደእኛ ባሉ ረጅም ዘመን በግጭትና ከዚህ በሚመነጭ የችግር አዙሪት ውስጥ ከፍ ያለ ዋጋ እየከፈሉ ለመጡና አሁንም ዋጋ እየከፈሉ ላሉ ሕዝቦች ፤ ከችግሮቻቸው አዙሪት ለመውጣት ነገ ላይ አስቦ መሥራት፤ ነገን በተሻለ ተስፋ አልሞ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ ውጭ ከትናንት እና ትናንቶች ከወለዷቸው ችግሮቻቸው መሻገር የሚችሉበት አቅም/ዕድል ሊያገኙ አይችሉም።

ትናንት በጊዜ ሂደት ውስጥ ጥሩም ሆነ መጥፎ የሚባሉ ጠባሳዎችን አሳቀምጦ ዛሬ ሆኖ እንዳይመለስ አልፏል። ከትናንት ጋር የተያያዙ ጠባሳዎችንም ማከም የሚቻለው ትናንት ላይ ሆኖ ማሰብ የሚያስችል የአዕምሮ ውቅር ሲኖረን ብቻ ነው። ከዛ ውጪ ታሪክና ዛሬን የተሻለ ለማድረግ የሚያስችል የመማሪያ መጽሐፍ ነው።

ከዚህ መጽሐፍ ለመማር ደግሞ ከሁሉም በላይ ጊዜ በአስተሳሰብ ላይ የሚኖረውን ከፍ ያለ ተጽዕኖ በነፃ ሕሊና መረዳትና በመረዳት ሂደት ውስጥ ለተገኘው እውነት ታማኝ መሆንን የሚጠይቅ ነው። ለዚህ ደግሞ ከራስ ጋር መታረቅንና ከዚህ የሚመነጭ ስብዕና መገንባትን ይፈልጋል።

በሀገራችን ዘላቂ ሰላም ለማምጣትም ሆነ የጀመርነውን የለውጥ አስተሳሰብ በማስፋት ሀገራዊ ብልጽግና ለማምጣት የሚቻለውም ትናንቶችን በቀና መንፈስና በራሳቸው ሁለንተናዊ ቁመና መረዳት የሚያስችል የአስተሳሰብ መሠረት መፍጠር ስንችልና ለአስተሳሰቡ መታመን የሚያስችል ማንነት ስንገነባ ነው።

በአንድም ይሁን በሌላ ትናንቶች እንደሀገር ብዙ ዋጋ አስከፍለውናል፤ ብዙ ጠባሳዎችንም ፈጥረውብን አልፈዋል። እነዚህን ጠባሳዎች እያከኩ የማቁሰሉ የፖለቲካ ሂደት፤ የትናንት ጠባሳ የሌለበት የማኅበረሰብ ክፍል ካለመኖሩ አንጻር ማንንም ሊጠቅም የሚችል አይደለም።




ጠባሳዎችን እያከኩ የማቁሰሉ የፖለቲካ ሂደት ጠባሳውን ለማስወገድ ሆነ ጠባሳው የፈጠረውን ታሪካዊ ክስተት ለማከምና ዳግም ሀገራዊ በሽታ እንዳይሆን ለማስቻል የሚደረገውን ጥረት ከማሰናከል እና ዛሬን የትናንት ጥላ ውስጥ ከመክተት ባለፈ አንዳች ፋይዳ አይኖረውም። ፋይዳ ይኖረዋል ብሎ ማሰብም በጠባሳው ከመቆመር ያለፈ ትርጉም አይኖረውም ።

እንደ ሃገርና ሕዝብ ከአራት ዓመት በፊት በብዙ ተስፋ እና መስዋዕትነት የጀመርነው የብልጽግና መንገድ ፍሬ እንዲያፈራ ከትናንት እና ትናንቶች ከፈጠሯቸው ጠባሳዎች ወጥተን ነገን ተስፋ በሚያደርግ የአስተሳሰብ መሠረት ላይ መቆም ይጠበቅብናል። ይህንን ማድረግ ካልቻልን ተስፋ ያደረግነው ሃገራዊ ብልጽግናም ሆነ ለዚሁ የከፈልነው መስዋዕትነት ትርጉም አልባ መሆኑ የማይቀር ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከትናንት በስቲያ በሃዋሳ በተከበረው የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክብረ በዓል ላይ ባስተላለፉት መልዕክታቸው ”ትናንት ያለፈና ያመለጠ ታሪክ ነው፣ ትናንትን ለመማሪያ ብቻ መጠቀም ከቻልን ነጋችን ያማረ ይሆናል። ዛሬ የትናንትናውን ጉዳይ እያነሳን ብንወቅስና ብናወድስ ግን ሰዎቹ የሉምና አይሰሙንም። ያጠፉትም ያለሙትም አልፈዋል” ማለታቸው ለዚህ ነው።

ከትናንት እና ትናንቶች ከወለዷቸው ጠባሳዎቻችን ዓይኖቻችንን እናንሳ፤ጠባሳዎቹን እያከኩ ከሚያቆስሉና ከቁስላችንም የፖለቲካ ትርፍ ከሚሹ ነጋዴዎችም ራሳችንን እናርቅ፤ ነገዎቻችንን ተስፋ አድርገን የጀመርነው ለውጥ ለትውልዶች እንዲተርፍ ተስፋችን ላይ ፀንተን እንቁም!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## በጽናት የመቻል ተምሳሌትነት - ከኳታር

ብርሃን ፈይሳ

ከዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ውድድሮች ሁሉ በተወዳጅነት ቀዳሚው የዓለም እግር ኳስ ዋንጫ ስለመሆኑ አያጠራጥርም። እግር ኳስ የዓለም ቋንቋ ነው የሚባለውም ቢሊዮኖች ሃገራቸው በውድድሩ ብትሳተፍም ባትሳተፍም በአካልና በቴሌቪዥን መስኮቶች ስለሚከታተሉት ነው። የብዙዎች የልጅነት ትዝታ እና የአይረሴ አጋጣሚዎች ማህደርም ነው- ዓለም ዋንጫ። በአራት ዓመት አንዴ የሚካሄደው ይህ ውድድር የበርካታ እግር ኳስ ተጫዋቾች ሕልም፤ የሃገር ፍቅር ማሳያ፣ የሃገራት ሁለንተናዊ ስኬት መለኪያም ነው።

ዓለም ዋንጫ ከእግር ኳስ እና ስፖርታዊ ውድድርነቱ የተሻገረ ትርጉምም አለው። ማኅበራዊ ግንኙነት የሚጠበቅበት፣ ኢኮኖሚያዊ አቅም የሚፈተንበት እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችም የሚንጸባረቁበት ግዙፍ አውድ ነው። ከሰሞኑ የዓለምን ህዝብ ዓይን፣ ጆሮ እና ትኩረት በእጅጉ የሳበችው ኳታርም ለዚህ ማሳያ ናት። በዓረብ ምድር ላይ ዓለም ዋንጫን በማዘጋጀት አዲስ ታሪክ ያስመዘገበችው ኳታር በተግባሯ ለሌሎች ተምሳሌት መሆን የምትችል ናት።

እንደሚታወቀው ሃገሪቷ የዓለም ዋንጫውን እንድታስተናግድ መመረጧ ከተሰማበት ቅጽበት አንስቶ በአብዛኛው የዓለም ሕዝብ ዘንድ የተንጸባረቀው ቅራኔ ነበር። የአዘጋጅነት ዕድሉን ያገኘችው በሙስና እንጂ በመቻሏ መሆኑን ማመን ያልፈለጉ አካላት በእጅጉ ሲያብጠለጥሏት ቆይተዋል። በዚህ እንደማይሳካላቸው ሲገባቸው ደግሞ አስቀድሞ ለስፖርት የተዘጋጀ መሠረተ ልማት ያልነበራት ሀገሪቷ በተቀመጠላት የጊዜ ገደብ ዝግጅቷን ታጠናቅቅ ይሆን የሚለውን ከጥርጣሬ የመነጨ ጥያቄ አቀረቡ። ከሚገነቡ ስታዲየሞች ጋር በተያያዘም የሰብዓዊ መብት ጉዳይን እንዲሁም ልዩ ልዩ የማሰናከያ ሃሳቦችን በማንሳት ከአዘጋጅነቷ እንድትነሳ ለማድረግ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ኳታሮች ግን በቀላሉ እጅ የማይሰጡ መሆናቸውን የሚደርስባቸውን ጫና ተቋቁመው ይህን የመሰለ ታሪካዊ ውድድር በማሰናዳት አረጋግጠዋል። ለዓላማቸው የነበራቸው ጽናትና እንደ ሀገር በአንድ መቆማቸው ይበልጥ እንዲጠነከሩና የመጨረሻውን ድል እንዲያጣጥሙም ምክንያት ሆኗቸዋል።

ኳታር ለስፖርቱ በሰጠችው ከፍተኛ ትኩረት እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት ስታዲየሞችንና ሌሎች የስፖርት መሠረተ ልማቶችን ማሟላት ችላለች። ይህ የመሠረተ ልማት ግንባታ ደግሞ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ለማዘጋጀት የሚያስችላት ነው። ከዚህ ቀደም ሃገሪቷ ምናልባትም ትታወቅ የነበረው እንደ ሌሎች የዓረብ ሃገራት ባለጸጋዎች በአውሮፓ ታላላቅ የሚባሉ የእግር ኳስ ክለቦችን ድርሻ በመግዛት እንዲሁም ስፖንሰር በመሆን ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በቀጥታ በስፖርቱ ተሳታፊ በመሆንና ለስፖርትም አስፈላጊውን ዋጋ በመክፈል የስፖርት ውድድሮች ማዕከል የመሆን ፍላጎቷን በማሳካት ላይ መሆኗ በግልጽ እየታየ ነው።

እኤአ በ2019 የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮናን ዶሃ ላይ ያስተናገደችው ሃገሪቷ፤ እኤአ በ2019 እና 2020 ደግሞ የፊፋ የክለቦች ሻምፒዮናንም አሰናድታ ነበር። በሌሎች ስፖርቶችም በተመሳሳይ በርካታ ሻምፒዮናዎችን የማስተናገድም ዕድል አግኝታለች። አሁን ደግሞ የዓለምን ሕዝብ በእግር ኳስ ዋንጫው አሰባስባለች። በዚህም ሃገሪቷ በቀጠናው፣ በአህጉሯ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ዕውቅና ከማሳደግ ባለፈ በቀጣይም ሌሎች ስፖርታዊ ውድድሮችን የማስተናገድ ተዓማኒነትን አግኝታለች። ይህም ኳታር እኤአ እስከ 2030 ለማሳካት ያለመችው ስትራቴጂክ እቅድ ሲሆን፤ ስፖርት ከነዳጅ ከምታገኘው 60 በመቶ ገቢዋ ባሻገር አዲስ የገቢ ምንጭ ይሆናት ዘንድ አሁንም አጠናክራ በመሥራት ላይ ትገኛለች።

ኳታር ዓለም ዋንጫውን ተከትሎ ለስታዲየሞች፣ ለሆቴሎች፣ ለመንገድና ሌሎች መሠረተ ግንባታዎች ከ220ቢሊየን ዶላር በላይ ያወጣችበት እንደሆነም ይነገራል። ይህ ደግሞ የዓለማችን ውዱ የዓለም ዋንጫ ያደርገዋል። ነገር ግን ከዚህ ውድድር ብቻ ከ6ነጥብ5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ትርፍ ታገኛለች ተብሎ እንደሚጠበቅም ዘ ኢኮኖሚክ ታይም ያስነበባል። ዓለም ዋንጫው ካወጣችው በላይ ትርፋማ የሚያደርጋት ሲሆን፤ ከአራት ዓመት በፊት ሩሲያ ካገኘችው ገቢ በ1ነጥብ3 ቢሊዮን ዶላር ብልጫ ያለው በመሆኑ በታሪክ ቀዳሚ ያደርገዋል።

ስፖርት የወቅቱ የዓለም ትኩረት የሆነውና ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ የሚባለውን ቱሪዝምን እንደሚያበረታታም ይታወቃል። ሃገራት ከተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መስህቦቻቸው ጎን ለጎን ቱሪስቶችን ለመሳብ በስፖርታዊ ውድድሮችንና ክንዋኔዎች ላይ እየሠሩ ነው። በመሆኑም ዓለም ዋንጫን መሰል ታላላቅ ውድድሮች ማዘጋጀት በሌላ መንገድ የስፖርት ቤተሰቡን መጋበዝ ነው። በዚህ ረገድ ኳታር ብዙ ተጠቅማለች። ሃገሪቷ ትንሽ እንደመሆኗ ያላት 2ነጥብ 6 ሚሊዮን ሕዝብ ብቻ ነው፤ ከእነዚህ መካከል የኳታር ዜግነት ያላቸው 313 ሺ የሚሆኑት ብቻ ናቸው። በአንጻሩ 2ነጥብ3 የሚሆኑት ለሥራና በሌሎች ምክንያቶች በሃገሪቷ ነዋሪ የሆኑ ናቸው። በዚህ ወቅት ደግሞ የዓለም ዋንጫውን ተከትሎ ከ1ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የእግር ኳስ ወዳጆች በኳታር ከትመዋል። ከዚህም ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም መረዳት አያዳግትም።

ዘርፈ ብዙ የሆነው ስፖርት ከውድድርና አካላዊ እንቅስቃሴነቱ ባለፈ በርካታ ጉዳዮችን እንደሚነካ ይታወቃል። አንድን ውድድር ወይም ስፖርታዊ ክንዋኔ ተከትሎ የሚገኘው ገጸበረከት ሰፊ በመሆኑ ሃገርና ሕዝብ የጥቅሙ ተቋዳሽ ይሆናል። ለአብነት ያህል ዓለም ዋንጫውን ተከትሎ የሚገነቡት ስታዲየሞች ብቻም ሳይሆኑ የአውሮፕላን ማረፊያዎች፣ ሆቴሎች፣ የገበያ ማዕከላት እና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ናቸው። ይህም የውድድር አዘጋጇን ሁለገብ ሃገራዊ እድገትን የማፋጠን ሚና ይኖረዋል። በዚህ ደግሞ ዜጎች ተጠቃሚ ከመሆናቸውም ባለፈ አዳዲስ የሥራ መስኮችንም የመፍጠር ዕድሉ ከፍተኛ ይሆናል።

ምዕራባውያን ሃገራት ከዓረቦች ጋር በጥቅም ጉዳይ ካልሆነ በቀር ታሪካዊ ተቃርኖ ያላቸው ሃገራት መሆናቸው ግልጽ ነው። እንደ ዓለም ዋንጫ ያሉና በሚሊየኖች የሚቆጠሩ የስፖርት ቤተሰቦችን በአንድ የሚያሰባስቡ ውድድሮች ግን ፖለቲካን የማለዘብና ወንድማማችነትን የመቀስቀስ አቅማቸው ከፍተኛ ነው። በተለይ ሕዝብና ሕዝብን በማገናኘት፣ በባህል ልውውጥና መልካም ገጽታን በመገንባት ረገድ ሚናቸው እጅግ ከፍተኛ ነው። ኳታርም በዓለም ዋንጫ አስተናጋጅነቷ ካገኘቻቸው ጠቀሜታዎች መካከል ዋነኛው ገጽታዋን መገንባት መቻሏ ነው። ከመመረጧ አንስቶ ሲቃወሟትና በደሏን ሲያጋንኑ የነበሩ አካላት አሁን ላይ ተቃራኒ ሁኔታ መሆኗን ይረዳሉ።

የራሱ ባህልና እምነት እንዳለው ሀገር ኳታር የራሷን አቋም ያንጸባረቀችበት መንገድም አበረታች ነው። ዜጎች በራሳቸው ወግና ባህል መሠረት የፈለጉትን የማድረግ መብት እንዳላቸው ሁሉ በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ምክንያት ሕዝቡን የማይወክልና ባህሉንም ሊበርዝ የሚችል ጉዳይን አሜን ብሎ የመቀበል ግዴታ የለበትም። በተለይ እንደ አፍሪካ ባሉ አህጉራት አሁንም ድረስ የማንነት መደበላለቅና የራስን ባህል ማሳነስ ከባድ ችግር ነው። ይህ የሚከሰተው ደግሞ በተለያዩ ሁኔታዎች በሚከሰተው የባህል መበረዝ ነው። ታዲያ ኳታር ከሕዝቧ ፍላጎት ውጪ የሆነን ነገር አለመቀበሏና በሌሎች ውድድሮች ላይ በመጠጥ ምክንያት ስፖርታዊ ጨዋነት እንዳይደፈርስ በማድረጓ ትውልዷ ሲያመሰግናት ይኖራል።

በመጨረሻም የስፖርታዊ ውድድሮች ሁሉ መደምደሚያ አሸናፊና ተሸናፊነት ነው። ኳታርም ጣፋጩን የአሸናፊነት ጽዋ ተጎንጭታለች። በአቋሟ በመጽናቷ እንዲሁም በስፖርት በማመኗ ያገኘችው ውጤት ኢትዮጵያን ጨምሮ ለብዙዎች ተምሳሌት ይሆናል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ዛሬም ባልተቃና ኑሮ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ወላጆቿ ስሟን ሲያወጡላት በተለየ ምክንያት ነበር። እነሱ በልጃቸው ስያሜ ህይወታቸውን፣ ኑሯቸውን ማሳየት ይሻሉ ። በስም ማውጣት ውስጣቸውን መግለጽ ይፈልጋሉ። እናት አባት ፍላጎትን በልጃቸው ሰበብ መግለጽ ፣ መንገር ቢሹ አዲሷን ጨቅላ «በትራቀች »ሲሉ ሰየሟት። በትራቀች ማለት በጉራጊኛ «ባደገች፣በወጣች፣በተመነደገች » እንደማለት ነው።

በትራቀች በጉንችሬ አንዲት የገጠር ቀበሌ ልጅነቷን እንደእኩዮቿ አሳለፈች። ወላጆቿ አስቀድመው እንደተመኙት በትራቀች ለእነሱ ህይወትና ኑሮ ስኬት ዕድገታቸው ትሆን ዘንድ እያሰቡ አሳደጓት። ልጅነቷ ግን እንደታሰበው ባመረ መንገድ አልቀጠለም። የህጻንነት ዕድሜዋን በወጉ ሳታጣጥም ወላጅ እናቷ «እዚህ ነኝ» ሳይሉ ከቤት ጠፉ፣ ራቁ ።

ይህ አጋጣሚ ለመላው ለቤተሰብ ፈታኝ ሆነ። የእማወራዋ በድንገት መለየት ሁኔታዎችን አከበዱት። ልጆች ያለእናት፣ አባወራውም ያለሚስት ኑሮን ለመምራት ህይወትን ለመቀጠል ተቸገሩ። እናታችን ትመጣለች፣ ትመለሳለች፣ ያሉ ልጆች ጠዋት ማታ ከበር ቆሙ፣ ዓይናቸውን አሻግረውም በናፍቆት ተሳቀቁ ። እናት እንደታሰበው አልመጡም። ልጆች ያለማቋረጥ በተስፋ ጠበቁ። አባወራው የሚስታቸውን መመለስ እያሰቡ ቀን ቆጠሩ ። የታሰበው አልሆነም። ከቤት የወጡት ወይዘሮ ሳይመለሱ ቀናት ወራት ነጉዱ።

**አዲስ ህይወት...**

ወራት ያስቆጠረው የወይዘሮዋ መጥፋት ተስፋ አስቆርጧል። ርቀው መሄዳቸውን ያወቁት አባወራው ከእንግዲህ እንደማይመለሱ ያወቁ ይመስላል። እንዲህ ማሰባቸው በቀጣይ ህይወታቸው ላይ እንዲወስኑ አድርጓል። እማወራዋ «ቤቴን ፣ ልጆቼን» ብለው ካልተመለሱ ትዳራቸውን እዳልፈለጉት ብዙዎች ገምተዋል።ይህ ግምት የአባወራውን ውስጥ ይበልጥ አነሳስቷል።አዲስ ጎጆ፣ አዲስ ህይወት መቀጠል እንዳለባቸው ካመኑበት ቆይቷል።

የታሰበው አልቀረም። አሁን ሰውየው ሌላ ሚስት አግብተዋል ፣ በአዲስ ትዳር አዲስ ህይወት መስርተው ልጆቻቸውን ማሳደግ ፣ ኑሯቸውን መምራት ይዘዋል።አዲሲቷ ወይዘሮ ለቤት ፣ለትዳሯ መበርታት መጣር ይዛለች። አባወራዋ ቀድሞ ያጣውን ልትሞላ፣ በአዲስ ሀይልና ብርታት እየታየች ነው፣ ሰውዬው በሙሽሪት ቅልጥፍና ሀሳባቸው ሞልቷል። የልባቸው ደርሷል። ይህ ስሜት ግን ከልጆች ልብ የደረሰ አይመስልም። ደስታ ከራቀቻው ቆይቷል። ሁሌም አዲሷን ወይዘሮ ሲያዩ እናታቸውን ያስታውሳሉ። እያስታወሱ ሆድ ይብሳቸዋል። ይተክዛሉ፣ያለቅሳሉ።

በትራቀች እናቷን ካጣች ወዲህ ውስጧ ሰላም የለውም። በየምክንያቱ ታኮርፋለች። ትበሳጫለች። ይህ እውነት ከእንጀራ እናቷ አላስማማትም። ደስተኛ አለመሆኗ፣ ሳቅ ጨዋታን መንፈጓ ወይዘሮዋን አናዷል።ሁሌም የእንጀራ ልጇን ባህርይ በመጥፎ ተርጉማ በጥርጣሬ ታያታለች ።

**ውሳኔ...**

ከቀናት በአንዱ በትራቀች ስታስብ ስታብሰለስል በቆየችበት ጉዳይ ላይ ወሰነች። ከእንግዲህ በተወለደችበት ቤት ማደግ ፣ መኖር እንደሌላባት ቆርጣለች ። ለውሳኔዋ ተጨማሪ ቀን አልሰጠችም። ቀጣይ ህይወቷ አዲስ አበባ እንዲሆን አሰባለች። የዛኑ ቀን በእጇ ከነበራት ጥቂት ገንዘብ ጥቂቱን አንስታ መኪና ተራ ሄደች ።

ለመንገዷ ከአምስት ብር በላይ አልተጠየቀችም። መኪናውን ተሳፍራ መንቀሳቀሱን ጠበቀች ። በእጥፍ የቆየ መሰላት። ተሳፋሪዎች ወንበሩን ሲሞሉ ሞተሩ ተንቀሳቀሰ። በንቃት ራሷን አዘጋጀች። አገሯን ስትለቅ የነገ ህይወቷን አሰበች። ከዛሬ ነገ እንደሚሻል ተሰማት ። ደስ እያላት ስሜቱን አጣጣመችው።መኪናው ጉዞ ሲጀምር የአዲስ አበባን አቅጣጫ ያዘ። ልቧ ደጋግሞ ሲመታ ተሰማት።ቦታ አልሰጠችውም።ዓይኖቿን ተክላ መንገዷን ተከተለች።

**አዲስ አበባ...**

በትራቀች ዕድሜዋ ከአስራ ሁለት አያልፍም ። አዲስአበባን የምታውቃት በስም ብቻ ነው ። ከመኪናው ወርዳ ካሰበችው ደረሰች። ልደታ አካባቢ ያሉ አክስቶቿ ፊት አልነሷትም። መምጣቷ ሳያስከፋቸው እንግድነቷን ተቀበሉት። ትንሽዋ በትራቀች ለቀረባት ሁሉ ባዳ አልሆነችም። የታዘዘችውን ሰርታ ፣የተሰጣትን ጎርሳ መስላ ማደርን አወቀች። ዕቃ ማጠብና ፣ መላላክ ስራዋ ሆነ ።

ጥቂት ቆይቶ ዘመዶቿ ሌላ አሰቡ ። ከሰው ቤት ተቀጥራ ብትሰራ፣ ገንዘብ እንደምታመጣ መከሩ ። ምክክራቸው ሲጸድቅ በቤት ሰራተኝነት አስቀጠሯት። በትራቀች የእድሜዋ ለጋነት ብዙ አላራቃትም። ጥቂት ቀን ቆይታ ተመልሳ መጣች ። አክስቶች በግምት ምክንያቷን ጠየቁ። ስራው እንደከበዳት ፣ አቅሟን እንደፈተናት ተናገረች። መልሷን ባይወዱትም «ይሁን» ብለው ተቀበሏት።

በሌላ ቀን ለበትራቀች ሌላ ስራ ተገኘላት ። ስራው ሞግዚነት ነው ። ጨርቋን ቋጥራ፣ ልትበረታ አስባ ከተባለው ቤት ደረሰች ። የቤቱ እመቤት ሰው በማግኘቷ ተደስታለች። በትራቀችን እንዳየች አልቆየችም። የመጀመሪያ ግዴታዋን ልጇን በማሳዘል አስጀመረቻት። ትንሽዋ ሞግዚት የወፍራሙን ህጻን ክብደት መቋቋም አልቻለችም። ከጀርባዋ ያለው ልጅ ከላይዋ ተመቻችቶ ከፉኛ አንገዳገዳት ። ቀጫጫ እግሮቿ ሸክሙን ሊይዙ ተቸገሩ ። የልጅነት አካሏ ተንቀጠቀጠ። ትከሻ፣ ወገቧ ከዳት፣ መላ ሰውነቷ ተብረከረከ።

በትራቀች አሁንም በአዲሱ ስራ አልዘለቀችም ። ልብሷን ቋጥራ በሄደችበት እግሯ ተመለሰች። አክስቶቿ ከስራዋ መውጣቷን አልፈቀዱም። መግባት ፣ መውጣት ድግግሞሹ ቀጥሏል ፣ይህ እውነት ከአክስቶች ጋር መሰልቸትን አስከትሎ ተያዥ እንድታጣ፣ ከሌላ እንዳትቀጠር ሰበብ ሆኗል።

አሁን በትራቀች ዕድሜዋ ጨምሯል። ከትናንት ዛሬ የተሻለውን እያሰበች ነው። በየጊዜው ስራ ብታገኝም ተያዥ የላትም። የአክስቶቿ ውሳኔ እያስከፋት ነው። ህይወቷ በሰው ቤት ስራ መወሰኑ ጭምር ያሳስባት ይዟል ።እንዲህ መሆኑ የትንሽዋን ልጅ ልብ አሸፈተ ።ደግማ ደጋግማ አሰበች። ከአክስቶቿ ቤት ይሻለኛል ያለችውን መረጠች። በድንገት ከቤት ወጥታ ከጎዳና ዋለች።

**ጎዳና ነው ቤቴ**

በትራቀች በድንገት ከቤት ወጥታ ከጎዳና መዋሏ አሳሳቢ ሆኗል ። እንደትናንቱ ህጻን ባትሆንም ማንነቷ ከስጋት ላይ ነው። እሷም ሴት መሆኗ፣ የደጁን ዓለም አለማወቋ እንደሚከብድ ታውቃለች። ። ህይወቷ በዚሁ ከቀጠለ የነገውን አታውቅም ።

ኑሮን አስከትለምድ ጥቂት ጊዜን በልመና አሳለፈች። ያገኘችውን እየቀመሰች የጎዳናውን ብርድና ጸሀይ ለመደችው። ጥቂት ቆይታ ግን ልመናውን ትታ በሌላ አማራጭ ተገኘች።ልደታ አካባቢ ውሎዋን በዕጣን ሽያጭ እያሳለፈች አዳሯን ከቤተክርስቲያኗ ግንብ ማድረግ ጀመረች።

ቀኑን ከጎኗ ሆና ቄጤማ የምትሸጠው ሴት እንደሷው መጠጊያ የላትም። አዳራቸውን በአንድ አድርገው ሌሊቱን አብረው ይገፋሉ። ህይወቷ በጎዳና የቀጠለው በትራቀች ውሎ አዳሯ ከዚህ ህይወት አልረቀም። ቀን ጸሀዩ ፣ሌት ብርድና ውርጩ እያንገላታት ሁለት ዓመታትን ቆጠረች።

አንድ ቀን ግን ከዚህ ያልተመቸ ህይወት የሚታደጉ በጎ ዓይኖች አረፉባት ። አንዲት ሴት ድንገት ቀርባ እሷንና ቄጤማ ሻጭዋን ሴት አዋየቻቸው ። እነሱ ውጭ ከሚያድሩ በእሷ ምግቤት አካባቢ ቢጠጉ እንደሚሻል ነገረቻቸው። ሴትዬዋ ለበትራቀች ስሜት አልከበደችም ። ያለችውን ሰምታ ፈጥና ተስማማች ።



የታሰበላቸው ተሳካ። ባለቄጠማዋ ከአንድ ቦታ በትራቀች ከዘበኛው ቤት አጠገብ እንዲያድሩ ተወሰነ። ሁለቱም ሀሳቡን በምስጋና ተቀብለው የጎዳናውን ጥግ ለቀቁ። ከተዘጋጀላቸው ስፍራ እያደሩም የዕጣን ቄጤማ ስራቸውን ቀጠሉ።

አንድቀን ግን ያልታሰበው ሆነ። በድካም የዋለችው በትራቀች ዕንቅልፍ እንደጣላት ያወቀው ዘበኛ ካለችበት ደርሶ ሊደፍራት ታገለ ። ዕንቅልፍ የለሸዋ ሴት በዋዛ እጇን አልሰጠችም ። እየጮኸች ራሷን ከጥቃት ለመከላከል ታገለች። ድምጽዋን የሰማችው ባልንጀራዋ ሮጣ ደረሰችላት ። የእሷን ፈጥኖ መምጣት ያየው ዘበኛ ሮጦ አመለጠ። እስከዛሬ ጎዳና ስትኖር ያልሆነባትን የመደፈር ሙከራ እያሰበች በትራቀች አለቀሰች፣ከልቧ አዘነች።

ይህ አጋጣሚ ግን ሌላ አጋጣሚን አስከተለ። ሁኔታውን የሰማች አንዲት የዕጣን ደንበኛዋ ከእሷ ማዕድ ቤት እንድትጠጋ ፈቀደችላት። ሴትዮዋ እንዳለችው ሆኖ ከቤቷ ወስዳ ከማድቤቱ አሳረፈቻት። እስካሻት ድረስ ብትኖር ፣ ውጭ እንደማትላትና ልጆቿም እንደማይጥሏት ቃል ገባችላት። በትራቀች። ሴትዬዋ እንደቃሏ ሆነች። በትራቀች የልቧ ሀሳብ ሞላ ፈጣሪዋን ደጋግማ አመሰገነች።

ጥቂት ቆይቶ ወይዘሮዋ ሌላ ሀሳብ አመጣች።በብቸኝነት ከምትኖር ልትድራት እንደምትሻ አሳወቀቻት። በትራቀች አልተግደረደረችም ። በሀሳቧ ተስማምታ በይሁንታ ጋብቻውን ተቀበለች ።

**ህይወት በጎጆ**

አሁን በትራቀች ባለትዳር ወይዘሮ ሆናለች ። ከባለቤቷ ጋር መኖር ከጀመረች ወዲህ ልጆች ወልዳ እያሳደገች ነው ። ትዳሯ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት መልካም የሚባል ነበር ። ጥቂት ቆይቶ ግን በባለቤቷ ላይ የሚታየው ባህሪይ አሳሳቢ ሆነ። እሷ ባታውቅም ባለቤቷ ቀደም ሲል የዓዕምሮ ታማሚ ነበር። ቆይቶ ህመሙ ሲያገረሽ እሷና ልጆቿ ካልታሰበ ፈተና ወደቁ።

ባለቤቷ አማኑኤል ሆስፒታል የህክምና ክትትል አለው። እሱን ከሚፈለገው አድርሶ ወደቤት ለመመለስ ጉልበትና ስልት ይጠይቃል። ይህን ለማድረግ አቅሙ የሌላት ወይዘሮ በታመመ ቁጥር እየታመመች አብራው በእንግልት ቀጥላለች። በትራቀች ቤተሰቧን ለማኖር የዕጣን ንግዷን ትሰራለች። በእሷ ትከሻ ብቻ የወደቀው የቤቱ ኑሮ የተሟላ አይደለም። አልጋ ፍራሽ፣ ብርድልብስና ሌላም ቁሳቁስ በወጉ የለም።

ለዕለት ፍላጎት ተብለው የተቀመጡ አንዳንድ ቁሳቁሶች በዓይምሮ ታማሚው አባወራ ይሰባበራሉ፣ ይወረወራሉ። ወይዘሮዋ እሱን ጨምሮ ልጆቿን ለመመገብ የሚቻላት አልሆነም። ከዕለት ገቢዋ ሰርታ ከምታመጣው በቀን አራት እንጀራ ብትገዛ ለባለቤቷ ሁሉንም ትሰጣለች። እንጀራው የግዢ ነውና ሆዱን አይሞላም። በየጊዜው ‹‹ምግብ አምጣ›› ለሚለው ፍላጎቱ አይበቃም።

ባለቤቷ ጤናማ ሳለ ሮጦ አዳሪ ነበር። ያገኘውን ተሸክሞ ለቤቱ ለመሆን ብርቱ ነው። የዛኔ ቤተሰቡ ለዕለት ጉርስ አያጣም። በእሷና በባለቤቷ የጎደለው ሞልቶ ፣ ልጆች በሰላም ተኝተው ያድራሉ። እሷም ልብስ አጥባ ጉልት ተቀምጣ ከምታገኘው ለቤቷ ስትሆን ኖራለች።

የነ በትራቀች ቤት በላያቸው ከወደቀ ቆይቷል። አሮጌውን አንስቶ በተሻለ ለመጠገን አቅም ይሉት የለም። ለምግብ እንጂ ለስራ ያልደረሱት ልጆች ውለው ሲገቡ የእናታቸውን እጅ ያያሉ። ሁሌም ይርባቸዋል፣ ይበርዳቸዋል። ታማሚው አባወራ የትኛውም ድምጽ ይረብሸዋል። የማሽን ፣ የሙዚቃ፣ የሰዎች ጫጫታ ባወከው ጊዜም ዕቃ እየወረወረ፣ አብዝቶ እየጮኸ ይወራጫል ።

የበትራቀች ልጆች አቅማቸው ደርሶ እናታቸውን የሚያግዙ አይደሉም። የአባታቸውን ጩኸት እንደግዴታ ተቀብለው አብረውት ይኖራሉ። በተሰበረው በርና መስኮት፣ በወደቀው ማገርና ግድግዳ የሚገባው ብርድና ንፋስ ለቤተሰቡ ችግር ሆኖ ዘልቋል ። ቤቱ የቀበሌ ነውና በትራቀች እንዲታደስላት ስትወተውት ኖራለች። አልተሳካም።

አንዳንዴ ቤተሰቡ ከአቅም በላይ የሚባል ችግርን ይጋፈጣል።ወይዘሮዋ ብዙ ችግሮችን አሳልፋለች፣ ችግሯን ለመፍታት ፣ መላ ዘዴውን ለማምጣት ብዙ ደክማለች። ከባለቤቷ ህመም ተያይዞ የሚገጥሟት ፈተናዎች ግን ከሁሉም ይብሳሉ።

በአንድ ወቅት ታማሚው አባወራ ለተለመደው ህክምና ወደሆስፒታል አቀና ። ሀኪሞቹ ተገቢውን ምርመራ አድርገው መድሀኒት አዘዙለት። መድሀኒቱ ለሶስት ወራት የሚያገለግል ነበር። ታማሚው ግን የተሰጠውን የሶስት ወራት ክኒን በአንድጊዜ ወሰደው ። በወቅቱ ህይወቱን ባያጣም በጤናው ላይ ተጨማሪ እክል ተፈጠረ።በቤቱ ሆኖ ህክምናውን እንዲወስድም ምክንያት ሆነ።

ይህ አጋጣሚ ወይዘሮዋን እንደልብ ወጥታ እንዳትሰራ ፣ያገኘችውን ለልጆቿ አቃምሳ እንዳታድር ሰበብ ሆኖ ዛሬን ዋጋ እያስከፈላት ይገኛል።አሁን የበትራቀችን ባለቤት ሆስፒታል የሚያመላልሰው የለም። ለእሱ ጤና፣ ለራሷና ለልጆቿ ህይወት ማለዳ የምትሮጠው ወይዘሮዋ ብቻ ነች።

**ዛሬ...**

በትራቀች በላይዋ ሊወድቅ ያዘነበለ ቤቷ የዘወትር ስጋቷ ነው። የልጆቿ አለመድረስና የእሷ የብቻ ድካምም ያሳስባታል። ከሁሉም የባለቤቷ ጤና ማጣት የህይወቷ ጎዶሎ እንደሆነ ይሰማታል። የእሷ የአንድ እጅ ድካም ከወቅቱ የኑሮ ውድነት ተዳምሮ እያንገዳገዳት ነው።

አሁን በቅርቡ በልደታ አካባቢ በተከፈተው የምገባ ማዕከል ተጠቃሚ ሆናለች። ማዕከሉ የእሷን ችግር ከሌሎች በመለየት የሶስት እንጀራ ተጠቃሚ አድርጓታል። የያዘችውን ይዛ፣ ተጨማሪውን አክላ ለህመምተኛው ባለቤቷ ትደርሳለች ። በትራቀች ሁሌም አመስጋኝ ልብ አላት። ጎዶሎዋን ትታ ፣ የሆነባትን ረስታ በተደረገላት ትረካለች። ዛሬም ባልቀናው ኑሮ፣አሁንም ባልሞላው ህይወት ትባዝናለች ። ስለነገው ግን በልጆቿ ተስፋ አትቆርጥም።

# ስፖርት




## የዳይመንድሊግ መርሃግብር አዳዲስ ለውጦችን ይዞ መጥቷል

ብርሃን ፈይሳ



**የ2023 ዳይመንድ ሊግ ውድድሮች የዓለማችንን ታላላቅ አትሌቶች እንደሚያፎካክሩ ይጠበቃል፣**

የዓለም አትሌቲክስ ከሚያዘጋጃቸው ትልልቅ ዓመታዊ ውድድሮች መካከል አንዱ በመም ሩጫዎችና በሜዳ ተግባራት የውድድር ዓይነቶች) የዓለም አትሌቶች የሚፎካከሩበት ዳመንድሊግ ነው:: እአአ ጀምሮ ይካሄድ የነበረውን ጎልደን ሊግ ውድድርን ተክቶ እአአ ከ2010 ጀምሮ እየተከናወነ የሚገኘው ይህ ውድድር ዙሮች ያሉት ሲሆን፤ በተለያዩ የዓለም በመዘዋወር ይካሄዳል::

ኢትዮጵያዊያን ወጣትና በስፖርቱ ትልቅ ስኬት ላይ አትሌቶችን ጨምሮ በመላው ዓለም አትሌቶች የሚካፈሉበት የዳይመንድሊግ የተለያዩ የዓለም ክብረወሰኖች እንዲሁም ሰዓቶች የሚመዘገቡበትና ከፍተኛ ፉክክር የሚስተዋልበት በመሆኑ ትልቅ ይሰጠዋል::

በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው የፈረንጆቹ ዓመት በተካሄደው የዳይመንድ ሊግ ውድድር በርካታ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ሲሳተፉ የቆዩ ሲሆን፤ የዓለም የ3ሺ ሜትር የብር ሜዳሊያ አሸናፊዋ አትሌት የወርቅውሃ ጌታቸው የዚህ ዳይመንድሊግ አጠቃላይ አሸናፊና የዋንጫ ተሸላሚ መሆና ይታወሳል:: የ3ሺ ሜትር መሰናክል አትሌቷ በሞናኮ እና ዙሪክ ባካሄደችው ውድድር ውጤታማ ልትሆን እንደቻለች አይዘነጋም:: ወጣቷ አትሌት በአሜሪካው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና በርቀቱ የብር ሜዳሊያ ካጠለቀች ጥቂት ጊዜያት በኋላ ዳግም በዳይመንድሊግ ባለድል መሆኗ ደግሞ በአትሌቲክስ ቤተሰቡ ዘንድ አድናቆትን አትርፎላታል::

ከአንድ ወር በኋላ በሚመጣው አዲሱ የፈረንጆች ዓመት የሚካሄደው የ14ኛው ዳይመንድ ሊግ መርሃ ግብርም ከወዲሁ ይፋ የተደረገ ሲሆን በርካታ የዓለማችን አትሌቶችም በጉጉት እየጠበቁት ይገኛሉ::

የ2023 የዳይመንድሊግ ውድድር አዳዲስ ጉዳዮች የተካተቱበት መሆኑን የዓለም አትሌቲክስ ይፋ ያደረገው መረጃ የሚጠቁም ሲሆን በመጪው የፈረንጆቹ ዓመት 2023 ግንቦት ወር ላይ ይጀመራል:: መነሻውን በኳታሯ ዶሃ የሚያደርገው ይህ ውድድር ከአምስት ወራት በኋላ በአሜሪካዋ ዩጂን መደምደሚያውን ያደርጋል:: ይህም ያልተለመደ ሁኔታ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም ይታወቅ የነበረው ውድድሩ ዙሪክ እና ብራሰልስ ላይ በሚኖረው ደማቅ መርሃ ግብር ይጠናቀቅ ነበር::

ውድድሩ በ12 ሃገራት 15 ከተሞች ላይ ሲከናወን እያንዳንዳቸው ከተሞች የአንድ ቀን መርሃ ግብር ያሰናዳሉ:: ከውድድሮቹ የሚልቁት በአውሮፓ አህጉር የሚዘጋጁ ሲሆን፤ በዓመቱ 10 የአውሮፓ ከተሞች የማስተናገድ እድል አላቸው:: ታላቋ አህጉር እስያ ሶስት ውድድሮች ሲካሄዱባት አፍሪካ እና አሜሪካ አንድ አንድ ከተሞቻቸው ውድድሩን ያከናውናሉ:: ማጠቃለያው የሚደረግበት ዩጂን ደግሞ የሁለት ቀናት ቆይታ ይኖረዋል:: እአአ የ2024 ዳይመንድ ሊግ መዝጊያ ብራሰልስ ስታዘጋጅ የ2025ቱን ደግሞ ዙሪክ ትሆናለች:: ቀጣዮቹን ሁለት ዓመታትም በተመሳሳይ አውሮፓዊያኑ ከተሞች በመፈራረቅ የመዝጊያ ስነስርዓቱን እንደሚያካሂዱም የተያዘላቸው መርሃ ግብር ያሳያል::

በመጪው የዳይመንድ ሊግ ውድድር ላይ አዳዲስ ውድድሩን የሚያስተናግዱ ከተሞች የተካተቱ ሲሆን፤ ላለፉት አራት ዓመታት አዘጋጅነቷን አቋርጣ የቆየችው ለንደንም በድጋሚ ወደ አዘጋጅነተ መመለሷ ታውቋል:: እአአ ከ2010-2019 ባሉት ዳይመንድሊግ ውድድሮች ተሳታፊ የነበረችው ለንደን አይረሴ የሆኑ ክስተቶችን አስተናግዳለች:: ከወራት በኋላም በንግስት ኤልሳቤት ኦሊምፒክ ፓርክ ዳግም ዳይመንድ ሊግን ለማስተናገድ ዝግጅቷን አጠናቃለች:: በተጨማሪም ሌላኛዋ የአውሮፓ ሃገር ፖላንድ ውድድሩን የሚያሰናዱን መቀላቀሏ ታውቋል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ዳይመንድ ሊግ እንዲካሄድበት የተመረጠው የፖላንድ ከተማ ደግሞ ሲሊዚያ የሚሰኝ ነው:: በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ውድድሩን ማስተናገድ ያቆሙት ቻይናዊያኑ ከተሞች ሻንጋይ እና ሺንዢንም በ2023ቱ ዳይመንድ ሊግ ወደ አዘጋጅነታቸው ተመልሰዋል:: አራት ወራትን ይፈጅ የነበረው ዳይመንድ ሊግ በመጪው ዓመት የተለያዩ መዳረሻዎችን በመጨመሩ ምክንያት የሚፈጀው ጊዜም ወደ አምስት ወራት ማደጉ ተጠቁሟል::


ግብርና ሚኒስቴር MINISTRY OF AGRICULTURE

ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ የሚታተም


## የሌማት ትሩፋት

ሸምሱዲን ዩሱፍ




**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም ባስጀመሩበት ወቅት**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ሰፊ የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ባለቤትና ምቹ የግብርና ስነ-ምህዳር አላት:: በእንስሳት ቁጥርም ከአፍሪካ አንደኛ ነች:: ነገር ግን ባላት እንስሳት ቁጥር ልክ በተለይ በወተት፣ በዶሮና በማር ምርቶች በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ መሆን አልቻለችም:: ችግሩንም ከስር መሰረቱ ለመፍታት በይፋ የተጀመረውን ሀገራዊ የሌማት ትሩፋት ፕሮግራምን በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል::

በዝቅተኛ የወተት ምርታማነት ምክንያት ከፍተኛ የወተት ምርት የፍላጎት ክፍተት ይታያል:: ካሉን 15 ሚሊዮን የወተት ላሞች ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ የሀገረሰብ ዝርያ ላሞች ሲሆኑ አማካይ ምርታማነታቸው በቀን 1.5 ሊትር እና የአለባ ወቅትም 210 ቀን ብቻ ነው:: አጠቃላይ አመታዊ የወተት ምርት 7.1 ቢሊዮን ሊትር ሲሆን አመታዊ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ከ66 ሊትር አይበልጥም (CSA, 2021):: ይህም በአለም-አቀፋዊ ልኬት መሰረት ለአንድ ጤነኛ ሰው በአመት ከሚያስፈልገው 200 ሊትር መጠን እጅጉን ያነሰ ነው:: የተቀመጠውን ዓለም-አቀፋዊ ልኬት ላይ ለመድረስም አሁን ያለውን የወተት ምርት በሁለት እጥፍ መጨመር ያስፈልጋል::

በሀገራችን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሀገረሰብ ዶሮዎች ቢኖሩም ምርታማነታቸው አነስተኛ በመሆኑ የሚገኘው ምርት በቂ አይደለም:: የእንቁላል ምርት 3.2 ቢሊዮን ሲሆን አመታዊ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ 30 እንቁላል ነው (MoA, 2014 EC):: ካሉን 19.5 ሚሊየን የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች ከ75 በመቶ በላይ የሀገረሰብ ዶሮዎች ሲሆኑ አማካይ ምርታማነታቸው በአመት 40 እንቁላል ይሆናል:: በዘመናዊ የዶሮ እርባታ በኩል አማካይ ምርታማነት በአመት 270 እንቁላል ቢደርስም ባለን የዶሮ ቁጥር ልክ በቂ ምርት ማግኘት አልተቻለም (MoA, 2014 EC):: የአለም-አቀፍ እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት ከደረሱበት አመታዊ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ አንፃር የኛ በጣም አነስተኛ በመሆኑ አሁን ያለውን ምርት በትንሹ በአምስት እጥፍ መጨመር ይጠይቃል::

በሀገራችን 7 ሚሊየን የሚጠጋ የንብ መንጋ ይገኛል:: ይህም ከብዙ አፍሪካ ሀገራት በቁጥር የሚበልጥ ቢሆንም 96 በመቶ በባህላዊ ቀፎ የሚነባ በመሆኑ ምርቱ ዝቅተኛ ነው:: በአመት 13 ሺህ ቶን ማር ቢመረትም ካለን ንብ መንጋ ቁጥር አንፃር በቂ አይደለም::

የእንስሳት ዘርፉ ለብዙ አመታት ትኩረት ተነፍጎ ቢቆይም ከአራት አመታት ወዲህ ግን ግብርና ሚኒስቴር ዘርፉን ተብትበው ከያዙት ችግሮች አላቆ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየሠራ ይገኛል:: የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲን በማሻሻል የ10 ዓመት መሪ ዕቅድና ስትራቴጂዎችን ቀርፆ ወደ ሥራ ገብቷል:: ዘመናዊ የግብርና ተክኖሎጂዎችን በመጠቀምም አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል::

በተለይ የከብት፣ የዶሮና የማር እርባታን በማዘመን ምርታቸውን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ሀገራዊ የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም ተቀርፆ በሀገር ደረጃ ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ከተማ በክቡር ኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በይፋ የተጀመረ ሲሆን ለተግባራዊነቱም ሁሉም ክልሎች ቃል ገብተዋል::

የሌማት ትሩፋት ሀገራዊ የወተት፣ ዶሮና ማር ምርት ማሻሻያ ፕሮግራም ነው:: ዋና ዋና ግቦቹም በአራት ዓመት (2015 - 2018 በጀት ዓመት) በሚፈለገው መጠንና ጥራት የወተት፣ የዶሮና የማር ምርትን በማሳደግ ለምግብና ስርዓተ-ምግብ ዋስትና መረጋገጥ፣ ለስራ እድል ፈጣራ፣ ለወጪ ንግድ ገቢ እና ከውጪ የሚገባ ምርት ለመተካት ለሚደረገው ርብርብ ተገቢውን አስተዋፅዖ ማበርከት ናቸው::

የሌማት ትሩፋት ዝርዝር አላማም የወተት፣ የዶሮና የማር ምርቶችን ማሳደግ ነው:: በአራቱ አመታት ውስጥ የላም ወተት ምርትን በ2014 ዓ.ም ከነበረበት ከ5.8 ወደ 10.3 ቢሊዮን ሊትር፣ የዶሮ እንቁላል ምርትን ከ3.2 ወደ 9.1 ቢሊየን፣ የማር ምርትን ከ 147 ሺህ ወደ 296 ሺህ ቶን ማድረስ ዝርዝር ዓላማዎቹ ናቸው::

ግብርና ሚኒስቴር የአስር ዓመቱን መሪ እቅድ መሰረት አድረጎ ፈጣንና ቀጣይነት የለውን የዘርፉን የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ አስር ፕሮግራሞችን ቀርፆ ወደ ትግበራ ገብቷል:: ባለፉት አራት አመታት በአረንጓዴ አሻራና በበጋ የመስኖ ስንዴ ልማት የተገኙ ስኬቶች ወደ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች እንዲስፋፉ አህጉራዊ መነቃቃትን መፍጠር ችሏል:: ይህ ስኬት በሌማት ትሩፋት ፕሮግራምም በላቀ ደረጃ የሚደገም ይሆናል::

የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም የራሱ የማስፈፀሚያ ስልቶችና ተግባራት አሉት:: ማስፈፀሚያ ስልቶቹን ብቻ ብናነሳ የመርሃ-ግብሩ ማስተባበሪያ አደረጃጀት መፍጠር፣ የቴክኒክና ክትትል ድጋፍ ማስፋፋት፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፣ የምርት ግብዓትና ቴክኖሎጅ አቅርቦት ማሳደግ፣ የምርት ግብይትና እሴት መጨመር፣ የፋይናንስ ፍላጎትና አቅርቦት አሰራር መዘርጋት ዋንኞቹ ናቸው:: መርሃ-ግብሩን በሃላፊነትና ተጠያቂነት ለመፈፀም የማስተባበሪያ አደረጃጀት በፌዴራል ደረጃ የሚደራጅ ሲሆን ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሩ የሚሳተፍበት የአብይ ኮሚቴና የቴክኒክ ቡድኖችን በማቋቋም የሚተገበር ይሆናል::

ስለዚህ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሀገራዊ የሌማት ትሩፋት ፕሮግራምን በቁርጠኝነት በመተግበር በሚቀጥሉት አራት አመታት ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ማሳካት ይጠበቅበታል::